# ምዕራፍ ስምንት

## የትውልዱ የወንጌል ባለአደራ

### ባለአደራ ማለት ምን ማለት ነው?

ባለአደራ ማለት የሌላን ሰው ንብረት፣ ገንዘብ ወይም ጉዳዮችን በአደራ ተቀብሎ የሚያስተዳድር ወይም የሚቆጣጠር ሰው ማለት ነው፡፡ ሰው ንብረቱን አደራ የሚሰጠው እንደ እኔ ሆኖ ሊያስተዳድር ይችላል ብሎ ላመነበት ሰው ነው፡፡ ይህም አደራ የተቀበለው ሰው በታማኝነት፣ በጥበብና በማስተዋል አደራውን እንዲጠብቅና በኃላፊነት የተቀበለውን ንብረት እንዲቆጣጠር ይጠበቅበታል፡፡

ክርስቲያን ሁሉ የወንጌል ባለአደራ ነው፡፡ እግዚአብሔር ክርስቲያኖችን ስላመናቸው ይህን ትልቅ አደራ ሰጥቷቸዋል፡፡ የእግዚአብሔርን ጉዳይ በእርሱ ፈንታ ሆነው እንዲያስፈጽሙ ሹመት ተሰጥቷቸዋል፡፡ ስለዚህ እነዚህ የትውልድን የወንጌል አደራ የተቀበሉ ሁሉ ብልህ መጋቢዎች፣ ባለአደራዎችና የሰማያዊ ጉዳይ ፈጻሚዎችና አስፈጻሚዎች እንዲሆኑ እግዚአብሔር ይፈልግባቸዋል፡፡ በተለያዩ ዘመናት በየትውልዳቸው ኖረውና የእግዚአብሔርን ሀሳብ አገልግለው ያለፉ የእምነት አባቶች ሁሉ ለወንጌሉ አደራ ታማኞች ሆነው ይህን ኃላፊነት ለእኛ አስተላልፈዋል፡፡ እኛ ደግሞ ባለንበት ትውልድ ወንጌልን ለማድረስና ሰዎችን የክርስቶስ ደቀመዛሙርት ለማድረግ ተጠያቂዎች ነን፡፡

ከእኛ በፊት ሮጠው ሩጫቸውን የፈጸሙ ሁሉ ያን ሩጫ ደግሞ እኛ እንድንቀጥል፣ ከእኛ በኋላ የሚመጡት ደግሞ እኛ በዘመናችን ለወንጌል አገልግሎት ታማኞች ሆነን አደራውን እንድናስተላልፍላቸው ይጠብቃሉ፡፡ ለመሆኑ የወንጌልን አደራ ለመጠበቅ የሚያነሳሱን ነገሮች ምንድር ናቸው? ለወንጌል ብልህ ባለአደራዎች መሆን ያለብንስ ለምንድር ነው?

## 1/ እኛ ለዚህ ትውልድ ተጠያቂዎች ነን

ከእኛ በፊት በየትውልዳቸው ሁሉ የኖሩ የእምነት አባቶች ከእግዚአብሔር ዘንድ ለተሰጣቸው አደራና ለተጠሩበት የወንጌል ጥሪ ታማኞች ሆነው ኖረዋል፡፡ ወንጌል ዛሬ ለእኛ ሊደርስ የቻለውም ከእነርሱ ታማኝነት የተነሣ ነው፡፡ እነርሱ በሮጡበት መንገድ እኛም ልንሮጥ፣ እነርሱ የፈጸሙትን የተቀደሰ ተግባር እኛም በዘመናችን ልንፈጽም ይገባናል፡፡ የዕብራውያን መልዕክት ጸሐፊ በአሥራ አንደኛ ምዕራፉ ከአቤል ጀምሮ የኖሩትን የእምነት አባቶችን ኖህን፣ አብርሃምን፣ ይስሐቅን፣ ያዕቆብን፣ ዮሴፍን፣ ሙሴንና ሌሎችንም በመጥቀስ በየትውልዳቸው ለእግዚአብሔር ጥሪ እንዴት እንደሮጡና ሩጫቸውንም ለመፈጸም ሲሉ የከፈሉትን ዋጋ ሁሉ በዝርዝር ጽፏል፡፡

እነዚህ ሰዎች ለእግዚአብሔር ሀሳብ የመገዛትና እግዚአብሔርንም ለመታዘዝ ከነበራቸው ፈቃደኝነት የተነሣ በዘመናቸው መልካም ባለአደራዎች ሆነው የኖሩ፣ በእግዚአብሔርም ፊት ከተጠያቂነት የዳኑ የእምነት ምሳሌዎቻችን ናቸው፡፡

እኛም የእነርሱን ምሳሌነት በመከተል በትውልዳችን የተጣለብንን የወንጌል አደራ እንደሚገባ መወጣት እንዳለብን የዕብራውያን መልዕክት ጸሐፊው እንደሚከተለው በማለት ያሳስበናል፡፡ "እነዚህ ሁሉ ስለ እምነታቸው የተመሰገኑ ቢሆኑም፣ የተሰጣቸውን ተስፋ ገና አላገኙም፡፡ እግዚአብሔር ለእኛ የተሻለ ነገር አቅዶልናልና፤ ስለዚህ እነርሱ ከእኛ ጋር እንጂ ብቻቸውን ፍጹሞች መሆን አይችሉም፡፡ እንደ ደመና በዙሪያችን የከበቡን እነዚህ ሁሉ ምስክሮች (ከአቤል ጀምሮ እግዚአብሔርን በመታዘዝ የኖሩ የወንጌል ባለአደራዎች) አሉልን፤ እንግዲያውስ እኛም እንደ ሸክም የሆነብንን ነገር ሁሉ በእኛ ላይ የተጣበቀውን ኃጢአት አስወግደን፣ በፊታችንም ያለውን ሩጫ በትዕግሥት በመጽናት እንሩጥ፡፡" /ዕብ. 11፡39-12፡1፣ አዲሱ ትርጉም/፡፡

ከእኛ በፊት በታማኝነት የሮጡ ሁሉ ሩጫውን እንድንቀጥልና በመልካም ፍጻሜ እንድንፈጽም እንዲሁም ለሚቀጥለው ትውልድ እንድናስተላልፍ እኛን ይጠብቁናል፡፡ እነርሱ እስከ ሞት ድረስ ታማኞች በመሆን ለእኛ ያስተላለፉትን የወንጌልን አደራ እኛ በዘመናችን ልንጥለው፣ ችላ ልንለውና እንደ ራሳችን ሀሳብ ልንሮጥ አይገባም፡፡





የወንጌል ባለአደራ ማለት ለእግዚአብሔር በመታዘዝና እንደ እግዚአብሔር ሀሳብ በማገልገል፣ በቅድስና ለወንጌል እንደሚገባ በመኖር፣ እንዲሁም በኑሮና በቃል የወንጌል ምስክሮች በመሆን፤ ከእኛ በኋላ እግዚአብሔርን በፍርሃትና በቅድስና የሚያገለግል ትውልድ ማሳደግ ማለት ነው፡፡ ከእኛ በፊት የኖሩ የእምነት አባቶችና የወንጌል ባለአደራዎች ለእኛ ምሳሌዎች እንደሆኑልን ሁሉ እኛም ለሚቀጥለው ትውልድ የመታዘዝና የእምነት ምሳሌዎች ለመሆን መኖር ማለት ነው፡፡

በዚህ ዘመን ላለን አገልጋዮችና የቤተክርስቲያን መሪዎች ሌላ ዕብራውያን ምዕራፍ 11 ቢጻፍ ኖሮ ምን ዓይነት ምዕራፍ ይጻፍልን ይሆን? በማለት መልካምና ሕያው ታሪክ እንዲጻፍ መኖር ማለት ነው፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የምናገኛቸውን ዓይነት ሰዎች (የእነ ሙሴን፣ የእነ ጳውሎስን፣ ወዘተ) ምሳሌነት እንኳን መከተል ባንችል የዛሬ ሃያ፣ ሠላሳና አርባ ዓመታት ገደማ ለወንጌል ዋጋን እየከፈሉ በየጫካውና በየዱሩ፣ በየተራራውና ሜዳው በባዶ እግራቸው እየተጓዙ በታማኝነት ወንጌልን ያዳረሱትን የአባቶቻችንን ምሳሌነት ለመከተል እግዚአብሔር እንዲረዳን ልንጸልይ ይገባል፡፡ ለዚህ ትውልድ ተጠያቂዎች ነን፡፡

በትውልዳችን ወንጌልን ለማድረስ ብቻ ሳይሆን ለአገራችንም ድህነትም ሆነ ብልጽግና፣ ጦርነትም ሆነ ሰላም፣ ኋላ ቀርነትም ሆነ ዕድገት፣ ጥፋትም ሆነ ልማት፤ በተዘዋዋሪም ሆነ በቀጥታ የመጀመሪየ ተጠያቂዎቹ እኛ ክርስቲያኖች መሆናችንን መዘንጋት የለብንም፡፡ እኛ ለሕዝቡ ፈሪሃ እግዚአብሔርን፣ ቅድስናን፣ ተግቶ መሥራትን፣ የአገርን ዕድገትና ብልጽግና፣ ሰላምንና ፍቅርን የምናስተምርና እንደምናስተምረውም የምንኖር ከሆነ፤ በአገራችን ፈሪሃ እግዚአብሔር ይጎለብታል፣ ሥራንና አገርን የሚወድ ሕዝብ ይበዛል፣ ሰላምና ፍቅርም ይሰፍናል፡፡

ነገር ግን እኛ መልካም ምሳሌነት የሌለን ከሆነ ሕዝቡ መልካም ምሳሌነትን ከየት ይማራል? ለፍቅር፣ ለሰላም፣ ለአገር ዕድገትና ብልጽግና፣ ለልማትና ለእኩልነት መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስተምረውን ያህል የቱ መጽሐፍ ነው የሚያስተምረው? ታዲያ የትውልዱ ባለአደራዎች የሆንን እኛ ምንም ነገር እንደማያገባን ልንኖር እንዴት እንችላለን?

ላለንበት ትውልድ የመጀመሪያዎቹ ተጠያቂዎች እኛ ነንና የትውልድ ባለአደራነታችንን ለመወጣት ለወንጌል እንደሚገባ እንኑር፡፡ "እንግዲህ፣ ልጄ ሆይ፣ አንተ በክርስቶስ ኢየሱስ ባለው

ጸጋ በርታ፡፡ ብዙ ሰዎች የመሰከሩለትን ከእኔም የሰማኸውን ሌሎችን ደግሞ ሊያስተምሩ ለሚችሉ ለታመኑ ሰዎች አደራ ስጥ፡፡" /2ጢሞ. 2፡1-2/

ባለአደራነትን መወጣት ማለት ታማኝ የሆኑ ሰዎችን ማሳደግ ማለት ነው፡፡ ዘመናችንን በሙሉ ለእግዚአብሔርና ለተጣለብን ኃላፊነት ታማኞች ሆነን መገኘት ማለት ነው፡፡ ባለአደራነትን በትክክል መወጣት ማለት እውነትን ሳንሸቃቅጥ ለእውነት ኖረን ለእውነት መሞት ማለት ነው፡፡ ወገኔ ሆይ! የዚህ ትውልድ አደራ አለብህ፤ የወንጌል አደራ፣ ለቀጣዩ ትውልድ እውነትን የማስተላለፍ አደራ አለብህ፡፡ ባለህበት ሥፍራ ሁሉ አንተ በመኖርህ ምክንያት እውነት ያብባል? ወይስ ያንተ መኖርም ይሁን ያለመኖር እውነትን በማስፋፋት የሚያመጣው ለውጥ የለም?

## 2/ ኢየሱስ ክርስቶስ የሁሉ ጌታ፣ የሁሉ ፈጣሪና የሁሉም ባለቤት ነው

እኛን የፈጠረን፣ ሕይወት የሰጠን፣ ካለመኖር ወደ መኖር ያመጣን ክርስቶስ ነው፡፡ ሐዋሪያው ጳውሎስ ስለ ኢየሱስ ጌትነትና ሥልጣን ለቆላስያስ ክርስቲያኖች ሲጽፍ እንዲህ ይላቸዋል፡፡ "ክርስቶስ ለማይታየው እግዚአብሔር እውነተኛ ምሳሌ ነው፡፡ እርሱ የፍጥረት ሁሉ በኩር ነው፡፡ ምክንያቱም በሰማይና በምድር ያሉት፣ የሚታዩትና የማይታዩት፣ የሰማይ ኃይሎችና ገዢዎች፣ አለቆችና ባለሥልጣኖች ሁሉ የተፈጠሩት በእርሱ ነው፡፡ እርሱ ከሁሉ ነገር በፊት ነበረ ሁሉም ነገር ተያይዞ የቆመው በእርሱ ነው፡፡ እርሱ አካሉ የሆነችው የቤተክርስቲያን ራስ ነው፤ በሁሉ ነገር የመጀመሪያ እንዲሆን፣ ከሞት በመነሳትም ፊተኛና መጀመሪያ ነው፡፡" /ቆላ. 1፡15-18፡፡ አዲሱ ትርጉም/

በዚህ ክፍል ውስጥ ያለው ዋናው መልዕክት ኢየሱስ የሁሉ ፈጣሪ፣ የሁሉ ጌታ፣ ሁሉን የሚገዛ፣ ከሁሉ በፊት የነበረ፣ የሁሉ ራስ የሚል ነው፡፡ እኛ የተፈጠርነው በእግዚአብሔር ነው፣ የተፈጠርነውም ለእርሱ እንድንኖር ነው፡፡ ሁሉም የተፈጠሩት ለርሱ ነው፣ እኛም የእርሱ ነን፡፡ እኔ የእርሱ ነኝ ብዬ ሙሉ በሙሉ ራሴን ለርሱ ከሰጠሁ፣ እርሱ በሕይወቴ የፈለገውን ሁሉ ሊፈጽም ይችላል ማለት ነው፡፡ ይህ እውነት ከሆነ እኔም ለጌትነቱና ለሥልጣኑ መገዛት አለብኝ፡፡





ኢየሱስ ክርስቶስ የሁሉም ባለቤት ነው፡፡ በተለይም እርሱ ጌታዬ ነው ብለው ለተቀበሉት ሁሉ ፈቃዱን በሕይወታቸው ሊፈጽም ይፈልጋል፡፡ ምክንያቱም እርሱ በክቡር ደሙ ለራሱ ገዝቷቸዋልና፡፡ /1ጴጥ. 1፡18-19/ በዋጋ ተገዝታችኋልና የእኔ ናችሁ፣ ከእንግዲህ የራሳችሁ አይደላችሁም፣ እንደፈለጋችሁ መኖር አትችሉም ይለናል፡፡ /1ቆሮ. 6፡19-20/

ኢየሱስን እግዚአብሔር የሁሉ ጌታ አድርጎታል፣ ሥልጣንንም ሁሉ በሰማይና በምድር ሰጥቶታል፡፡ /ኤፌ. 1፡20-23/ እግዚአብሔር አብ ጌታ ያደረገውን ኢየሱስን እኛ ደግሞ ጌታ ልናደርገው ይገባናል፡፡ ጌታ ካደረግነው ደግሞ ለእርሱ ጌትነት እንገዛለን፡፡ ለሀሳቡና ለፈቃዱም ራሳችንን እንሰጣለን፣ አድርጉ የሚለንንም ነገር ለማድረግ በቆራጥነት እንነሳለን፡፡ እንግዲህ የተሰጠንን አደራ ለመጠበቅ፣ ለሚመጣውም ትውልድ ለማስተላለፍና በታማኝነት ለመፈጸም የሚያነሳሳን ኢየሱስ የሕይወቱ፣ የኑሮዬ፣ የትዳሬ፣ የገንዘቤ፣ የጊዜዬና የጉልበቴ ባለቤትና ጌታ ነው ብለን ሙሉ በሙሉ ስንቀበል ብቻ ነው፡፡

በሕይወትህ፣ በኑሮህ፣ በፈቃድህ፣ በፍላጎትህ፣ በጊዜህ፣ በጉልበትህና በገንዘብህ ኢየሱስ ጌታ ነውን? ለአንተ ባለህ ነገር ሁሉ ባለቤቱ ማነው? ባለቤቱ እግዚአብሔር ነው፣ ያለኝ ሁሉ የእርሱ ነው፣ የዚህ ቤት ራስ ክርስቶስ ነው እያልን ነገር ግን እንደምንናገረው ላንኖር እንችላለን፡፡ እግዚአብሔር ከእኛ የሚፈልገው መናገርን ሳይሆን እንደምንናገረው መኖርን ነው፡፡ እርሱ የሁሉ ባለቤት ነው ካልን አድርጉ የሚለንን ሁሉ ለማድረግና እርሱን ለማገልገል የሚያስከፍለንን ዋጋ ሁሉ ለመክፈል ፈቃደኞችና ደስተኞች እንሆናለን፡፡

## 3/ ብልህ ባለአደራዎች እንድንሆን እግዚአብሔር አዞናል

እኛ ያለን ነገር ሁሉ የተሰጠን ከእግዚአብሔር ነው፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ "ያልተቀበልኸውስ ምን አለህ? የተቀበልህ ከሆንህ ግን እንዳልተቀበልህ የምትመካ ስለምንድር ነው?" /1ቆሮ. 4፡7/ በማለት ሁሉን ነገር የተቀበልነው ከእግዚአብሔር እንደሆነ ያሳስበናል፡፡ ስለዚህም ይህ የእኔ ነው የምንለው ምንም ነገር የለም፡፡ ያለን ነገር ሁሉ የእግዚአብሔር ከሆነ ደግሞ ያለንን ለእግዚአብሔር ምርጫና ፈቃድ መልሰን ልንሰጥ ይገባል፡፡

የእግዚአብሔር ትዕዛዝ ልንፈጽመው የሚገባን ትዕዛዝ ነው፡፡ እያንዳንዱ ክርስቲያን አንድ ቀን በእግዚአብሔር ፊት ቆሞ ስለመታዘዙና ስለሠራው ሥራ ሁሉ ለእግዚአብሔር መልስ ይሰጣል፡፡ ጌታም ለሁሉም እንደየሥራው ዋጋ ይሰጣል፡፡ "የእያንዳንዱ ሥራ ይገለጣል፣ በእሳት ስለሚገለጥ ያ ቀን ያሳያልና፣ የእያንዳንዱም ሥራ እንዴት መሆኑን እሳቱ ይፈትነዋል፡፡ ማንም በክርስቶስ ላይ ያነጸው ሥራ ቢጸናለት ደመወዙን ይቀበላል፡፡" /1ቆሮ. 3፡10-14/

ሰዎች በሕይወታቸው ዘመን የከበረን ነገር ወይም እንደ ገለባ የሚቃጠል ከንቱን ነገር በመሥራት፣ ወይም ለእግዚአብሔር መንግሥትና ለእግዚአብሔር ፈቃድ ቅድሚያ ሰጥተው ጥበበኞች ሆነው፤ ወይም የሚፈርስን ህንፃ በመገንባት ሞኞች ሆነው ሊኖሩ ይችላሉ፡፡ እኛ ግን የተጠራነው ለዘላለም የሚኖርና የከበረን ነገር ለመሥራት ነው፡፡ ይህም በእሳት ተፈትኖ የሚያልፍና በእግዚአብሔር ፊት ጸንቶ የሚኖር የከበረ ነገር ነው፡፡ በእግዚአብሔር ፊት የከበረን ነገር ለመሥራት ብልህ የወንጌል ባለአደራ ሆነን መኖር ይጠበቅብናል፡፡ አንድ ክርስቲያን እንዴት ብልህ ባለአደራ ሊሆን ይችላል?

## ሀ. ሕይወቱን ለእግዚአብሔር ዘላለማዊ እቅዶች በማስገዛት

እግዚአብሔር ለእያንዳንዱ ሰው እቅድና ዓላማ አለው፡፡ እቅዱም መልካምና ዘላለማዊ ነው፡፡ ለኑሮአችን ከሚያስፈልጉን ከሌሎች ነገሮች ሁሉ የእግዚአብሔርን መንግሥት እንድናስቀድም የእግዚአብሔር እቅድ ነው፡፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ እግዚአብሔር መንግሥት ቀዳሚነት ሲናገር ሁለት አስገራሚ፣ ነገር ግን ተመሳሳይ ታሪኮችን ተናግሮ ነበር፡፡

የመጀመሪያው ታሪክ ዋጋዋ እጅግ የበዛ አንዲት ዕንቁ ለመግዛት ስለሚፈልግ ነጋዴ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ በእርሻ ውስጥ የተሸሸገን ሀብት ስለሚፈልግ ሰው ነው፡፡ ሁለቱም ሰዎች የሚፈልጉትን ነገር ባገኙ ጊዜ ያላቸውን ሁሉ ሸጠው ያን የሚፈልጉትን ነገር ገዙት፡፡ ካላቸው ከማንኛውም ነገር ጋር ሲያወዳድሩት ያ የሚፈልጉት ነገር በለጠባቸው፡፡ /ማቴ. 13፡44-46/፡፡





የእግዚአብሔር መንግሥት እጅግ የከበረና ከዕንቁ የሚበልጥ ነው፡፡ ከማንኛውም ነገር አብልጠን ልንፈልገውና ልንንከባከበው የሚገባን የእግዚአብሔር መንግሥት መስፋት፣ የእግዚአብሔር ዘላለማዊ እቅድ ነው፡፡ ለዚህ እቅድ ራሱን የሚያስገዛ፣ የእግዚአብሔር መንግስትና የእግዚአብሔር ፈቃድ ከሁሉ ይበልጥብኛል የሚል ክርስቲያን፣ እርሱ መልካም ባለአደራ ነው፣ እርሱ ሕይወቱን በጥበብ የሚመራ ሰው ነው፡፡

## ለ. በማንነቱና ባለው ነገር በመርካት

እያንዳንዱ ሰው ለእግዚአብሔር ልዩ ነው፡፡ እግዚአብሔር እስከዛሬ ድረስ በዓለም ላይ በመልክ በባህርይና በጠባይ ተመሳሳይ የሆኑ ሰዎችን ፈጥሮ አያውቅም፤ እያንዳንዱ ሰው ከሌላው የተለየ መልክ፣ ጠባይና ባህርይ አለው፡፡ እያንዳንዱን ሰው እግዚአብሔር ሲፈጥር ሌላውን ሰው እንዳይመስል ተጠንቅቆ ጊዜ ወስዶና አስቦ ነው፡፡ ስለዚህ እግዚአብሔር እያንዳንዱን ሰው ልዩ አድርጎ እንደሠራው ሁሉ ለእያንዳንዱም ሰው ያለው ዓላማም ልዩ ነው፡፡ ማለትም ለአንተ ያለው የእግዚአብሔር ዓላማ ልዩ ነው፣ ለእኔም ያለው የእግዚአብሔር ዓላማ ልዩ ነው፡፡

ከእግዚአብሔር የተቀበልነው ስጦታና ችሎታም የተለያየ ነው፡፡ ስለዚህ በእግዚአብሔር እንድንረካ ያስፈልጋል፡፡ ሌሎች ሰዎች ያላቸው ሀብትና ክብር እንዲኖረን በመመኘት መኖር ሳይሆን እኛ ራሳችን ባለን ነገር ልንረካና እግዚአብሔርን ልናከብር መቻላችን የተሰጠንን አደራ በታማኝነት ለመፈጸማችን አንዱ ማረጋገጫ ነው፡፡ ባለን ነገር ስንረካ በምስጋና ሕይወት መኖር እንችላለን፡፡ መርካት ካልቻልን ግን አሁን ከደረስንበት ቀጥሎ ያለውን ደረጃ ለመድረስ ስንንጠራራ፣ ከአሁኑ ክብር የሚቀጥለውን ክብር ለመድረስ ስንሮጥ ዘመናችን እንዲሁ ያልፋል፡፡

ስለዚህ ነው ሐዋሪያው ጳውሎስ ከእርሱ በኋላ ለሚቀጥለው ትውልድ የወንጌልን አደራ እየተረከበ ለነበረው ለተከታዩ ጢሞቴዎስ "ኑሮዬ ይበቃኛል ለሚለው ግን እግዚአብሔርን መምሰል እጅግ ማትረፊያ ነው፡፡" (1ጢሞ. 6፡6) በማለት ባለው ነገር እንዲረካ የጻፈለት፡፡ የትውልዱ የወንጌል ባለአደራነትህን እንደሚገባ መወጣት የምትችለው ባለህ ነገር ስትረካ ነው፡፡ ባለህ ነገር መርካት ካልቻልክ ግን የበረከት፣ የምስጋናና የመከናወን (የማደግ) ሕይወትህ ችግር ይኖረዋል፡፡ በማንነትህና ባለህ ነገር መርካት እግዚአብሔርን ለማመስገን ያስችልሃል፣ እየተንጠራራህ ከመውደቅም ያድንሃል፡፡

## ሐ. ለእግዚአብሔር ታማኝና ታዛዥ በመሆን /ማቴ. 25፥20-23/

መልካም ባለአደራ ለመሆን ታማኝነት እጅግ አስፈላጊ ነገር ነው፡፡ እግዚአብሔር የሚፈልግብን ብዙ እንድንሠራ ሳይሆን በሰጠን ነገርና ባስቀመጠን ሥፍራ ለእርሱ ታዛዦችና ታማኞች እንድንሆን ነው፡፡ እርሱ በእኛ ለማየት የሚፈልገው በአቅማችን መሥራታችንና በጥቂቱ ነገር ታማኞች መሆናችንን እንጂ የማንችለውን እንድንሠራ አይደለም፡፡ መልካም ባለአደራ ሆኖ ለመገኘት ለወንጌል ሥራ ብዙ ገንዘብ መስጠት ወይንም ደግሞ ያለውን ሥራ ለቆ የሙሉ ጊዜ የወንጌል አገልጋይ መሆን ላያስፈልግ ይችላል፤ የሚያስፈልገው ግን የትም ሥፍራ ሆነን ምንም ብንሠራ በልባችን ፈቃድና በደስታ የክርስቶስ ምስክር ለመሆን ታማኝ ሆኖ መገኘት ነው፡፡

## መ. ፍሬን በማፍራት /ማቴ. 13፥23/

በማቴ 13፥18-23 ጌታ ኢየሱስ በምሳሌ በገለጸው ታሪክ መሠረት ዘር ሲዘራ በአራት ዓይነት መሬት እንደወደቀ ተናግሯል፡፡ የመሬቱም ዓይነት የመንገድ ዳር፣ ጭንጫ፣ እሾሃማና መልካም መሬት ናቸው፡፡ እነዚህን የመሬት ዓይነት ጌታ ከሰዎች ሕይወት ጋር በማያያዝ ሲተረጉም፤ የማያስተውል፣ ሥር የሌለው፣ በዚህ ዓለም ሀሳብና የባለጠግነት ምኞት የሚታነቅና፣ መልካም ፍሬ የሚያፈራ ወይም የሚያስተውል በማለት ገልጾታል፡፡

የመጀመሪያዎቹ ሦስቱ ዓይነት ሰዎች ፍሬ ለማፍራት ያልበቁ ሲሆኑ ፍሬን ሊያፈራ የቻለው የሚያስተውለው፣ ለዚህ ዓለም ሀሳብ ምኞትና ባለጠግነት ግድ የሌለው፣ ሀሳቡን ለእግዚአብሔር ሀሳብ ያስገዛው ብቻ እንደሆነ እንመለከታለን፡፡ እንግዲህ አንተ ከአራቱ ዓይነት የቱ ነህ? የወንጌል ባለአደራ የወንጌልን ፍሬ ያፈራል፡፡ የወንጌልን ፍሬ ለማፍራት ደግሞ ለወንጌል እንደሚገባ መኖር ያስፈልጋል፡፡ ለወንጌል መኖር የሚቻለው ደግሞ ጊዜን፣ ጉልበትን፣ ገንዘብን እንደሚገባ ለወንጌል ሥራ መጠቀም ሲቻል ነው፡፡ እነዚህም ደግሞ በአደራነት ከእግዚአብሔር ዘንድ የተሰጡን ነገሮች ናቸው፡፡





## 4/ በአደራ የተሰጡን ሦስት ዋና ዋና ነገሮች

## ሀ/ የጊዜ ባለአደራነት

እግዚአብሔር ለእያንዳንዱ ሰው የተወሰነ ጊዜ ሰጥቶታል፡፡ ስለዚህም በተሰጠን ውስን ጊዜ መሥራት የሚገባንን እንድንሠራ ይጠበቅብናል፡፡ ከዘላለም ጋር ሲነጻጸር ዘመናችን በጣም አጭር ነው፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ "ሕይወታችሁ ምንድን ነው? ጥቂት ጊዜ ታይቶ ኋላ እንደሚጠፋ እንፋሎት ናችሁና" /ያዕ. 4፥13-17/ ካለ በኋላ በዚህች አጭር በሆነው ዘመናችን ዘላለማዊ ዋጋ ያለውን ሥራ መሥራት እንድንችል ፈቃዳችንን ለእግዚአብሔር ፈቃድ እንድናስገዛ ያሳስበናል፡፡ በዚህ አጭር በሆነው ዘመናችንም መልካም የሆነውን ነገር ማድረግ እንደሚገባን ያስጠነቅቀናል፡፡ መልካም የሆነውም ነገር ሁሉ የእግዚአብሔርን ሀሳብና ፈቃድ ማገልገል ነው፣ የእግዚአብሔርም ፈቃድ ሰው ሁሉ በክርስቶስ የሚገኘውን መዳን እንዲቀበልና ከእርሱም ጋራ ህብረት እንዲኖረው ነው፡፡

መዝሙረኛው ዳዊት ስለ ሰውና ስለ ጊዜ ሲናገር "ሰው ከንቱን ነገር ይመስላል፣ ዘመኑ እንደ ጥላ ያልፋል" ይላል፡ /መዝ. 144፥4/፡፡ እንፋሎት ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ ይበተናል፣ ጧት የታየውም ጥላ እኩለ ቀን ሲሆን አይታይም፤ የሰውም ሕይወት በምድር ላይ እንደዚሁ ነው፡፡ አለሁ፣ እኖራለሁ ሲል፤ ለነገም ሲያቅድ ሳያውቅ ይሄዳል፣ እቅዱም ሁሉ ይቀራል፡፡ ጊዜ እጅግ ውድ የሆነ ነገር ነው፣ በጥበብም ልንጠቀምበት ይገባል፡፡ እያንዳንዱን በዚህ ምድር የምንኖርበትን ቀን እግዚአብሔር የሰጠን በአደራ ነው፡፡ እኛም እያንዳንዱን ቀን ስንኖርበት በማስተዋል መሆን አለበት፡፡

የጊዜን ውድነትና እንዴትም መጠቀም እንዳለበት የተረዳ የእግዚአብሔር ሰው ሙሴ "ጥበበኞች ለመሆን እንድንችል ዘመናችን ምን ያህል አጭር እንደሆነ አስተምረን" ብሎ ጸለየ፡፡ /መዝ. 90፥12፣ አዲሱ ትርጉም/፡፡ ይህ በትልቅ ማስተዋል የተጸለየ ጸሎት ነው፡፡ ጊዜያችንን በትክክል መጠቀም መቻል ትልቅ ጥበብ ነው፡፡ እግዚአብሔርም በአደራ የተሰጠንን ጊዜያችንን በጥበብ መጠቀም እንድንችል "እንግዲህ እንዴት እንደምትኖሩ በጥንቃቄ አስተውሉ፤ እንደ ጥበበኞች እንጂ እንደ ሞኞች አትኑሩ፡፡ ይህ ዘመን ክፉ ስለሆነ በማናቸውም አጋጣሚ ሁሉ ተጠቀሙ፡፡" በማለት ያስጠነቅቀናል፡፡ /ኤፌ. 5፥15-16፣ አዲሱ ትርጉም/

ዘመኑን በጥበብና እንደ እግዚአብሔር ፈቃድና ሀሳብ ለተጠቀመው ሰንጉሥ ዳዊት በሕይወቱ መጨረሻ የተሰጠው ምስክርነት "በዘመኑ የእግዚአብሔርን ሀሳብ ያገለገለ" የሚል ነበር፡፡ /የሐዋ. 13፡36 ተመልከት፡፡/ ለእኛስ ምን ስም፣ ምንስ ምስክርነት ይሰጠን ይሆን? ጥበበኞች ወይስ ሞኞች? የእግዚአብሔርን ሀሳብ ያገለገለ ወይስ በራሱ ፈቃድና ፍላጎት የኖረ?

እግዚአብሔር የሰጠንን የራሳችንን ዘመን ዘላለማዊ ውጤት ላለው ለወንጌልና ለእግዚአብሔር ክብር እንድንጠቀምበት ያስፈልጋል፡፡ ዘመናችንን በጥበብ መጠቀም እንድንችል የመንፈስ ቅዱስ ኃይል እንደሚያስፈልገን የእግዚአብሔር ቃል ያሳስበናል፡፡ /ኤፌ.5፡15-18/፡፡ ስለዚህም የእግዚአብሔር ባሪያ ሙሴ የጸለየው ጸሎት የእኛም ጸሎት ሊሆን ይገባል፡፡ "ጥበበኞች ለመሆን እንድንችል እድሜያችን ምን ያህል አጭር እንደሆነ አስተምረን፡፡"

## ለ/ የችሎታ፣ የዕውቀትና የስጦታ ባለአደራነት

እግዚአብሔር ለእያንዳንዱ ሰው የተፈጥሮ ችሎታን ሰጥቷል፣ ይህም የተሰጠን በአደራ ነው፡፡ እውቀትን፣ መንፈሳዊ ስጦታንና ብዙ መልካም ነገሮችን ሁሉ ሰጥቶናል፡፡ እግዚአብሔር ሲሰጠን በዓላማና ለዓላማም ነው፡፡ የተሰጡን ስጦታዎች ሁሉ እግዚአብሔር ለራሱ ክብር ሊጠቀምበት እንጂ እኛ ለራሳችን ክብርና ዝና ወይም ምቾት እንድንጠቀምበት አይደለም፡፡ የተሰጠንን የተፈጥሮ ችሎታ፣ እውቀትና ማንኛውንም ስጦታ በጥበብ እንድንጠቀምበት ታዝናል፡፡ /ሉቃ. 19፡12-26/፡፡ ከእግዚአበሔር የተቀበልነውን ማንኛውንም ስጦታ ለእግዚአብሔር ክብር ስንጠቀም እኛም እንባረካለን፣ እግዚአብሔርም ይከብራል፡፡

## ሐ/ የገንዘብ ባለአደራነት

ገንዘብ ከእግዚአብሔር ዘንድ በአደራ የተሰጠን ስለሆነ፣ የገንዘባችን አጠቃቀም ሁኔታ እግዚአብሔርን የሚያስከብር መሆን አለበት፡፡ ገንዘብ የዚህ ዓለም አምላክ እንደሆነና ሰዎች ለእግዚአብሔር ክብር እንዳይኖሩ ሊያስታቸው የሚችል ትልቅ ኃይል እንዳለው መጽሐፍ ቅዱስ በመግለጽ እኛ ደግሞ እንዴት መኖር እንዳለብን ያስተምረናል፡፡ /ማቴ. 6፡24/ ሰው ገንዘብን ከወደደ በቀላሉ የገንዘብ ባሪያ ይሆናል፡፡ እግዚአብሔር ደግሞ ሰው ሁሉ መውደድ የሚገባው እግዚአብሔር አምላክን ብቻ እንዲሆን ይፈልጋል፡፡ "ጌታ አምላክህን በፍጹም ልብህ በፍጹም ነፍስህም





በፍጹም ሀሳብህም ውደድ፡፡ ታላቂቱና ፊተኛይቱ ትዕዛዝ ይህች ናት፡፡" /ማቴ. 22፡37-38/

ዛሬ ዓለምን ሁሉ ያስጨነቀው ወንጀል፣ ጦርነት፣ የነፍስ ግድያና በዓለም ላይ የሚታዩት አስጨናቂ ሁኔታዎች ሁሉ ምንጫቸው ምንድን ነው ቢባል ሰዎች ለገንዘብ ያላቸው ፍቅር ነው፡፡ ይህ የገንዘብ ፍቅር ያለው ጌታን በማያውቁ ሰዎች ዘንድ ብቻ ሳይሆን እግዚአብሔርን ያመልካሉ በሚባሉ ዘንድ እንኳን ሳይቀር የሚታይና ክርስቲያኖች በጥንቃቄ ሊመላለሱበት የሚገባ አሳሳቢ ጉዳይ ነው፡፡

ክርስቲያኖች ከገንዘብ ፍቅር ነጻ ሆነው በጥንቃቄ መመላለስ የሚችሉት መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ገንዘብ አጠቃቀምና አያያዝ የሚያስተምረውን በመታዘዝና በመኖር ብቻ ነው፡፡ በዚህ ጊዜ ዓላማዬ ስለ ገንዘብ አጠቃቀምና አያያዝ ለመጻፍና ለማስተማር ባይሆንም ገንዘብ እንደሌሎቹ ነገሮች ሁሉ ከእግዚአብሔር ዘንድ በአደራ የተሰጠን ስለሆነ ይህን አደራ እንዴት መጠበቅ እንዳለብን ለመገንዘብ ጥቂት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ደንቦችን እንመለከታለን፡፡

## *የመዝራት ደንብ /2ቆሮ. 9፡6/*

መጽሐፍ ቅዱስ ስለ መዝራትና ማጨድ ወይም ስለ መስጠትና ፍሬ ስለማፍራት ብዙ ይናገራል፡፡ ፍሬ የሚገኘው በተዘራው መጠን ነው፡፡ "በጥቂት የሚዘራ በጥቂት ደግሞ ያጭዳል፣ በበረከትም የሚዘራ በበረከት ደግሞ ያጭዳል" /2ቆሮ. 9፡6/ በማለት የምናገኘው የበረከት መጠን በምንዘራው የዘር መጠን እንደሚወሰን የእግዚአብሔር ቃል ያረጋግጥልናል፡፡

እኛ ክርስቲያኖች ገንዘብን እንድንዘራ ማለትም እንድንሰጥና ፍሬን እንድናፈራበት እንጂ እንድናከማች የእግዚአብሔር ፈቃድ አይደለም፡፡ ገንዘባችንን ወይም ንብረታችንን በሰማይ እንጂ በምድር እንድንሰበስብ እግዚአብሔር አልተናገረንም /ማቴ. 6፡19-24 ተመልከት፡፡/ እኛ የምናገኘው በምንሰጠው ልክ ነው፡፡ ጥቂት ከሰጠን ጥቂት በረከት፣ ብዙ ከሰጠን ደግሞ ብዙ በረከት እናገኛለን፡፡ ጌታችን ኢየሱስ ሲናገር "በምትሰፍሩበት መስፈሪያ ተመልሶ ይሰፈርላችኋል" /ሉቃ. 6፡38/ በማለት በምንዘራው ልክ እንደምናጭድ አስታውቆናል፡፡

## ከልብ የመስጠት ደንብ /ሉቃ. 21፥1-4/

እግዚአብሔር ከእኛ የሚፈልገው መስጠት ስላለብን እንድንሰጥ ሳይሆን ለእርሱ ካለን ፍቅር የተነሳ፣ እርሱ የእኛ ጌታና የሁሉ ባለቤት መሆኑን አውቀን ከልብ እንድንሰጥ ነው፡፡ በዚህ ክፍል የተጠቀሰችዋ ድሃዋ መበለት በጌታ የተመሰገነችው እንደ ሌሎቹ ብዙ ገንዘብ ስለሰጠች ሳይሆን በፍቅር ስለሰጠች ነው፡፡ ለጌታ ካላት ፍቅር የተነሳ ያላትን በመሉ ሰጠች፣ ይህን ያለኝን በሙሉ ሰጥቼ ነገ ምን እሆናለሁ አላለችም፡፡ ነገር ግን ሕይወቴ፣ ትዳሬ፣ ኑሮዬ እግዚአብሔር ነው፣ ከእርሱ ሌላ የለኝም ብላ ያላትን በሙሉ ሰጠች፡፡

ለእግዚአብሔር የምንሰጠው፣ ገንዘብ ሲተርፈን ብቻ አይደለም፡፡ ለእርሱ ፍቅር ካለን ለእኛ ሳይበቃንም እንሰጣለን፤ ምክንያቱም ጌታን የራሳችን ካደረግነው እርሱ የሁሉ ባለቤት ነውና ስለነገው ቢኖረን ባይኖረን የሚያስጨንቀን የለም፡፡ ለእግዚአብሔር ስንሰጥም ይህን ያህል ሰጠን እያልን እንዳንታበይ፣ ጌታ ኢየሱስ "ምጽዋትህ በስውር እንዲሆን ቀኝህ የምትሠራውን ግራህ አትወቅ፤ በስውር የሚያይ አባትህም በግልጥ ይከፍልሃል" በማለት ያስጠነቅቀናል፡፡ /ማቴ. 6፥3-4/

ለእግዚአብሔር ስንሰጥ ከፍቅር ልብ የመነጨ እንጂ ሰዎች እንዲያመሰግኑን ወይም እግዚአብሔር እንዲባርከን በመፈለግ መሆን የለበትም፡፡ የፍቅር ስጦታ የሕግና የደንብ ውሳኔን ሁሉ ያልፋል፡፡ አስራት ለመስጠት ደንቡ አንድ አስረኛውን የሚል ከሆነ ፍቅር ካለ ደግሞ አንድ አስረኛውን ሳይሆን እንደ መበለቷ ያለንን በሙሉ እንሰጣለን፡፡ እግዚአብሔር የሚመለከተው የምንሰጠውን የገንዘብ መጠን ሳይሆን ባለን የገንዘብ ልክ የምንሰጠውን መጠን ወይም ለጌታ ያለንን የፍቅር መጠን (ልክ) ነው፡፡

## በደስታ የመስጠት ደንብ /2ቆሮ. 9፥8-11/

እግዚአብሔር በግድ ሳይሆን በደስታና ዘላለማዊ በረከትን ለማግኘት እንድንሰጥ ይፈልጋል፡፡ እኛ በደስታ ስንሰጥ እግዚአብሔርም ይደሰታል፣ የመስጠታችንም ዋጋ ለዘላለም በፊቱ ይኖራል፡፡ ይህንንም መጽሐፍ ቅዱስ ሲያረጋግጥ፡- "እግዚአብሔር በደስታ የሚሰጠውን ይወዳልና እያንዳንዱ በልቡ እንዳሰበ ይስጥ፣ በኀዘን ወይም በግድ አይደለም፡፡ በተነ፣ ለምስኪኖች ሰጠ፣ ጽድቁ ለዘላለም ይኖራል" ይላል /2ቆሮ. 9፥7-9/፡፡ በደስታና በልብ





ፈቃድ ስንሰጥ የሥራችንን ውጤት በእግዚአብሔር ፊት እናገኛለን፡፡ በደስታ የማንሰጥ ከሆነ ግን መስጠታችን እግዚአብሔርን አያስደስተውም፡፡

የመጀመሪያዋ ምዕተ ዓመት ክርስቲያኖች በደስታ፣ በልግስናና በፍቅር ይሰጡ ነበር /2ቆሮ. 8፥1-5/፡፡ እነዚህም ክርስቲያኖች የሰጡበትን ምክንያት ስንመለከት በዘመናቸው የወንጌልን ተልዕኮ ለመፈጸም ነበር፡፡ ያላቸውን ለወንጌል ሥራ በታማኝነት በመስጠታቸውም በራሳቸው ትውልድ ከጌታ የተቀበሉትን አደራ ለመፈጸም ችለዋል፡፡ ወንጌልንም በዘመናቸው ለነበሩ ሰዎች ሁሉ ፈጽመው ሰብከዋል፡፡ እነዚህ ክርስቲያኖች የሰጡት፣ ገንዘብ ተርፎአቸው ሳይሆን ከድህነታቸው በልግስናና በፍቅር ነው፡፡ በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታ ሊሰጡ የቻሉት በመጀመሪያ ሕይወታቸውን ሙሉ በሙሉ ለእግዚአብሔር በመስጠታቸው ነበር፡፡

## ገንዘብን ለማስተዳደር አራት ቀዳሚ ደንቦች

### 1. ለቤተሰብ የሚገባውን መስጠት /1ጢሞ. 5፥8/

ከገንዘባችን የመጀመሪያውን ለቤተሰባችን እንክብካቤ ማዋል መልካም የገንዘብ ባለአደራነት ነው፡፡ ቤተሰባችን እየተጎዳ፣ የሚበላውንና የሚለብሰውን እያጣ፣ ገንዘብን ለሌሎች ጉዳዮች ማዋል መልካም የገንዘብ አስተዳደር አይደለም፡፡ "ለራሱ ዘመዶች፣ ይልቁንም ለቅርብ ቤተ ሰዎቹ የማያስብ ሃይማኖቱን የካደ ነው፤ እንዲያውም ከማያምን ሰው እንኳ የባሰ ክፉ ነው" /1ጢሞ. 5፥8፣ አዲስ ትርጉም/፡፡ ለራሳችንና ለቤተሰባችን የሚያስፈልገውን ነገር ማሟላት ብልህ ባለአደራነት ነው፡፡

### 2. ከገንዘብ ፍቅር ነፃ መሆን /1ጢሞ. 6፥7-10/

እውነተኛ ሀብት የሚገኘው ገንዘብን በመውደድ ሳይሆን ባለን ነገር እግዚአብሔርን በማመስገን፣ ለእርሱ ክብርና ፈቃድ ለመኖር ባለን መሰጠት እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ በግልጥ ይነግረናል፡፡ "ኑሮዬ ይበቃኛል ለሚለው ግን እግዚአብሔርን መምሰል እጅግ ማትረፊያ ነው፤ ወደ ዓለም ምንም እንኳ አላመጣንምና፣ አንዳችንም ልንወስድ አይቻለንም፤ ምግብና ልብስ ከኖረን ግን፣ እርሱ ይበቃናል፡፡ ዳሩ ግን ባለጠጎች ሊሆኑ የሚፈልጉ በጥፋትና በመፍረስ ሰዎችን በሚያሰጥምና በሚያሰንፍ በሚጎዳም በብዙ

ምኞትና በፈተና በወጥመድም ይወድቃሉ፡፡ ገንዘብን መውደድ የክፋት ሁሉ ሥር ነውና፡፡" /1ጢሞ. 6፡6-10/፡፡

ይህ ለእኛ ለክርስቲያኖች ትልቅ ማስጠንቀቂያ ነው፤ ወደዚህ ዓለም ስንወለድ ራቁታችንን ተወለድን፣ ከዚህ ዓለም ስንሄድም ራቁታችንን እንሄዳለን እንጂ አንዳች ነገር ይዘን አንሄድም፡፡ አንዳንድ ጊዜ ግን ይህንን እውነት ዘንግተን ብዙ ገንዘብ ለማከማቸት እንሮጣለን፣ መሥራት የሚገባንን ቁም ነገር ሳንሠራ ዘመናችን ያልፋል፡፡ ዳዊት ከገንዘብ ፍቅር ነፃ ሆኖ፣ እግዚአብሔርን በታማኝነት ማገልገል ማለት ምን ማለት እንደሆነ ጠንቅቆ ያወቀ ሰው ነበር፡፡

ስለዚህም ለራሱ እንደዚህ ብሎ ጸለየ፡- "እግዚአብሔር ሆይ! ከእንግዲህ ወዲህ የምኖረው ምን ያህል ጊዜ ነው? የምሞተውስ መቼ ነው? የሕይወቴ ፍጻሜ መቼ እንደሆነ አስታውቀኝ፡፡" (መዝ. 39፡4፣ አዲሱ ትርጉም) በትክክል አሜን የሚያስብል ጸሎት ነው፡፡ ዳዊት ይህንን እውነት የሆነ ጸሎት ከጸለየ በኋላ የምድር ላይ ሕይወቱ ምን ያህል አጭር እንደሆነና ከገንዘብ ፍቅርና ከስግብግብነት ነፃ መሆን ምንኛ አስፈላጊ መሆኑን በትክክል ተገነዘበ፡፡ ስለዚህም ወደሚከተለው መደምደሚያ ሀሳብ ሊደርስ ቻለ፡፡ "ዕድሜዬን እንዴት አጭር አደረግኸው፣ የሕይወቴ ዘመን በአንተ ፊት እንደሌለ የሚቆጠር ነው፤ እንዲያውም ሕያው የሆነ ሰው ሁሉ ከነፋስ ሽውታ የተሻለ አይደለም፤ ከጥላም የተሻለ አይደለም፤ በከንቱ ይደክማል፤ ሀብትን ያከማቻል፤ ነገር ግን ማን እንደሚጠቀምበት አያውቅም፡፡" /መዝ. 39 5-6፣ አዲሱ ትርጉም/፡፡

የዳዊትን ዓይነት ጸሎት መጸለይና እርሱ የተረዳውን ዓይነት እውነት መረዳት በዘመናችን ሁሉ እግዚአብሔርን ብቻ ተስፋ አድርገን እንድንኖር ያስችለናል (መዝ. 39፡7)፡፡ ከገንዘብ ፍቅር ነጻ ወጥተን፣ ገንዘባችንን ለወንጌል ሥራ እንድንጠቀም እግዚአብሔር ይርዳን፡፡

## 3. *በልግስና መስጠት /1ጢሞ. 5፡17-19/*

ሐዋሪያው ጳውሎስ ክርስቲያኖች ገንዘብን እንዴት ማስተዳደር እንዳለባቸው ለአገልጋዩ ለጢሞቴዎስ ሲጽፍለት፡- "በአሁኑ ዘመን ባለጠጎች የሆኑት የትዕቢትን ነገር እንዳያስቡ፣ ደስም እንዲለን ሁሉን አትርፎ በሚሰጠን በሕያው እግዚአብሔር እንጂ በሚያልፍ





ባለጠግነት ተስፋ እንዳያደርጉ እዘዛቸው ... ለሚመጣው ዘመን ለራሳቸው መልካም መሠረት የሚሆንላቸውን መዝገብ እየሰበሰቡ ... ሊረዱና ሊያካፍሉም የተዘጋጁ እንዲሆኑ ምከራቸው" /1ጢሞ. 6፡17-19/ በማለት አስጠንቅቆታል፡፡

ከዚህ መልዕክት ማስተዋል የሚገባን ብዙ ነገሮች አሉ፡፡ ከእነዚህም መካከል ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸው፡፡ 1ኛ/ ሰዎች ተስፋ ማድረግ ያለባቸው በሀብታቸውና በብልጥግናቸው ሳይሆን በእግዚአብሔር ብቻ ነው፡፡ ምክንያቱም ባለጠግነትና ሀብት የሚያልፉ ነገሮች ሲሆኑ እግዚአብሔር ግን ሀብትንም ብልጥግናንም ለሚፈልገው አትረፍርፎ መስጠት ይችላል፡፡ 2ኛ/ ሰዎች ንብረታቸውን ማስቀመጥ ያለባቸው ዋስትና በሌለበት በዚህ ምድር ላይ ሳይሆን ለዘላለም በሚኖረው በእግዚአብሔር መንግሥት መሆን አለበት፡፡ 3ኛ/ ንብረታቸውን በእግዚአብሔር መንግሥት ለማከማቸት የሚቻለው ሌሎችን በመርዳት፣ ለሌላቸው በማካፈልና የወንጌልን ተልዕኮ ለመፈጸም ገንዘብን በመስጠት ነው፡፡

## 4. *ገንዘባችንን ለማንና ለምን እንደምንሰጥ ማወቅ*

ባለአደራዎች እንደመሆናችን መጠን ገንዘብን በታማኝነትና ለመልካም ውጤት ለሚጠቀሙ መስጠት ያስፈልጋል፡፡ ገንዘባችንን መስጠት ያለብን 1ኛ/ ለአጥቢያ ቤተክርስቲያን /1ቆሮ. 9፡1-14፣ ሚል 3፡10/፣ 2ኛ/ የወንጌልን ተልዕኮ ለመፈጸምና ሰዎችን ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ለማምጣት ለሚንቀሳቀሱ አገልግሎቶች /ፊል. 4፡14-16/፣ 3ኛ/ ገንዘብ ለሚያስፈልጋቸው አማኝ ወገኖች /ገላ. 6፡10/፣ 4ኛ/ ችግር ላለባቸው ድሆችና ላላመኑ ሰዎች /ገላ. 2፡10/፡፡

በእጃችን የሚገኘው ገንዘብ የራሳችን ሳይሆን የእግዚአብሔር ነው፡፡ ስለዚህም እንደ እግዚአብሔር ሀሳብ ማስተዳደር ይጠበቅብናል፡፡ ገንዘባችንን ከመስጠታችን በፊት ይህ ገንዘብ ለእግዚአብሔር ክብር ብዙ ውጤት የሚያስገኘው የት ነው ብለን መጠየቅ ይኖርብናል፡፡ ከዚያም ገንዘቡ ብዙ ፍሬ ለሚያፈራበት አገልግሎት ማዋል በገንዘብ የተሰጠንን ባለአደራነት በአግባቡ መፈጸም ነው፡፡

## ተግባራዊ እርምጃዎች

የሚቀጥለውን ምዕራፍ ማንበብ ከመጀመርህ በፊት አንዳንድ ጥያቄዎችን መጠየቅና ለጥያቄዎቹ ተገቢ ምላሽ በመስጠት አስፈላጊ ውሳኔዎችን አድርግ፡፡ እነዚህን ውሳኔዎች ስታደርግም መንፈስ ቅዱስ እንዲረዳህ ጸልይ፡፡ ውሳኔህንም በማስተወሻ ደብተርህ ላይ ጻፈው፡፡ ከውሳኔህም በኋላ ለተግባራዊነቱ ጸልይ፣ አስፈላጊውንም እርምጃ ውሰድ፡፡

ክርስቲያን እንደ መሆኔ መጠን ለዚህ ትውልድ የመጀመሪያው ተጠያቂ እኔ ነኝ፣ የትውልዱም የወንጌል ባለአደራ ነኝ፤ ነገር ግን ባለአደራነቴን ለመወጣት እየኖርኩ ያለሁት እንዴት ነው? ያለኝ ነገር ሁሉ የእግዚአብሔር ነውን? አሁን ባለኝ ነገር ሁሉ ባለቤቱ ማነው? እግዚአብሔር የጊዜዬ፣ የችሎታዬና የገንዘቤ ጌታ ነውን? ባለፈው ሳምንት ጊዜዬን እንዴት ተጠቀምኩ? በጊዜዬ ምን ምን ቁም ነገሮችን ሠራሁበት? ገንዘቤ ለእግዚአብሔር ክብርና ለነፍሳት ደህንነት እየዋለ ነው? ገንዘቤን ለእግዚአብሔር ሥራ መስጠት ያልቻልኩበት ምክንያቱ ምንድን ነው? ባለኝ ነገር እንዳልረካ ችግሬ ምንድር ነው? ከዛሬ በኋላ እንዴት መኖር አለብኝ? ውሳኔ ማድረግ ከዛሬ በኋላ በምትኖረው ኑሮህና ሕይወትህ ለውጥ እንድታይ ይረዳሃል፡፡

በራሳችን ኃይል የወንጌል ባለአደራነታችንን በብቃት ለመወጣት አንችልም፡፡ ነገር ግን ይህን የሚያስችለን የእግዚአብሔር መንፈስ ነው፡፡ የእግዚአብሔር መንፈስ ደግሞ የሚሠራው እኛ ስንጸልይ ነው፡፡ በጸሎት ውስጥ ታላቅ የሆነ ኃይል አለ፡፡ በጸሎት በሚገኝ ጉልበት ወንጌልን የማዳረስ ተልዕኮ እንዴት መፈጸም እንደምንችል በሚቀጥለው ምዕራፍ እንመለከታለን፡፡



# ምዕራፍ ዘጠኝ

## ወንጌልና ጸሎት

ወንጌል እግዚአብሔር በዘላለማዊ ፍቅሩና ዕቅዱ የሰውን ልጆች ከኃጢአት ባርነት ነፃ ለማውጣት የተናገረበት ታላቅ መልዕክት ነው፡፡ ይህ የእግዚአብሔር መለኮታዊ መልዕክት ወደ ሰዎች እንዲደርስ፣ ሰዎችም መልዕክቱን ሰምተው በሕይወታቸው ለውጥን እንዲያገኙና ወደ እግዚአብሔር መንግሥት እንዲገቡ የእኛ ጸሎት እጅግ አስፈላጊ ነው፡፡

ጸሎት ማለት በኃይሉ እንዲሠራ እግዚአብሔርን ማነሳሳት ማለት ነው፡፡ እግዚአብሔር ሁሉን ነገር በራሱ ማከናወን የሚችል አምላክ ቢሆንም እኛ እንድንጸልይ ይፈልጋል፡፡ ምክንያቱም እኛ ስንጸልይ እምነታችንና በእርሱ ላይ ያለን መደገፍ ይበልጥ እንዲያድግ ይፈልጋልና፡፡ የጥያቄ ሁሉ መልስ የሚገኘው በጸሎት ሲሆን፣ ጸሎት ደግሞ ዓለምን የመለወጥ ታላቅ ኃይል አለው፡፡

በእግዚአብሔር ሕዝብ ታሪክ ውስጥ የጸሎት ሰዎች እግዚአብሔርን አነጋግረውታል፣ ከእርሱም አስደናቂ መልሶችን አግኝተዋል፡፡ በሰዶምና በገሞራ ሀገሮች የእግዚአብሔር ቁጣ እንዳይወርድ አብርሃም ጸለየ፣ እግዚአብሔርም የአብርሃምን ጸሎት ሰማ፤ ነገር ግን በአብርሃምና በእግዚአብሔር ስምምነት መሠረት በሰዶምና ገሞራ እግዚአብሔርን የሚፈሩ አስር ሰዎች ስለታጡ የእግዚአብሔር ቁጣ በዚያች ምድር ወረደ፡፡ /ዘፍ. 18፡22-23/

ጠላቶቹን እስኪበቀል ድረስ ፀሐይ በገባዖን እንድትቆም ኢያሱ ጸለየ፣ ፀሐይም ቆመች፡፡ /ኢያሱ. 10፡12-14/ በጸሎት ታሪክ ተለውጧል፣ አዲስ ታሪክም ተሰርቷል፤ በጸሎት የፈረሰው ታድሷል፣ የተማረከውም ነፃ ወጥቷል፡፡ በጸሎት ባህር ተከፍቷል፣ ባዶ ሸለቆም በውሃ ተሞልቷል፡፡ በጸሎት የሰዎች እስራት ተበጣጥሰዋል፣ የወህኒ መዝጊያዎች በራሳቸው ተከፍተዋል፣ የጠላትም ኃይል ድል ተመቷል፡፡ በጸሎት የሰማይና የምድር ፈጣሪ የሆነው እግዚአብሔር ለሰዎች ተገልጧል፣ ታላቅ ሥራውንም ሠርቷል፡፡

ከዚህ በፊት ታላላቅ ነገሮችን የሠራው እግዚአብሔር ዛሬም ይሠራል፣ ምክንያቱም እርሱ ዛሬም ሕያው አምላክ ነው፡፡ እርሱ ዛሬም የሚሠራና የሚያስደንቅ አምላክ ነው፡፡

ለወንጌል የተዘጉ በሮች ሁሉ እኛ ተግተን ስንጸልይ ይከፈታሉ፣ ሰዎች ወደ እግዚአብሔር መንግስት ይመጣሉ፣ የዲያቢሎስም ዕቅድና ሥራ ሁሉ ይፈርሳል፡፡ እኛ ስንጸልይ እግዚአብሔር ይሠራል፡፡ መንፈስ ቅዱስ ከአእምሮአችን በላይ የሆነውን አስደናቂውን የእግዚአብሔርን ሥራ ሲሠራ ለማየት ከፈለግን መጸለይ አለብን፡፡ እኛ እንድንጸልይ እግዚአብሔር ይፈልጋል፣ መፈለግም ብቻ ሳይሆን እንድንጸልይ ያዝናል፡፡ በዚህች አነስተኛ ምዕራፍ ስለ ጸሎት ሁሉንም ነገር ለማየት ባይቻልም እግዚአብሔር ለእኛ ጸሎት ያለውን ሥፍራና በጸሎት የሚገኙትንም አስደናቂ ውጤቶች ጥቂቶቹን ብቻ እንመለከታለን፡፡

## 1/ እኛ ስንጸልይ እግዚአብሔር ይሠራል /ኤር. 33፡3/

ከእግዚአብሔር የሆነውን እውነተኛ ቃል ለሕዝቡ በመናገሩ ምክንያት ብዙ ተቃውሞ እየደረሰበትና በብዙ ሰቆቃ ውስጥ እያለፈ ለነበረ ለነቢዩ ኤርምያስ እግዚአብሔር እንደዚህ አለው፡፡ "ወደ እኔ ጩኸ እኔም እመልስልሃለሁ፣ አንተም የማታውቀውን ታላቅና ኃይለኛ ነገር አሳይሃለሁ፡፡" /ኤር. 33፡3/፡፡ ይህ ኤርምያስን ወደ እኔ ጩኸ ብሎ የተናገረው እግዚአብሔር፣ እርሱ ማን ነው ብለን ብንጠይቅ፣ እርሱ "ምድርን የፈጠራትና ያዘጋጃት ተደላድላም እንድትኖር ያደረጋት እግዚአብሔር፣ ስሙ እግዚአብሔር የሆነ ጌታ" ነው፡፡ /ኤር. 33፡2፣ አዲሱ ትርጉም/

ይህ በሁሉ ላይ ሥልጣን ያለው እግዚአብሔር ኤርምያስን እኔ የሁሉ ጌታ ነኝ፣ ምድርና ሞላዋ የእኔ ናቸው፣ እኔ ታላቅ ነገርን ማድረግ እችላለሁ፣ ስሜ እግዚአብሔር ነው ወደ እኔ ጩኸ፣ ወደ እኔ ጸልይ ይለዋል፡፡ ነቢዩ ወደ እግዚአብሔር በሚጮኽበት ጊዜ እግዚአብሔር ምን እንደሚሠራም በግልጽ ይናገራል፡፡ እኛ ከጸለይን በዘመናችን ታላቅ የሆነውን የእግዚአብሔርን ሥራ እናያለን፡፡ እግዚአብሔርም ወደ እርሱ ለሚጸልዩ ሰዎች ጸሎታችውን ሊመልስ ታማኝ አምላክ ነው፡፡





## ሀ. እግዚአብሔር ይመልሳል

"ወደ እኔ ጩኸ እኔም እመልስልሃለሁ፡፡" ያለው እግዚአብሔር እንደፈቃዱ የተደረገውን ጸሎት የሚመልስ አምላክ ነው፡፡ እግዚአብሔር ጣዖት አይደለም፣ ነገር ግን የሚሰማና የሚመልስ ሕያው አምላክ ነው፡፡ /1ነገ. 18፡16-40/ እኛ ክርስቲያኖች ወደ እግዚአብሔር የእምነት ጩኸት በምንጮኽበት ጊዜ እግዚአብሔር ይመልሳል፡፡

በኢያሱ ዘመን በእስራኤላውያን ጩኸት የኢያሪኮን ግንብ ያፈረሰው አምላክ (ኢያሱ 6) ዛሬም በወንጌል የሚወረሱትን ስፍራዎች እንዲያወርሰን ከጮኽን ያወርሰናል፡፡ የጠላትን የዲያብሎስን ቅጥር ዛሬም ያፈርሳል፡፡ በጌዴዎንና በሦስት መቶ ሠራዊት ጩኸት ምድያማውያንን የመታና ጠላቶቻቸውን ያሳደደ አምላክ (መሳ. 7) ዛሬም ሕዝቡ ሲጮኽ የወንጌልን ጠላት ያሳድዳል፡፡ እግዚአብሔር በዘመናችን መመለስ ያለበት ብዙ ነገር አለ፣ ስለዚህ በስሙ የተጠራን ሕዝቡ መጮኽ ያስፈልገናል፡፡ በአገራችን ወንጌል ያልደረሳቸውና በመንፈሳዊ ጨለማ ውስጥ ያሉ ብሔረሰቦች ብዙ ናቸው፡፡ በጣዖት አምልኮና በሰይጣን ቀንበር ውስጥ ያሉ በሚሊየን የሚቆጠሩ ሰዎች ናቸው፡፡ የወንጌል በር እንዲከፈት፣ እነዚህም ሰዎች ከጨለማ ወጥተው በክርስቶስ ወደሚገኘው ብርሃን እንዲመጡ፣ ከሰይጣን እስራት እንዲፈቱ እኛ መጸለይ ይገባናል፡፡ በጸሎት ታሪክ ይሠራል፣ እግዚአብሔርም አዲስን ነገር ያደርጋል፡፡

እ.ኤ.አ. በ1963 ዓ.ም. በአሜሪካን ግዛቶች በሚገኙ ትምህርት ቤቶች ጸሎት እንዳይደረግና ማንኛውም ዓይነት የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት እንዳይሰጥ በመንግሥት ተደነገገ፡፡ ይህ ድንጋጌ በአሜሪካ እግዚአብሔርን የማይፈራና በስነ ምግባሩ የላሸቀ ትውልድ እንዲነሳ ምክንያት ሊሆን እንደሚችል የተገነዘቡ ክርስቲያኖች ድንጋጌው ከወጣ ከአምስት ዓመት በኋላ እግዚአብሔር ድንጋጌውን እንድሽር ታላቅ የእምነት ጩኸት ወደ እግዚአብሔር መጮኽ ጀመሩ፡፡ በሁሉም የአሜሪካን ግዛቶች ታላቅ የጸሎት እንቅስቃሴ ተጀመረ፡፡

ወደ እኔ ጩኸ እኔም እመልስልሃለሁ ያለው እግዚአብሔር ጩኸታቸውን ሰማ፣ መለሰላቸውም፡፡ የጸሎት እንቅስቃሴው በተጀመረ በጥቂት ዓመታት ውስጥ በጠቅላላው 125 ሚሊየን

የአሜሪካ ሕዝብ የምሥራቹን ወንጌል ሰምቶ 85 ሚሊዮን ሕዝብ ወደ ቤተክርስቲያን ተጨመረ፡፡

## ለ. እግዚአብሔር አዲስን ነገር ያደርጋል

"አንተም የማታውቀውን ታላቅና ኃይለኛ ነገርን አሳይሃለሁ፡፡" ጸሎት እጅግ ታላላቅ ነገሮችን የሚያደርግ የክርስቲያን መሣሪያ ነው፡፡ ለወንጌል አገልግሎት በየቀኑ ጥቂት ደቂቃዎችን እንኳን ሰጥተን በታማኝነት ብንጸልይ እኛ ከምናስበው በላይ ታላቅ ነገርን እግዚአብሔር ያደርጋል፡፡ እኛ ጮኸን እግዚአብሔር ውጤቱን ለሌሎች ብቻ አያሳይም፡፡ ለሚጮኸው ለራሱ ታላቅን ነገር ያሳየዋል፡፡

ከጌታ ዘንድ ታላቅ ነገር እንዲደረግልን ከፈለግን፣ በዘመናችን እግዚአብሔር አዲስ ነገርን ሲሠራ ለማየት ፍላጎታችን ከሆነ፣ መንገዱ አንድ ብቻ ነው፤ ወደ እግዚአብሔር መጮኸ፡፡ በአገራችን ብዙ የምንጸልይባቸው ጉዳዮች አሉ፡፡ ከፊታችን የቆሙ ብዙ የወንጌል እንቅፋቶች አሉ፡፡ እነዚህ እንቅፋቶች በቤተክርስቲያንም ውስጥ ከቤተክርስቲያንም ውጪ ያሉ ናቸው፡፡ እነዚህም እንቅፋቶች መወገድ የሚችሉት በእምነት በሚጮኹት ሰዎች ታላቅ ጩኸት ነው፡፡ ገና በወንጌል ያልተወረሰ ብዙ ምድር አለ፡፡ ይህም ያልተወረሰ ምድር የሚወረሰው በጸሎት የሰይጣንን መንግሥት ተግቶ በመዋጋትና ወደ እግዚአብሔር በመጮኸ ነው፡፡

ይህ ጽሁፍ በሚዘጋጅበት ጊዜ በአገራችን ውስጥ ገና የምሥራቹ ወንጌል ያልደረሳቸው ከ40 በላይ የሆኑ ብሔር ብሔረሰቦች እንደሚገኙ ይገመታል፡፡ በአንዳንድ የአገሪቱ ክልሎች ከሚኖሩ ሰዎች መካከል በክርስቶስ አዳኝነት ያመኑት ከአስር ሺህ ሰው መካከል ሁለት ወይም ሦስት ሰው ብቻ ነው፡፡

ኢየሱስ ለሰው ልጆች ብርሃንን ለመስጠት እርሱ የዓለምን ጨለማ ለብሶ በመስቀል ላይ የሞተ ቢሆንም /ማቴ. 27፡45/ አሁንም ብዙዎች በሰይጣን ግዛት በጨለማው መንግሥት ውስጥ ይገኛሉ፡፡ ለእነዚህ ሰዎች የእግዚአብሔር መንግሥት ብርሃን እንዲበራላቸው፣ የአምላካችንም መንግሥት በምድራችን እንዲሰፋ ብርቱ ጸሎት ልናደርግ ይገባል፡፡ በዘመናችን የእግዚአብሔርን ክብር ለማየት ከፈለግን በትጋት መጸለይ ይጠበቅብናል፡፡ ከልብ የሚወጣ ጩኸት በእግዚአብሔር ዘንድ ታላቅ ዋጋ አለው፡፡





## 2/ እኛ ስንጸልይ እግዚአብሔር ይሰጣል /መዝ. 2፡8-9/

እግዚአብሔር ለእኛ እንደፈቃዱና እንደሀሳቡ ሁሉን ነገር ለመስጠት ይፈልጋል፡፡ እርሱ ደግሞ ሁሉ ያለው፣ የሁሉ ባለቤት ነው፡፡ እርሱ የሚሰጠው ግን እኛ ስንጠይቅ ነው፡፡ "ለምኑ ይሰጣችሁማል፣ ፈልጉ ታገኙማላችሁ፣ መዝጊያን አንኳኩ ይከፈትላችሁማል፡፡ የሚለምነው ሁሉ ይቀበላልና፣ የሚፈልገውም ያገኛል መዝጊያውንም ለሚያንኳኳ ይከፈትለታል፡፡" /ማቴ. 7፡7-8/ ከእግዚአብሔር ዘንድ ለማግኘት መንገዱ እርሱን መለመንና እርሱን መፈለግ ነው፡፡ የተዘጋውም በር እንዲከፈት መንገዱ ማንኳኳት ነው፡፡ እጅግ የሚገርመው ነገር ቢኖር የሚለምን ሁሉ ይሰጠዋል፣ የሚፈልግም ሁሉ ያገኛል፡፡

ምንድን ነው ከእግዚአብሔር የምትለምነው? በሕይወትህ ዘመን ለማየት የምትፈልገውስ ነገር ምንድን ነው? የእግዚአብሔር የክብሩ ወንጌል ምድራችንን ሲያጥለቀልቅና ሰው ሁሉ ለኢየሱስ ጌትነት ሲንበረከክ ማየት ትፈልጋለህ? ይህን ከፈለግህ ጸልይ፣ እግዚአብሔርን ለምን፡፡ እግዚአብሔር ሁልጊዜ ለመስጠት ዝግጁ ነው፣ ምክንያቱም እርሱ የሚሰጥ አምላክ ነውና፡፡ ነገር ግን እግዚአብሔር ሊሰጥ እኛ እርሱን እንድንጠይቅ ይፈልጋል፡፡ "ለምነኝ አሕዛብን ለርስትህ የምድርንም ዳርቻ ለግዛትህ እሰጥሃለሁ፡፡" /መዝ. 2፡8/ የምሥራቹን ወንጌል ይዘን እስከ ምድር ዳርቻ ድረስ እንድንሄድ ትዕዛዝ ተቀብለናል፡፡ እግዚአብሔር የምድርን ዳርቻዎችና አሕዛብን ሁሉ የሚሰጠን እኛ እንዲሰጠን ስንጠይቀው ነው፡፡ እግዚአብሔር ታላቅ ነገር እንዲሠራ እኛ ታላቅ ነገርን እንጠይቅ፡፡

## 3/ እኛ ስንጸልይ የእግዚአብሔር በረከት ይመጣል

እግዚአብሔር የበረከትና የመልካም ነገር ሁሉ ምንጭ ነው፡፡ ይህንንም በረከቱንና መልካምነቱን በምድር ላይ ለማፍሰስ ይፈልጋል፡፡ እግዚአብሔር ፈቃዱን የሚያደርገው በምድር ላይ ፈቃዱን የሚፈልጉና የሚያደርጉ ሰዎችን ሲያገኝ ነው፡፡ ክርስቲያን ሁሉ በሰማይ ያለውን የእግዚአብሔርን ፈቃድ በምድር እንዲፈልግና

እንዲያደርግ ተጠርቷል፡፡ ንጉሡ ሰለሞን የእግዚአብሔርን ፈቃድ በመፈለግ ላይ ሳለ ነበር እግዚአብሔር ፈቃዱን የገለጠለት፡፡

ፈቃዱንም የገለጠለት እንደዚህ በማለት ነበር፡- "በስሜ የተጠሩት ሕዝቤ ሰውነታቸውን አዋርደው ቢጸልዩ፣ ፊቴንም ቢፈልጉ፣ ከክፉ መንገዳቸውም ቢመለሱ፣ በሰማይ ሆኜ እሰማለሁ፣ ኃጢአታቸውንም ይቅር እላለሁ፣ ምድራቸውንም እፈውሳለሁ፡፡" /2ዜና. 7፡14/፡፡ በእግዚአብሔር ስም የተጠሩ ክርስቲያኖች ወደ እግዚአብሔር በሚጸልዩበት ጊዜ፣ በፊቱም ከክፉ መንገዳቸው ተመልሰው ንስሃ በሚገቡበት ጊዜ እግዚአብሔር ብዙ ነገሮችን እንደሚያደርግ ቃል ገብቷል፡፡

## ሀ. እግዚአብሔር በሰማይ ሆኖ ይሰማል

ክርስቲያኖች በእግዚአብሔር ፊት በትህትና፣ ራሳቸውን ዝቅ በማድረግና ክብርን ሁሉ ለእግዚአብሔር በመስጠት በሚጸልዩበት ጊዜ እርሱ ጸሎታቸውን ይሰማል፡፡ እግዚአብሔር እርሱን ለሚፈልጉት ሁሉ ለመገኘትና ሀሳቡንም ለመግለጥ ተስፋ ሰጥቶአል፡፡ ስንጠራው የሚሰማን አምላክ በሰማይ ስላለ እጅግ ደስ ሊለንና ልንመካበት ይገባል፡፡ እኛ የምናመልከው አምላክ በዓል አይደለም፣ አስታሮትም አይደለም፣ ነገር ግን እርሱ የኤልያስ አምላክ ነው፣ የእስራኤል አምላክ ነው፡፡ የእኛ አምላክ የሚሰማ፣ የሚመልስ አምላክ ነው /1ነገሥ. 18፡20-39፡፡/

## ለ. እግዚአብሔር ኃጢአትን ይቅር ይላል

ኃጢአት ማለት ሰው ወደ እግዚአብሔር እንዳይደርስ፣ የእግዚአብሔርንም አስደናቂ ፍቅርና ዓላማ እንዳያውቅ የሚጋርድና ሰውን ከአምላኩ የሚለይ ክፉ ደዌ ነው፡፡ ይህ ደዌ ከእግዚአብሔር ይቅርታ በስተቀር በሌላ በምንም መድኃኒት አይፈወስም፡፡ የእግዚአብሔርም ይቅርታ የተገለጠበት መልዕክት ወንጌል ነው፡፡ እግዚአብሔር የሰዎችን ኃጢአት ይቅር የሚለው ወንጌል ሲሰበክ ነው፣ ወንጌል የሚሰበከው ደግሞ በጸሎትና የእግዚአብሔርን ፊት በመፈለግ ነው፡፡

የጸሎት እንቅስቃሴና የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ከሌለ በስተቀር ወንጌልን በመስበክ ብቻ ብዙ ሰዎችን ወደ ደህንነት ማምጣት እጅግ አስቸጋሪ መሆኑን ከቤተክርስቲያን ታሪክ እንማራለን፡፡ ብርቱ ጸሎትና የመንፈስ ቅዱስ ኃይል፣ መለኮታዊ ሥራን በማይሠራባቸው በአንዳንድ አገሮችና አካባቢዎች በአንዲት ቤተክርስቲያን ውስጥ





በአምሳ ዓመት የወንጌል ስብከት ወደ ደህንነት የሚመጡ ሰዎች ቁጥር ከአምሳ እንደማይበልጥ ይገመታል፡፡ ይህም ማለት የእግዚአብሔር ኃይል በማይሠራበት በአንድ ዓመት ስብከት በወንጌል የዳነው አንድ ሰው ብቻ ነው፡፡ ስለዚህ ሰዎች የኃጢአት ይቅርታን እንዲቀበሉ የክርስቲያኖች ጸሎት እጅግ አስፈላጊ ነው፡፡

## ሐ. እግዚአብሔር ምድራችንን ይፈውሳል

ከሚኖሩባት ሰዎች ኃጢአት የተነሣ ምድር የተረገመች ትሆናለች፡፡ ሰዎች እግዚአብሔርን ሲፈሩትና ሲታዘዙት ከእግዚአብሔር በረከትን እንደሚወርሱ፣ እግዚአብሔርን መስማት እምቢ ሲሉና ሲያምፁ ግን መርገም እንደሚያገኛቸው መጽሐፍ ቅዱስ ያስተምረናል፡፡ /ዘዳ. 28፡1-29/፡፡ ዓመጽ በምድራችን ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ መምጣቱ ለማንም ግልጽ ነው፡፡ አስራ ሰባት ዓመታት ሙሉ በኮምዩኒዝም ርዕዮተ ዓለምና በፍልስፍናቸው አለንጋ በመገረፋችን ቀድሞ የነበረን የህዝባችን ክብር፣ የሞራል ውበትና ግርማ ዛሬ እየራቀን መሄዱ ለማንም መንገር የሚያሻው ጉዳይ አይደለም፡፡

በጎዳና ላይ ከሚጫወቱት ህፃናት አፍ እንኳን ሳይቀር አስጸያፊ ስድብ መስማቱ የተለመደ ነገር እየሆነ መጥቷል፡፡ ልጆች ለወላጆች የሚታዘዙበት ቤት በቁጥር እየቀነሰ ይገኛል፡፡ ልጆች አዋቂዎችን ማክበር የትናንት ትዝታ እየሆነብን ሄዷል፡፡ የጎረቤት ልጅ ሲያጠፋ ቀጥቶ መመለስና መምከር የአባቶቻችን ዘመን ታሪክ ሆኗል፡፡ በገዛ ልጄ የፈለገውን ቢያደርግ ምን አገባህ በሚለው ተተክቷል፡፡ ጠባያችን፣ ባህሪያችን፣ ሞራላችን ከጊዜ ወደ ጊዜ እየከሰመ፣ ውሸት በእውነት ቦታ ተተክቷል፡፡ ዝርፊያ፣ ንጥቂያ፣ ሌብነትና ወንጀል ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መጥቷል፡፡ ጉቦኝነት አድልዎና ዘረኝነት በየመሥሪያ ቤቱ የለም ለማለት ያስቸግራል፡፡ ስንቱ ባለሥልጣን ነው በጽድቅና በፍትህ የሚፈርደው? የሕዝብንና የእግዚአብሔርን አደራ ተሸክመው እያሉ ነገር ግን የሕዝብን ገንዘብ በማጭበርበር ለራሳቸው ጥቅም የሚያውሉና ንብረት ያለአግባብ የሚያባክኑ ኃላፊዎች ጉዳይ በየዕለቱ በዜና እንሰማ የለምን?

ምድራችን በተፈጥሮ የበለጸገች አገር ሆና ሳለ እስከ መቼስ ድረስ ህዝቧን ዳቦ መመገብ ያቅታት? በእርሻ ፍሬ፣ በቤትና በውጭስ በረከት የማናየው እስከ መቼ ነው? መቀበሉን አቁመን ለሌሎች መስጠት የምንጀምረውስ መቼ ነው? ህዝባችን እግዚአብሔርን መፍራት የሚጀምረው፣ አንዱ ሌላውንስ የሚያከብረው መቼ ነው? ሰዎች የኃጢአታቸውን ይቅርታ

እስካላገኙ ድረስ ምድር አትፈወስም፡፡ ምድርን መፈወስ የሚችለው የፈጠራት እግዚአብሔር ብቻ ነው፡፡

እግዚአብሔር ምድርን እንዲፈውሳት ክርስቲያኖች ራሳቸውን አዋርደው በትህትና ወደ እግዚአብሔር መጮህና ለምድራቸውም በፊቱ ማልቀስ አለባቸው፡፡ ምድር የምትፈወሰው በወንጌል ነው፡፡ ሰዎች ለወንጌል ሲታዘዙ ዓመፅ ይጠፋል፣ ዓመፅ ሲጠፋም በሰዎች ሕይወት ሰላም ይሰፍናል፣ ሰላም ሲሰፍን ደግሞ ምድር ከእግርማን ታርፋለች፡፡ እኛ በስሙ የተጠራን ህዝቦቹ ወደ አምላካችን መጮኽ ካልጀመርንና የእግዚአብሔርን በረከት ለምድራችን ካልፈለግን ዓመጽና ጉስቁልና ከምድራችን ከቶም ሊወገድ አይችልም፡፡

አገርን ለሚያስተዳድሩ መሪዎቻችን እግዚአብሔር የመሪነት ጥበብንና ማስተዋልን እንዲሰጣቸው፣ እግዚአብሔርንም በመፍራት ህዝብንና አገርን እንዲያስተዳድሩ፣ ለአገር ሰላምና በረከት የመጸለይ ኃላፊነት አለብን፡፡ ይህንን የማናደርግ ከሆነ ባለአደራነታችንን ዘንግተናል ማለት ነው፡፡

የእግዚአብሔር ክብር በምድራችን ከዳር እስከ ዳር እንዲያበራ ትፈልጋለህ? መርገም፣ ጉስቁልናና ረሃብ ከምድራችን እንዲጠፋ ትመኛለህን? የወንጌሉን የምሥራች ሰዎች ሁሉ በምድራችን እንዲሰሙ ትፈልጋለህን? ለዚህ ሁሉ ጥያቄ መልስ ያለው እግዚአብሔር ብቻ ነው፡፡ እግዚአብሔር መልስ የሚሰጠው ደግሞ እኛ ወደእርሱ ስንጮኽና እርሱን በጸሎት ስንጠይቅ ነው፡፡

## 4/ ጸሎታችን ታላቅ ውጤት አለው

መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ነቢዩ ኤልያስና ስለ ጸሎቱ "ኤልያስ እንደ እኛ የሆነ ሰው ነበረ ዝናብም እንዳይዘንብ አጥብቆ ጸለየ፣ በምድርም ላይ ሦስት ዓመት ከስድስት ወር አልዘነበም፤ ሁለተኛም ጸለየ፣ ሰማዩም ዝናብን ሰጠ ምድሪቱም ፍሬዋን አበቀለች" በማለት ይናገራል፡፡ /ያዕ. 5፡17-18/፡፡ ይህም ማለት እኛም አስፈላጊ ከሆነ ኤልያስ የጸለየውን ዓይነት ጸሎት፣ ከዚያም በላይ የሆነ ጸሎት፣ የመጸለይ መብትና ሥልጣን አለን፡፡

በእግዚአብሔር የታመኑ ሰዎች ታላላቅ ጸሎቶችን ጸልየው ከእግዚአብሔር ዘንድ አስደናቂ መልሶችን አግኝተዋል፡፡ ዝናብ እንዲቆም ጸልየዋል፣ ዝናብም ቆሟል፤ እንዲዘንብ ጸልየዋል፣ ሰማይም ተከፍቶ ዝናብን ሰጥቷል፡፡ /ያዕ. 5፡17-18/፡፡





የዮርዳኖስ ውኃ ሙላት ከሁለት እንዲከፈል ወደ እግዚአብሔር ጮኸዋል፣ ዮርዳኖስም ተከፍሏል /ኢያሱ 3/፤ እሳት እንድትጠፋ ጸልየዋል፣ እሳትም ጠፍታለች /ዘኁል. 11፡1-2/፡፡

የእግዚአብሔር ኃይል ወደ መካከላቸው እንዲመጣ ጸልየዋል፣ ኃይልንም ተቀብለዋል፤ የፈለጉትን እግዚአብሔርን አግኝተዋል፡፡ እግዚአብሔር ጠላቶቻቸውን እንዲበቀልላቸው ጸልየዋል፣ ጠላቶቻውንም አሸንፈው ወንጌልን እስከ ምድር ዳርቻ ድረስ ሰብከዋል /የሐዋ. 4፡24-31፣ የሐዋ. 16፡5/፡፡ እኛም እንደነርሱ ሰዎች ነን፣ በእነርሱ ዘመን የሠራው አምላክ ዛሬም የሚሠራ ሕያው አምላክ ነው፡፡ ዛሬም ስሙ፣ ኃይሉ፣ ክንዱና ብርታቱ አልተለወጠም፡፡

የአምላካችን ስሙ ዛሬም እግዚአብሔር ነው፣ ተዋጊ ነው፣ ብርቱና ኃያል ነው፣ በሰልፍ ኃያል ነው፣ ኤልሻዳይ ነው፣ ባለስልጣን ነው፡፡ የእነርሱ አምላክ የእኛም አምላክ ነው፡፡ እኛ ሌላ አምላክ የለንም፣ የማይሠራና ሕያው ያልሆነ አምላክ አናውቅም፡፡ እኔ በበኩሌ የማይሠራ፣ ተኝቶ እንደሆነ ቀስቅሱት የሚባል አምላክ አላውቅም፡፡ እኔ የማውቀው አምላክ የአብርሃም፣ የይስሐቅና የያዕቆብ አምላክ፤ የነበረ፣ ያለና የሚመጣ፤ ጨለማውን የሚያበራ፣ ባህርን የሚከፍል፣ ከዓለት ውሃን የሚያፈልቅ፣ በምድረ በዳ እንጀራን የሚሰጥ፣ የኢያሪኮን ግንብ የሚያፈርስ፣ የሞተውን የሚያስነሣ ሕያው አምላክ ነው፡፡ አንተ የምታውቀው አምላክ የቱ ነው?

አንተ የምታውቀው አምላክ የኤልያስ አምላክ ከሆነ፣ ዮርዳኖስን የከፈለው አምላክ ከሆነ፤ ኤልያስ ሰው እንደሆነ አንተም እንደእርሱ ሰው ነህና ወደዚህ አምላክ መጮኽ ትችላለህ፡፡ ከአምላክህ ዘንድ ታላቅን ነገር መጠየቅ ትችላለህ፡፡ "የጻድቅ ሰው ጸሎት በሥራዋ እጅግ ኃይል ታደርጋለች" /ያዕ. 5፡16/፡፡ ምናልባት እኔ ጻድቅ ሰው አይደለሁም ልትል ትችላለህ፡፡ በእግዚአብሔር ልጅ በኢየሱስ አምነህ ከሆነ ጽድቅህ ክርስቶስ ነው፡፡ ከእግዚአብሔር ዘንድ ምን ትጠይቃለህ? "ለራስህ ታላቅን ነገር ትፈልጋለህን? ... አትፈልገው፡፡" /ኤር. 45፡5/ "ነገር ግን አስቀድማችሁ የእግዚአብሔርን መንግስትና ጽድቁንም ፈልጉ፣ ይህም ሁሉ ይጨመርላችኋል፡፡" /ማቴ. 6፡33/

ከእግዚአብሔር ዘንድ ታላቅን ነገር ጠይቅ፡፡ ነገር ግን ለራስህ፣ ለቤትህና ለኑሮህ ሳይሆን ታላቁ የምሥራቹ ወንጌል ለህዝብ ሁሉ እንዲነገር፣ የእግዚአብሔር ክብር በምድር ሁሉ ላይ በተለይም

በሀገራችን እንዲሞላ፣ ከእግዚአብሔር ዘንድ የመጽናናትና የመታደስ ዘመን እንዲመጣ፣ ሰማያት ተከፍተው የእግዚአብሔር በረከት በምድራችን እንዲፈስ፣ ምድር እግዚአብሔርን በማወቅ እንድትሞላ፣ ሰዎች እግዚአብሔርን እንዲፈሩትና እንዲያከብሩት፣ ብዙ ሰዎች ከኃጢአት እስራት ወጥተው ወደ እግዚአብሔር መንግስት እንዲገቡ፣ ታላቅ ነገርን ፈልግ፡፡ ታላቅ ጸሎትን ጸልይ፣ ታላቅ የሆነው እግዚአብሔርም ታላቅ የሆነውን መልስ በዘመንህ ያሳይሃል፡፡

## 5/ ሰማያዊ ሥራ የሚሠራው በሰማያዊ ኃይል ነው

በመጀመሪያው ምዕተ ዓመት የኖሩት ክርስቲያኖች ወንጌልን እስከ ምድር ዳርቻ ድረስ ለማድረስና በዘመናቸውም የእግዚአብሔርን ሀሳብ ለማገልገል የቻሉት በራሳቸው ኃይልና እውቀት ሳይሆን በመለኮታዊ ኃይል ስለተሞሉ ነበር፡፡ በኢየሩሳሌም የነበሩት የሃይማኖት መሪዎች እንኳ "መጽሐፍን የማያውቁና ያልተማሩ ሰዎች ሆነው እንዴት በግልጥ ወንጌልን ሊናገሩ ቻሉ?" /ሐዋ. 4፡13/ በማለት እስኪደነቁ ድረስ ሐዋሪያት በታላቅ ኃይልና ጸጋ የእግዚአብሔርን ቃል ይናገሩ ነበር፡፡ ይህም የሆነው ሕይወታቸው በመንፈስ ቅዱስ የተሞላና የጸሎት ሰዎች ስለሆኑ ነበር፡፡ ለጸሎት እጅግ ከፍተኛ ስፍራ ነበራቸው፡፡

ሐዋሪያት እግዚአብሔርን ቃሉን በግልጥነት መናገር እንዲችሉ መንፈስ ቅዱስን አብዝቶ እንዲሰጣቸውና ወደ ጠላቶቻቸው ዛቻ እንዲመለከት ጸለዩ፡፡ ጸሎታቸውም ውጤት ነበረው፡፡ እግዚአብሔር ወደ እነርሱ መጣ፣ የመንፈስ ቅዱስንም ኃይል በሁሉም ላይ ሞላባቸው፤ ከዚህም የተነሣ ለታላቅ ለታናሽ፣ ለተማረ ላልተማረ፣ በቅርብም በሩቅም ላለ ሁሉ ወንጌልን በድንቅና በታአምራት ሊናገሩና የተሰጣቸውን አደራ ሊፈጽሙ ችለዋል፡፡ /ሐዋ. 4፡23-32/

የእግዚአብሔርን ሥራ መሥራት የምንችለው በእግዚአብሔር መንፈስ ነው፡፡ "ለዘሩባቤል የተባለው የእግዚአብሔር ቃል ይህ ነው፣ በመንፈሴ እንጂ በኃይልና በብርታት አይደለም ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር፡፡ ታላቅ ተራራ ሆይ አንተ ምንድን ነህ? በዘሩባቤል ፊት ደልዳላ ሜዳ ትሆናለህ፡፡" /ዘካ. 4፡6-7/፡፡ በምድራችን ወንጌልን ለማድረስ ብዙ ስብሰባዎች አያስፈልጉንም፣ ብዙም ኰሚቴ የሚያስፈልገን አይመስለኝም፤ ነገር ግን የሚያስፈልገን የእግዚአብሔር መንፈስ ነው፡፡ ስብሰባም፣ ስልጠናም፣





ኰሚቴም፣ ዕቅድም ጠቃሚ ነው፡፡ ነገር ግን ተራራውን ደልዳላ ሜዳ የሚያደርገው የእግዚአብሔር መንፈስ ሥራውን እንዲሠራ ካልፈቀድን ሁሉም ከንቱ ነው፡፡ ለስብሰባ አንድ መቶ ሰዓት ከመስጠት ለመንፈስ ቅዱስ አንድ ሰዓት መስጠት የሚሻል እንደሆነ አምናለሁ፡፡

የእግዚአብሔርን መንግሥት ሥራ በተማሩ ሰዎች ብዛት፣ ብዙ ገንዘብ ወይም ጥሩ እቅድ ስለተዘረጋ መሥራት አይቻልም፡፡ ነገር ግን የእግዚአብሔር መንግሥት ሥራ የሚሠራው በእግዚአብሔር በራሱ ነው፡፡ ስለዚህ ከማንኛውም ነገር በላይ ለወንጌል ሥራ እጅግ የሚያስፈልገው እግዚአብሔርን ማግኘት ነው፡፡ እግዚአብሔር ደግሞ የሚገኘው በጸሎት ነው፡፡ በዚህ ዘመን ለእኛ የሚያስፈልገን በኰሚቴ ብዛት የሚዘንበው ዝናብ ሳይሆን በእግዚአብሔር እጅ "ከባህር የምትወጣ የሰው እጅ የምታህል ታናሽ ደመና" ነች /1ነገ. 18፡ 41-46 ተመልከት፡፡/

የእግዚአብሔር መንፈስ ሲሠራ የሰው እጅ የምታህል ደመና ከባህር ከወጣች ለምድር ሁሉ ትበቃለች፣ የደረቀውን ምድር ሁሉ ታረሰርሳለች፣ ጠማማውን ሁሉ ታቃናለች፡፡ ክብር ለእግዚአብሔር ይሁን፡፡ በኤልያስ ላይ የነበረች እጅ ብቻ በእኛ ላይ ትሁንልን፣ እግዚአብሔር ታናሽ የክብር ደመናውን ከባህሩ ይላክልን፣ ይህች ደመና ከወጣች ታላቅ ነጕድጓድና ዝናብ ይመጣልና፡፡

ኢቫን ሮበርት ይባላል፡፡ ከጓደኞቹ ጋር የድንጋይ ከሰል በሚያመርትበት ጫካ ውስጥ ነበር ይህችን የሰው እጅ የምታህል ታናሽ ደመና ያየው፡፡ በ1904 ዓ.ም. ከእንግሊዝ ግዛቶች አንዷ በሆነችው በዌልስ ግዛት፡፡ ሮበርት የተማረ ሰው አልነበረም፣ የመናገርም ችሎታ አልነበረውም፡፡ በሕይወቱ ያያቸውና ያነበባቸው መጽሐፍት ቢኖሩ አንድ መጽሐፍ ብቻ ነው፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ፡፡ ብዙ የማንበብም ችሎታ አልነበረውም፡፡ ጸጉሩ በከሰል ጭስ የቆሸሸ፣ የሚለብሰው ጥላሸት የለበሰ ካኪ ቱታ፡፡ የሮበርት ውስጡ ግን በእግዚአብሔር የፍቅር እሳት ይነድ ነበር፡፡

ይህ ሰው በዘመኑ ታላቅ ነገርን እግዚአብሔር እንዲያሳየው ይጮህ ነበር፡፡ ከዕለት ወደ ዕለት በልቡ ይቃጠል የነበረው የወንጌል እሳት አብዝቶ ወደ አምላኩ እንዲጮህ አደረገው፡፡ የነበረበትን ሁኔታ፣ አለመማሩንና የሥራውን ዓይነት ሁሉ ወደ ኋላ ትቶ ኤልሻዳይ የሆነውን አምላክ ለትልቅ ነገር ለመነው፡፡

እግዚአብሔር እኔን ደካማውን ሰው ሊለውጥና ለክብሩ ሊጠቀም ይችላል ብሎ አመነ፡፡ ከከሰል አምራችነትና ከጫካ ሕይወት ወደ ነፍስ አዳኝነትና ወደ አደባባይ ሕይወት ያመጣኛል ብሎ አመነ፡፡ በባዶ ሜዳ ሰሚ በሌለበት ወንጌልን ይሰብክ ነበር፡፡ በውስጡ የሚነድደው እሳት ምናልባት ይበርድ እንደሆን በማለት ከአንዲት ባለርስት ሴት በጥገኝነት ባገኛት ትንሽ የመኖሪያ ክፍሉ ውስጥ እንኳ ሳይቀር ሰው በሌለበት ወንጌልን በታላቅ ድምጽ ይሰብክ ነበር፡፡ ያንን ስብከቱን ሰው ባይሰማውም ስፍራ የማይወስነው እግዚአብሔር ግን ይሰማው ነበር፡፡ ሰሚ በሌለበት ቢጮኽ እንኳን በልቡ ያለው ግለት አልቀነሰም፡፡ ይልቅ ያስጠጋችው ባለርስት በጩኽትህ እረፍት ነሳኸኝ ብላ በሃያ አምስት ዓመቱ ከመሬቷ አባረረችው፡፡

ወደ እኔ ጩኽ እኔም እመልስልሃለሁ ያለው እግዚአብሔር ከዕለታት አንድ ቀን ወደ ኢቫን ሮበርት መጣ፡፡ ጸሎትህን ሰምቻለሁ፣ ታላቅንም ነገር አሳይሃለሁ፤ በአንተ ሕይወት የምጀምረው የወንጌል እሳት በጥቂት ጊዜ በመላ ኢንግላንድ ከዚያም አውሮፖ አፍሪካና ኤሽያ ሀገሮች እንዲነድ አደርጋለሁ አለው፡፡ ሃሌሉያ! እግዚአብሔር ጸሎትን የሚሰማና የሰውንም ፊት አይቶ የማያዳላ አምላክ ነው፡፡

ይህ ራዕይ ሮበርትን የበለጠ ልቡን ያነደው ነበር፡፡ በሰው ፊት ቆሞ የሚሰብክበትን አጋጣሚ ሁሉ ቢሞክር አልተሳካለትም፡፡ የቤተክርስቲያኑንም ወንጌላዊ "እባክህ አንድ ጊዜ እንድሰብክ እድል ስጠኝ" ብሎ ደጋግሞ ቢለምነውም ወንጌላዊው ናቀው እንጂ እድል አልሰጠውም፡፡

ከብዙ ጊዜ ጸሎትና ጥያቄ በኋላም ወንጌላዊው "እሺ መልካም ያንተን ስብከት እንኳ ሊሰማ የሚፈልግ ሰው ይኖራል ብዬ አላስብም፣ ለማንኛውም ረቡዕ ማታ በሚኖረው የቤተክርስቲያን ፕሮግራም ላይ ፕሮግራሙ ሁሉ ከተጠናቀቀ በኋላ ስብከትህን ለመስማት ወደ ኋላ መቅረት የሚፈልጉ ሰዎች ካሉ እጠይቅልሃለሁ" አለው፡፡

የረቡዕ ማታ ፕሮግራም አበቃ፡፡ ወንጌላዊውም ጉባዔውን አሰናበተ፣ የሮበርትን ስብከት ለመስማት የሚፈልጉ ሰዎች ካሉ ወደ ኋላ እንዲቀሩ ማስታወቂያ ተናገረ፡፡ ይህ ከሰል አምራች ምን ሊሰብክ ነው እያሉ በማሾፍ ብዙዎች የቤተክርስቲያኒቷን አዳራሽ ለቀቁ፡፡ ነገር ግን እንዲሁ ምን ይሰብክ ይሆን በማለት ለትችት





የቋመጡ አስራ ስድስት ሰዎችና ወንጌላዊው ጭምር በአዳራሹ ውስጥ ቀሩ፡፡

ሮበርት ተነሳ፣ ብዙ የመናገር ችሎታ የለውም፤ ነገር ግን ስለ ኃጢአት፣ ስለ ቅድስና፣ ስለ መንፈስ ቅዱስና ወንጌልን ለሌሎች ስለመመስከር አስፈላጊነት በጣም ቀላል የሆነ ስብከት አቀረበ፡፡ ሮበርት ሲሰብክ የእግዚአብሔር የክብር ደመና ቤቱን ሞላው፡፡ ወንጌላዊውና አስራ ስድስቱ ሰዎች የእግዚአብሔርን ክብር ሊቋቋሙት አልቻሉም፡፡ በእግዚአብሔርም ፊት መቆም አቃታቸው፡፡ ምህረትንና ይቅርታን ከእግዚአብሔር በመለመን ከዓይናቸው እንባ እንደ ጎርፍ ይፈስ ነበር፡፡ ወንጌላዊውም ሮበርትን እኔ ልሰብክ አይገባኝም፣ ከነገ ጀምሮ አንተ ብቻ ስበክ አለው፡፡

በጥቂት ቀናት ውስጥ የወንጌሉ እሳት አቅራቢያ ወዳሉት ቤተክርስቲያናት ሁሉ ተዛመተ፡፡ በሚቀጥሉት ሰላሣ ቀናት ውስጥ ብቻ ሠላሣ ሰባት ሺ ሰዎች ክርስቶስን መድኃኒታቸውና ጌታቸው አድርገው ተቀበሉት፡፡ በሚቀጥሉት አምስት ወራት አንድ መቶ ሺ ሰዎች ወደ እግዚአብሔር መንግስት ተጨመሩ፡፡

የተለያዩ ጋዜጦች ስለ ኢቫን ሮበርት አስደናቂ አገልግሎት መመስከር ጀመሩ፡፡ አንድ ጋዜጣ "ኢቫን ሮበርት በማንም የማይታወቅ ሰው ነበር፣ ነገር ግን ትዕዛዝ ከሰማይ ሲመጣለት ታዛዥ ሆነ፡፡ ለዚህም ታላቅ ሥራ በቀጥታ የጠራው መንፈስ ቅዱስ እንደሆነ በድፍረት ይናገራል፡፡ በአንድ ጊዜ ያለ ምንም ጥያቄ ሰው ሁሉ ተቀበለው፣ ሮበርት በሄደበት ስፍራ ሁሉ የሰዎች ልብ በእግዚአብሔር እሳት በመቀጣጠል ላይ ይገኛል" በማለት ጽፏል፡፡ ሌላኛው ጋዜጣ ደግሞ "በዌልስ ግዛት ታላቅ እሳት እየተቀጣጠለ ነው፡፡ ይህም እሳት የሰዎች ሁሉ ሕይወት የሚቀልጥበትንና የሚለወጥበትን ታላቅ አብዮት አስነስቷል" በማለት ነበር የዘገበው፡፡

ኮሌጆችና ትምህርት ቤቶች ሁሉ ተዘግተው ተማሪዎች በየጎዳናዎቹና በየአደባባዮቹ ለእግዚአብሔር የምስጋና መዝሙር እየዘመሩ የጸሎት ስብሰባዎች ወደሚደረጉባቸው ሜዳዎች በሰልፍ ይተምሙ ነበር፡፡ ልጆች በየሰፈራቸው እየተገናኙ እነርሱም አዋቂዎች የሚያደርጉትን ያደርጉ ነበር፡፡ ታላላቅ የጸሎት ቡድኖች ተቋቋሙ፡፡ በአንድ ከተማ የተቋቋመው የጸሎት ቡድን እጅግ የሚያስደንቅ ነበር፡፡ ወንጌልን ለመመስከር ወደ ሰዎች ቤት መሄድ አያስፈልገንም በማለት ወደ ሰፊ ሜዳ ሄደው በመሰብሰብ ሌሊቱን በሙሉ ወደ እግዚአብሔር ሲጸልዩ ያድሩ ነበር፡፡

በጸሎታቸውም ሰፍራ ሌሊት በሜዳ ሆነው ክርስቶስን ሳያውቁ በየቤታቸው በአልጋ ላይ በተኙ ሰዎች ላይ የእግዚአብሔር እሳት እንዲወርድባቸውና እየመራቸው ወደ ጸሎቱ ስፍራ እንዲያመጣቸው ይጸልዩ ነበር፡፡ በጸሎታቸውም መሠረት የእግዚአብሔር እሳት በሌሊት በየቤቱ በየመኝታቸው እየወደቀ ሰዎችን ወደ ጸሎት ሜዳ ያመጣቸው ነበር፡፡ ሰዎቹም "ኢየሱስ ሆይ አድነን በኃጢአታችን መጥፋታችን ነው" እያሉ በመጮኸ ወደ ጸሎት ስፍራ በመምጣት ክርስቶስን ይቀበሉ ነበር፡፡

ይህ የወንጌል እሳት በአጭር ጊዜ ውስጥ መላ ኢንግላንድን አጥለቀለቀ፡፡ ሁለት ሚሊየን ሰዎች ወደ ክርስቶስ መጡ፡፡ ይህም የወንጌል እሳት አውሮፓን በሞላ አጥለቅልቆ ወደ አሜሪካና እስያ አገሮች ገሰገሰ፡፡ በአሜሪካን ሀገር በኒው ጀርሲ ግዛት በአትላንታ ሲቲ ይኖሩ ከነበሩ ስልሣ ሺ ሰዎች መካከል ክርስቶስን አንቀበልም ያሉት በቁጥር አምሳ አይሞሉም ነበር፡፡ በኬንታኪ ግዛት በፓዱካ ከተማ በአንድ ቤተክርስቲያን ውስጥ በአንድ ጊዜ አንድ ሺ ሰዎች ተጨምረው የቤተክርስቲያኒቱ መጋቢ ከሥራ ብዛት እንደሞተ ተዘግቧል፡፡

በዴንቨር የከተማው ሹም ለመላ ከተማው የጸሎት ቀን በማወጃቸው ከሌሊቱ አስር ሰዓት ጀምሮ ጸሎት ቤቶች፣ የቲያትርና የሲኒማ አዳራሾችና ሜዳዎች ሁሉ ለጸሎት በተሰበሰቡ ሰዎች ተሞልተው ነበር፡፡ በፖርትላንድ ግዛት ደግሞ ሠራተኞቻቸው በሙሉ ከሌሊቱ አስራ አንድ ሰዓት ጀምሮ እስከ ቀኑ ስምንት ሰዓት ድረስ በጸሎት የእግዚአብሔርን ፊት እንዲፈልጉ ሁለት መቶ አርባ ትላልቅ የንግድ ማዕከሎችና የገበያ አዳራሾች ስምምነት ተፈራርመው ነበር፡፡ በሉስ አንጀለስ በሺህ የሚቆጠሩ ሰዎች መንፈስ ቅዱስ መጣልን እያሉ የመንፈስ ቅዱስን መምጣት ለማክበር በትላልቅ መንገዶች ሰልፍ ያደርጉ ነበር፡፡ በአሜሪካን ብቻ ከዚህ እሳት የተነሳ ሃያ ሚሊየን ሰዎች ወደ ክርስቶስ እንደመጡ ይገመታል፡፡

ይህ ሁሉ ታላቅና መለኮታዊ እሳት እንዴት ሊቀጣጠል ቻለ? የዚህ ሁሉ ውጤት ምክንያቱ ያ ምስኪን ተራ ሰው ነው፡፡ ኢቫን ሮበርት፡፡ ሕያው ወደ ሆነው አምላኩ ታላቅ ጩኸትን የጮኸው ተራ ሰው፣ በዘመኑ እግዚአብሔር አስደናቂን ነገር ሲሠራ በራሱ ዓይን አየ፡፡ እግዚአብሔር በአንተ ሕይወት ታላቅ ሥራን እንዲሠራ ትፈልጋለህ? ወንጌል በዘመንህ እንደ ሰደድ እሳት እንዲቀጣጠልና ብዙዎች ወደ እግዚአብሔር መንግስት እንዲመጡ





ትፈልጋለህ? የምታመልከው አምላክ ከዚህም በላይ መሥራት ይችላልና ወደ አምላክህ ጸልይ፡፡ ስትጸልይ ትንሽን ነገር አትጠይቅ፡፡ እግዚአብሔር ትልቅ አምላክ ነውና ትልቅን ነገር ጠይቅ፡፡ እኔም እግዚአብሔርን በዘመኔ ትልቅን ነገር እንዲያሳየኝ እጠይቀዋለሁ፡፡

ወደ ሚቀጥለው ምዕራፍ ከማለፍህ በፊት ማስታወሻ ደብተርህን አዘጋጅ፡፡ እግዚአብሔር በዘመንህ እንዲያደርግ የምትናፍቀውን ታላቅ ነገር በማስታወሻ ደብተርህ ላይ ጻፈው፡፡ የአሁኑን ሰዓትና የዛሬውን ቀን መዝግብ፡፡ አምላክህ የሙሴ፣ የኢያሱ፣ የኤልያስ፣ የጳውሎስ አምላክ መሆኑን እመን፡፡ በእነርሱ ዘመን የሠራው እግዚአብሔር በአንተም ዘመን ይሠራል፡፡ ነገር ግን እግዚአብሔር እንድታምነው ይፈልጋል፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ያለ እምነት እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘት እንደማይቻል ይናገራል፡፡ /ዕብ. 11፡6/፡፡ በሕይወትህ ዘመን በእምነትህ እግዚአብሔርን ለማስደሰት እንድትችል መንፈስ ቅዱስ እንዲረዳህ ጸልይ፡፡ አሁን የተመኘኸውን ታላቅ ነገር ሊያሳይህ እግዚአብሔር ታማኝ እንደሆነ ደግሞ እመን፡፡ ይህን የናፍቆት ጸሎትህን ሀሳብህን ለሚደግፍ፣ በመንፈሳዊ ሕይወቱ ለበሰለ፣ ሊመክርህና ሊጸልይልህ ለሚችልና ለሚወድ ለአንድ ክርስቲያን አካፍል፡፡ አንተም በልብህ ውስጥ በተቀመጠው ራዕይና ናፍቆት ወይም ሸክም ላይ አሁን ጊዜ ወስደህ ጸልይ፡፡ እኔም ጌታ በረዳኝ መጠን እንድጸልይህ ከፈለግህ በአድራሻዬ ልትጽፍልኝ ትችላለህ፡፡ እግዚአብሔርም ትልቁን ናፍቆትህን ዕውን ያድርግልህ፡፡

# ምዕራፍ አሥር

## በራዕይ መኖር

ራዕይ ማለት ከሩቅ ያለውን አቅርቦ የማየት ወይም በዛሬ ላይ ቆሞ ነገን የማየት ችሎታ ማለት ነው፡፡ የራዕይን አስፈላጊነት እግዚአብሔር በቃሉ ሲናገር "ራዕይ ባይኖር ህዝብ መረን ይሆናል" /ምሳሌ 29፥18/ ይላል፡፡ መረን ማለት ልቅ፣ ተቅበዝባዥ፣ የሚጓዝበትን አቅጣጫ የማያውቅ፣ እረኛ የሌለው፣ ስለ ነገ ብዙም የማያውቅ ማለት ነው፡፡

ክርስቲያኖች ሁሉ በተለይም ክርስቲያን መሪዎች ራዕይ እንዲኖራቸውና በዚያ ራዕይ መሠረት እንዲኖሩ እግዚአብሔር ይፈልጋል፡፡ ህዝብ መረን የሚወጣውና በትክክለኛ አቅጣጫ የማይጓዘው በትክክል የሚመራውና ራዕይ ያለው መሪ የሌለው ከሆነ ነው፡፡ ህዝቡ የሚሄደው መሪው በሚያሳየው አቅጣጫ ነው፡፡ ይህ ትክክለኛ አቅጣጫ አይደለም፣ መሪያችንን አንከተልም ብሎ ህዝቡ በመሪው ላይ ካላመጸ በቀር ህዝቡ ስለሚጓዝበት አቅጣጫ ሁሉ ተጠያቂው መሪው ነው፡፡

በተለይም በቤተክርስቲያን ውስጥ ክርስቲያኑ ቶሎ በመሪው ላይ ስለማይነሳና ለዓመጽ ስለማይጋበዝ፣ ከፈሪሃ እግዚአብሔር የተነሣ ዝም ብሎ በትዕግስት መሪውን የመከተል አዝማሚያ ስለሚኖር፣ ህዝቡ ስለሚጓዝበት አቅጣጫ ሁሉ ዋናው ተጠያቂው መሪው ነው፡፡ ስለዚህ እግዚአብሔር በቤተክርስቲያን ውስጥ ያሉ መሪዎች ራዕይ ያላቸው እንዲሆኑ ይፈልጋል፡፡

ራዕይ ያለው መሪ ከሌለ ህዝብ መረን ይሆናል፣ አቅጣጫ የለሽ ወይም በትክክለኛ አቅጣጫ የማይጓዝ ይሆናል፡፡ ስለዚህም በራዕይ ስለመኖር ስንናገር ከምዕመኑ ይልቅ በመሪው ላይ ትኩረት እንሰጣለን፡፡ የዚህም ምዕራፍ ሀሳብ ዋናው ትኩረቱ በመሪዎች ላይ ሆኖ የቤተክርስቲያንም ራዕይና ዋና ተልዕኮ ምን መሆን እንዳለበት እንመለከታለን፡፡

የክርስቲያን መሪ ራዕይ ሁልጊዜም መሆን ያለበት ወንጌል ነው፡፡ የቤተክርስቲያንም ራዕይና ኃላፊነት የወንጌል ተልዕኮና ይህን ተልዕኮ መፈጸም ነው፡፡ ቤተክርስቲያን ከሁሉ ሥራ አስቀድማ የወንጌልን ሥራ የማትሠራ ከሆነ በምድር ላይ የመኖሯ ዓላማ ምንድር ነው?

ሰው እስከሆነ ድረስ ማንም ሰው የራሱ የሆነ ራዕይ አለው፡፡ ይህም ራዕይ መልካም ወይም ክፉ፣ ሰፊ ወይም ጠባብ ሊሆን ይችላል፡፡ የቤተክርስቲያን መሪ ራዕይ ግን መልካምና ሰፊ መሆን ይጠበቅበታል፡፡ መልካም ራዕይ ሲባል የወንጌልን ተልዕኮ ከመፈጸም የተሻለ ራዕይ አይገኝም፡፡ ሰፊ ራዕይ ሲባል ደግሞ ሰማይንና ምድርን የሠራው እግዚአብሔር ሁሉን የሚችልና ታላቅ መሆኑን በማመን ከእኛ ውስንነት ባሻገር እግዚአብሔር ብቻ ሊሠራ የሚችለውን ነገር ለመሥራት ማቀድና መመኘት ነው፡፡ ወይንም ደግሞ በሰው ጥበብና እውቀት ሊፈጸም ከቶ የማይቻለውን ነገር ገና ሥራው ሳይጀመር ከእግዚአብሔር የተነሳ ተሠርቶ እንዳለቀ በእምነት ማየት ነው፡፡

በአምስት ዓመት የአገልግሎት ዘመኔ በታላቁ ተልዕኮ አገልግሎት ውስጥ እግዚአብሔር ትልቅን ሥራ ሲሠራ አይቻለሁኝ፡፡ እግዚአብሔርም ይህን ሊሠራ የቻለው እኛ በእግዚአብሔር በመታመን ትልቅ እቅድ ስለነበረን ነው፡፡ ከአቅማችን በላይ የሆነ እቅድ ባወጣን ጊዜ 'አጉል መንጠራራት' ብለው የሚተቹ ሰዎች ነበሩ፡፡ ነገር ግን የእግዚአብሔርን ኤልሻዳይነት በመታመን የሚደረግ አጉል መንጠራራት እግዚአብሔርን ያከብራል፣ ያስከብራልም፡፡ እግዚአብሔር ክብር የሚያገኘው ከእኛ አቅም በላይ የሆነ ሥራ ሲሠራ እንጂ፣ እኛ የምንችለውን ብቻ ባለን የሰው ኃይልና ባለን ገንዘብ ብቻ ተደግፈን የምንሠራ ከሆነ እግዚአብሔር ኤልሻዳይ መሆኑን እንዴት ልናውቅ እንችላለን?

## የቤተክርስቲያን ዋናው ራዕይ

የቤተክርስቲያን ዋናው ራዕይ የወንጌልን ተልዕኮ የመፈጸም ራዕይ ነው፡፡ "ወደ ዓለም ሂዱ ወንጌልንም ለፍጥረት ሁሉ ስበኩ" /ማር. 16፡15/ የሚለውን መለኮታዊ ትዕዛዝ ሁል ጊዜ የመታዘዝና ታማኝ ሆኖ የመገኘት ራዕይ ነው፡፡ ቤተክርስቲያን "ሂዱ" የሚለውን ተልዕኮ ችላ ካለች የሞተች ቤተክርስቲያን ትሆናለች፡፡ ከክርስቶስ የተቀበለችውን የወንጌል አደራ በየዘመኑ በታማኝነት የማትፈጽም ከሆነ በምድር ላይ የመኖሯን ዓላማ ዘንግታለች ማለት ነው፡፡





የዚህች ዓይነት ቤተክርስቲያን ነግዶ እንዲያተርፍ የተሰጠውን መክሊት ቀብሮ የጌታውን መመለስ የጠበቀውን ሰነፍና ሃኬተኛ ባሪያ ትመስላለች፡፡ ቤተክርስቲያን ለጌታዋ ታማኝ ሆና የጌታዋን ተልዕኮ የምትፈጽም እንድትሆንም እንዳትሆንም የሚያደርገው መሪው ነው፡፡ የመሪው ራዕይ ወንጌል ከሆነ የቤተክርስቲያንም ራዕ ይ ወንጌል ይሆናል፡፡

ጌታ ኢየሱስ በማቴ. 24፡14 ላይ "ለአህዛብም ምስክር እንዲሆን ይህ የመንግስት ወንጌል በዓለም ሁሉ ይሰበካል፣ በዚያን ጊዜም መጨረሻው ይመጣል" ብሎ በተናገረው መሠረት የመጨረሻው ዘመን ምልክት የሆነው የወንጌል በዓለም ሁሉ መሰበክ በከፍተኛ ፍጥነት እየተፈጸመ ባለበት በዚህ ዘመን ቤተክርስቲያን ከማንኛውም አጀንዳ አስቀድማ የወንጌሉን አጀንዳ ልትወያይና ልትፈጽም ይገባታል፡፡ እግዚአብሔር ያስቀመጣቸው የቤተክርስቲያን መሪዎችም ቤተክርስቲያንን ወደዚህ ራዕይ ሊመሯት ይገባል፡፡

የቤተክርስቲያን ራስ የሆነው ክርስቶስ ኢየሱስ ከቤተክርስቲያን የሚጠብቀው ምንድር ነው? ጌታስ በክብር በመላዕክት ታጅቦ ቤተክርስቲያንን ወደራሱ ለመሰብሰብ ከመመለሱ በፊት ቤተክርስቲያን መፈጸም የሚገባት ነገር ምንድር ነው? የቤተክርስቲያንስ ራዕይና ዋና ተልዕኮዋ ምንድር ነው?

## 1/ ለዓለም መብራት መሆን

የቤተክርስቲያን ትልቁ ተልዕኮዋ መብራትዋን ለዓለም ማብራት ነው፡፡ ቤተክርስቲያን መብራትዋን ለዓለም የማታበራ ከሆነ በተሰጣት መብራት ላይ የራስዋን እንቅብ ደፍታለች ማለት ነው፡፡ የሚያስገርመው ግን በመብራትዋ ላይ እንቅብ የደፋች ቤተክርስቲያን፣ እንኳን በጨለማ ውስጥ ላለው ማብራት ቀርቶ እራስዋም በጨለማ ውስጥ መሆኗ ነው፡፡

በእኛ ዘመን ያለችውን ቤተክርስቲያን ከሐዋሪያት ዘመን ቤተክርስቲያን ጋር ስናወዳድር የሰማይና የምድር ያህል ልዩነት እንዳላቸው እንገነዘባለን፡፡ የሚያሳዝነው ግን ሁለቱም ቤተክርስቲያን ተብለው መጠራታቸው ነው፡፡ በሐዋርያት ዘመን የነበረችዋ ቤተክርስቲያን የምሥራቹን ወንጌል በመቅደስ፣ በየቤቱ፣ በየመንገዱና በየአካባቢው በግልጽነትና በድፍረት በማወጅዋ ምክንያት በዚያን ዘመን የነበረውን ዓለም በሙሉ በወንጌል ለመድረስ ችላለች፡፡ ከዚህም የተነሣ መሪዎቿ ሩጫችንን ጨርሰናል፣

መልካሙን ገድል ተጋድለናል፣ የተሰጠንን ተልዕኮ ፈጽመናል ብለው በድፍረት ለመናገር ችለዋል፡፡ /2ጢሞ. 4፡6-8 ፣ ዮሐ. 17፡4፣ የሐዋ. 13፡25/፡፡

በእኛ ዘመን ያለችዋን ቤተክርስቲያን ሁኔታ ቀርበን በምናጤንበት ጊዜ ግን ዋናው ተልዕኮዋ በየሰንበቱና በየሳምንቱ በአምልኮ ጣቢያዎች ወይም በየመሰብሰብያ አዳራሾች መሰባሰብ ወይንም ደግሞ የአገልጋዮችን መልዕክት መተንተንና መተቸት እየሆነ መጥቷል፡፡ የምሥራቹን ወንጌል ሳይሰማና በእግዚአብሔር ልጅ ሞትና ትንሣኤ የደህንነት መንገድ እንደተከፈተለት ሳያውቅ ወደ ዘላለም የሥቃይ ሥፍራ በየቀኑ የሚሄደው ህዝብ ቁጥር ምን ያህል ይሆን?

ምናልባት ቤተክርስቲያን አንዳንድ ጊዜ መደበኛ የአምልኮ ጊዜዋን ትታ በዚያ ሰዓት ወደ ቤተክርስቲያን ሳይሄዱ በየመንገዱና በአልባሌ ቦታዎች የሚገኙትን ወደ ክርስቶስ ለማምጣት ብትወጣስ አይቻል ይሆን? እስቲ መሪዎች እናስብበት፡፡

እግዚአብሔር ለቤተክርስቲያን የሰጣት ሥልጣንና ችሎታ እጅግ ትልቅ ነው፡፡ ይህንን የተሰጣትን ሥልጣን ከመጠቀም ይልቅ ግን በቤተክርስቲያን ውስጥ "እኛ ገና ራሳችንን አልቻልንም፣ ከራሳችን አናልፍም፣ አሁን ከምንሠራው በላይ መሥራት አንችልም፣ ወዘተ" የሚሉ ንግግሮች መሰማት የተለመዱ ናቸው፡፡ ይህም ማለት ከራሳችን አልፈን ተርፈን ለዓለም ሁሉ የምንበቃበት መብራት ተሰጥቶን እያለ መብራታችን ለሌሎች እንዳይታይ እንቅብ ደፍተንበታል ማለት ነው፡፡

ቤተክርስቲያን እኔ ራሴን ችያለሁ ወይም ያለኝ ከራሴ አይተርፍም ልትል ከቶ አትችልም፡፡ የቤተክርስቲያን ድንበርዋ ዓለም፣ የሥራዋም ውጤት የእግዚአብሔር መንግስት መስፋት ናቸው፡፡ ስለዚህም መብራትዋን በጨለማ ውስጥ ላሉና በዓለም ላሉ ሁሉ የማብራት ራዕይ ሊኖራት ይገባል፡፡

## 2/ የእግዚአብሔርን መንግሥት ማስፋፋት

ሌላው የቤተክርስቲያን ራዕይ ሊሆን የሚገባው የእግዚአብሔርን መንግሥት ማስፋፋት ነው፡፡ "የእኔ ቤተክርስቲያን" ወይም "የእኔ መንግሥት" የሚለው አስተሳሰብ ጠባብና ምድራዊ አስተሳሰብ ነው፡፡





ሁላችንም በትክክል ልናውቀው የሚገባን በጣም ቀላልና ግልጽ የሆነ እውነት አለ፡፡ ይኸውም ቤተክርስቲያን የክርስቶስ ነች እንጂ በአንድ ወቅት በእግዚአብሔር ጸጋ የቤተክርስቲያን መሪ ሆኖ የተቀመጠ የአንድ ሰው ወይንም የአንድ ቡድን አነስተኛ መንግሥት አይደለችም፡፡ ይህንን እውነት የእያንዳንዱ መሪ ልብ በትክክል እያወቀ በምድራዊ ሀሳብ በመታወር ይሁን ወይም በሌላ፣ የቤተክርስቲያን መሪዎች አንድን የክርስቶስን ቤተክርስቲያን "የእኔ"፣ "የአንተ" ሲባባሉ ይስተዋላሉ፡፡ አርቆ ያለማየት ችግር ወይንም የጠባብ ራዕይ ችግር ማለት እንግዲህ የዚህ ዓይነቱ ነው፡፡

የምድራዊና የሥጋዊ ሀሳብ ባላቸው ክርስቲያኖች ምክንያት ተሰቃይታ የነበረችው የቆሮንቶስ ቤተክርስቲያንም ተመሳሳይ ችግር እንደነበረባት ሐዋርያው ጳውሎስ በመረዳቱ፣ ከዚህ ጠባብ ራዕይ ተላቀው ሰፊ ራዕይ እንዲኖራቸውና ነገሮችን ሁሉ ከራሳቸው ጥቅም ይልቅ ለክርስቶስ ጥቅም እያሰቡ በእውነት እንዲመላለሱ ሲለምናቸውና ሲገስጻቸው እንደዚህ በማለት ጽፎላቸዋል፡፡

"ነገር ግን፣ ወንድሞች ሆይ፣ ሁላችሁ አንድ ንግግር እንድትናገሩ በአንድ ልብና በአንድ አሳብም የተባበራችሁ እንድትሆኑ እንጂ መለያየት በመካከላችሁ እንዳይሆን በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እለምናችኋለሁ፡፡ ወንድሞቼ ሆይ፣ በመካከላችሁ ክርክር እንዳለ ስለ እናንተ የቀሎዔ ቤተ ሰዎች አስታውቀውኛልና፡፡ ይህንም እላለሁ፡- እያንዳንዳችሁ፡- እኔ የጳውሎስ ነኝ፣ እኔስ የአጵሎስ ነኝ፣ እኔ ግን የኬፋ ነኝ፣ እኔስ የክርስቶስ ነኝ ትላላችሁ፡፡ ክርስቶስ ተከፍሎአልን? ጳውሎስስ ስለ እናንተ ተሰቀለን? ወይስ በጳውሎስ ስም ተጠመቃችሁን?" /1ቆሮ 1፡10-13/፡፡

ሐዋርያው ጳውሎስ በዚህ ስፍራ ለሚጠይቃቸው ጥያቄዎች መልሶቹ ክርስቶስ አልተከፈለም፣ ለቤተክርስቲያን የተሰቀለው ክርስቶስ ብቻ ነው፣ የተጠመቃችሁትም በክርስቶስ ስም ነው፣ የሚሉ ናቸው፡፡ ቤተክርስቲያን የክርስቶስ መሆንዋን ስንዘነጋ "የእኛ" እንደሆነች ለመቁጠር እንነሳሳለን፡፡ ስለዚህም "የእኔ" ድንበርና መንግሥት የሚል ስሜት በውስጣችን ይፈጠራል፡፡ ማንም የራሱ መንግሥት እንዲሰፋለት እንደሚፈልግ ሁሉ እኛም "የእኛ" የምንለው ቤተክርስቲያን እንደምንም ቢሰፋልን ደስታችን ብዙ ይሆናል፡፡ ከዚህም የተነሳ በሌላ አጥቢያ ቤተክርስቲያን የሚያመልክ ምዕመን እንደምንም ብሎ "የእኛን" እንዲሞላ ፍላጎታችን ከፍ ይላል፡፡

በመሠረቱ "የእኛ" ወይም "የሌላ" የሚለው ቋንቋ ከየት መጣ? ራዕይ ከማጣት የተነሳ አይደለምን? ይህንን እውነት ግልጽ ለማድረግ አንድ ምሳሌ ለመስጠት እወዳለሁ፡፡ ለምሳሌ ያህል በአንድ ወቅት በአንድ መንደር በ"ሀ" ቤተክርስቲያን የሚያመልኩ ምዕመናን ቁጥር 3,000፣ በ"ለ" ቤተክርስቲያን የሚያመልኩ ደግሞ ቁጥራቸው 2,000 ነው እንበል፡፡ በዚያን ወቅት በዚያን መንደር የሚገኙ ምዕመን ጠቅላላ ቁጥር 5,000 ነው ማለት ነው፡፡

ለምሳሌ ያህል የ"ሀ" ቤተክርስቲያን መሪዎች ራዕያቸው ጠባብና ሀሳባቸው ምድራዊ ስለሆነ "የእኔ" የሚሉት ቤተክርስቲያናቸው እንዲያድግ ስለፈለጉ በተለያየ ምክንያት በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ 1,000 ምዕመን ከ"ለ" ቤተክርስቲያን ወደ እነርሱ እንዲፈልስ አደረጉ፡፡ በዓመቱ ውስጥ በዚያን መንደር ወደ እግዚአብሔር መንግሥት የተጨመረ አዲስ ሰው አልነበረም፡፡ ነገር ግን የ "ሀ" ቤተክርስቲያን ምዕመን ቁጥር አድጎ 4,000 ሲሆን የ "ለ" ቤተክርስቲያን ምዕመን ቁጥር በአንጻሩ ቀንሶ 1,000 ብቻ ሆኗል፡፡

ከዓመት በኋላ በሁለቱም ቤተክርስቲያን የከረረ ግጭትና ቅራኔ ተፈጥሮ ነበር፡፡ ክርስቶስንም ያላወቁ የአካባቢው ነዋሪዎች በቤተክርስቲያናቱ መካከል ያለውን ግጭት ስለሚያውቁ በራሳቸው አነሳሽነት ወደ ቤተክርስቲያን ሄደው ክርስቶስን ለመከተል ውሳኔ አላደረጉም ነበር፡፡ የሁለቱም ቤተክርስቲያን መሪዎች ዓመቱን በሙሉ ያሳለፉት በጥላቻና በክርክር እንጂ ምዕመኑ ወንጌል ላልደረሳቸው ለአካባቢው ነዋሪዎች ወንጌልን እንዲያደርስ በመላክ አልነበረም፡፡ በዚህም ምክንያት በዓመቱ ውስጥ አንድም አዲስ ሰው ወደ ጌታ አልመጣም ነበር፡፡ በዚህ መንደር ያለችው የክርስቶስ ቤተክርስቲያን በዓመቱ ውስጥ ዕድገት አሳይታለችን? የትኛዋ ቤተክርስቲያን አድጋለች? ችግሩስ ምንድር ነው?

እንግዲህ ራዕይ ለሌለውና "የእኔ" በሚል ጠባብ አስተሳሰብ ለታሰረው መሪ የ"ሀ" ቤተክርስቲያን አድጋለች ለማለት ያስችል ይሆናል፡፡ ራዕዩና አስተሳሰቡ ሰማያዊ ለሆነ መሪ፣ ቤተክርስቲያን የክርስቶስ እንጂ የእኔ አይደለችም ለሚለው፣ በዚያን ዓመት የክርስቶስ ቤተክርስቲያን አላደገችም፡፡ በአንጻሩ ግን እድገቷ ቀንሶ ታይቷል፡፡ በምዕመናን ቁጥር ባትቀንስም፣ በዓመቱ መጨረሻ ብዛቱ ያው 5,000 ቢሆንም፤ በጥራት፣ በቅድስናና በምስክርነት ግን እጅግ ቀንሳለች፡፡

ስለዚህ የመሪ ራዕዩ ቤተክርስቲያን የክርስቶስ ናት፤ ለእኔ ድርሻዬ፣ ክልሌ፣ መንግሥቴ የምለው የለኝም፣ እኔ በእግዚአብሔር





መንግሥት ውስጥ አገልጋይ ነኝ የሚል መሆን አለበት፡፡ የራስን መንግሥት ለመገንባት ከመሯሯጥ ይልቅ የክርስቶስን መንግሥት ለማስፋፋት ዋጋ ብንከፍል ይመረጣል፡፡

## 3/ የእግዚአብሔርን ክንድ ማስተዋወቅ

የቤተክርስቲያን ሌላው ተልዕኮ የእግዚአብሔርን ማንነት፣ ችሎታውንና ኃይሉን፣ ቸርነቱንና ፍቅሩን ለሰዎች ሁሉ መመስከር ነው፡፡ የእግዚአብሔር ስም "ኤልሻዳይ" ሲሆን ትርጉሙም ሁሉን የሚችል እግዚአብሔር ማለት ነው፡፡ በእርግጥም እግዚአብሔርን የሚያቅተው አንድም ነገር የለም፡፡ በእግዚአብሔር ዘንድ "ይህ እንዴት ይቻላል?" የሚባል ነገር የለም፡፡ ይህንን የእግዚአብሔርን ችሎታና ብርታት፣ ለዓለም የማስተዋወቅ ኃላፊነት የቤተክርስቲያንና የቤተክርስቲያን መሪ ኃላፊነት ነው፡፡

"በእግዚአብሔር ዘንድ ይህ የሚያቅት ነው፣ ከቶ የማይቻል ነው" የሚል ቋንቋ የለም፡፡ የእግዚአብሔርን ኤልሻዳይነት የበለጠ ለመረዳት እንድትችል የሚከተሉትን የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች አጥና፡፡ (ዘፍጥ. 18፡12-14፤ ሉቃ. 1፡36-37፤ ሉቃ. 18፡27፤ ኢዮብ 42፡2፤ ኤር. 32፡17፣27፤ ዮሐ. 14፡12፤ ሮሜ. 4፡18-21፤ 2 ነገሥ. 3፡16-19፡፡) በ1990 ዓ.ም. በክረምት ወራት በ52 ቀናት የዘመቻ ፊልጶስ አገልግሎት የአዲስ አበባን ከተማ በወንጌል ለመድረስ በተነሳንበት ጊዜ የሚያስፈሩን እጅግ ብዙ ነገሮች እንዲሁም የውስጥና የውጭ ተቃውሞዎች ነበሩብን፡፡ ነገር ግን እነዚህን ጥቅሶች በማጥናት እግዚአብሔር ኤልሻዳይ መሆኑን በማመን በዕቅዳችን ጸንተን ቆምን፡፡ እግዚአብሔርም ሁሉን ቻይነቱን ሲገልጥ በዓይኖቻችን አየን፡፡

ስለዚህም የቤተክርስቲያን መሪዎች "ይቻላል" የሚልን ቋንቋ እንዲናገሩ እግዚአብሔር ይፈልጋል፡፡ ወንጌልን ለዓለም ሁሉ ማድረስ በሚታሰብበት ጊዜ ብዙ እንቅፋቶች፣ ተራራ የሚመስሉና የሚያስፈሩ ነገሮች ከፊት ለፊት ተደቅነው ሊታዩ ይችላሉ፡፡ የቤተክርስቲያን መሪ እነዚህን የተለያዩ ተራራዎች እያየ መፍራትና ኃላፊነቱን ሳይወጣ መቅረት አይገባውም፡፡ ነገር ግን ተራራን ሁሉ ደልዳላ ሜዳ ሊያደርግ በሚችል በእግዚአብሔር በመታመን፣ ተልዕኮውን ለመወጣት በቆራጥነት መነሳትና መንቀሳቀስ አለበት፡፡

አንድን ነገር እንድንፈጽም እግዚአብሔር ሲያዘን መፈጸም እንደምንችልና ከእያንዳንዱ ትዕዛዝ ጋራ የእርሱ ክንድና ብርታት

አብሮ መኖሩን ስለሚያውቅ ነው፡፡ ስለዚህ አንድ መሪ ገና ጉዞውን ሳይጀምር የተራራውን ረጅምነት፣ የውቃውን ሙላት እያየ መንቀጥቀጥ የለበትም፡፡ ተራራው ደልዳላ ሜዳ እንደሆነ፣ የውቃውም ሙላት እንደሌለ አድርጎ በእምነት የማየትንና ወደፊት የመራመድን ራዕይ በውስጡ ሊያሳድግ ይገባዋል፡፡ (ዘኍል ምዕራፍ 13 እና 14 ተመልከት፡፡)

ብላቴናው ዳዊት ገናና መስሎ ይታይ የነበረውን ጎልያድን ለመዋጋት በቀረበበት ጊዜ የነበረው ራዕይ ይህ ነበር፡፡ ያን አስፈሪ የነበረውን ጎልያድን እንደ ተራ ነገር መቁጠር፡፡ ዳዊት እንደ መሪ ጎልያድን ፊት ለፊት ለመጋጠም ሲሄድ ያይ የነበረው "ቁመቱ ስድስት ክንድ ከስንዝር የሆነ፣ ዋናኛ ጀግና፣ በራሱ የናስ ቁር የደፋ፣ አምስት ሺ ሰቅል ናስ የሚመዝን ጥሩር የለበሰ፣ ስድስት መቶ ሰቅል ብረት የሚመዝን ጦር የያዘ፣ በጋሻ ጃግሬ የሚመራውን" የሚያስፈራውን ጎልያድን አልነበረም፡፡ /1ሳሙ. 17 ተመልከት፡፡/

ይህንን የመሰለውን ጎልያድን ቢያይ ኖሮ ይህ ብላቴና ለጋ ወጣት በተንቀጠቀጠና አካባቢውን ለቆ በሸሸ ነበር፡፡ ዳዊት ግን የነበረው ራዕይ "ራሱ የተቆረጠ ጎልያድ፣ የፍልስጥኤማውያንን ሠራዊት ሬሶች የሰማይ ወፎችና የምድር አራዊት ሲበሉ፣ የተናቀውም የእስራኤል ሠራዊት ድልን ሲቀዳጅ" ነበር፡፡ /1ሳሙ. 17፡45-47/

ዳዊት ከፊት ለፊቱ ከቆመው ተራራ ባሻገር ያለውን ይመለከት ነበር፡፡ ይኸውም ምድር ሁሉ በእስራኤል ዘንድ አምላክ እንዳለ፣ ይህም የእስራኤል አምላክ በጦር ብዛት ሳይሆን በስሙ ሥልጣን ብቻ የሚያድን እንደሆነ ዛሬ ይታወቃል በማለት፣ ይህ በአምላኩ የበረታ ብላቴና የእግዚአብሔርን ሁሉን ቻይነት መስከረ፣ አስመሰከረም፡፡

የወንጌልን ተልዕኮ የተቀበለ መሪ የእግዚአብሔርን ሁሉን ቻይነት ለማወጅና ለማሳወጅ የተጠራ ነው፡፡ መሪ "አይቻልም" ካለ ተከታዮቹም "አይቻልም" ይላሉ፡፡ ይህም ብቻ ሳይሆን መሪ "አይቻልም" ካለ ሁሉን ቻይ የሆነው እግዚአብሔርም ከእንደዚህ ዓይነቱ መሪ ጋር ለመሥራት ይቸገራል፡፡

መሪዎች የዘሩትን ያጭዳሉ፡፡ ሙሴን እግዚአብሔር ለታላቅ ሥራ ሲጠራው ሙሴ በተደጋጋሚ "እኔ ይህን ተልዕኮ ለመፈጸም አልችልም" ብሎ የመለሰ ሰው ነበር፡፡ በኋላም እርሱ ከላካቸው





አሥራ ሁለት ሰላዮች መካከል አሥሩ "አንችልም" ብለው መለሱለት፡፡ ኢያሱ ከእግዚአብሔር ጋር "እንችላለን" ብሎ የመለሰ መሪ ነበር፡፡ በኋላም እርሱ የላካቸው መሪዎች "እንችላለን" ብለው መለሱለት፡፡ (ዘኍ. 14፡6-9 ፤ ኢያሱ 2፡24)፡፡

ቤተክርስቲያን እችላለሁ፣ እዋጋለሁ፣ አሸንፋለሁ፣ እወርሳለሁ ማለት ይኖርበታል፤ ምክንያቱም የተጠራችው ለዚሁ ነውና፡፡ የቤተክርስቲያን መሪም ራዕይ እንደዚሁ የመቻል፣ የመዋጋት፣ ድል የማድረግ፣ የመውረስና የማውረስ ራዕይ መሆን አለበት፡፡ የቤተክርስቲያን መሪ ከዛሬ ይልቅ ነገ ለማደግና የተሻለ ፍሬን ለማፍራት በድል አድራጊው በእግዚአብሔር መታመን አለበት፡፡ ወንጌልን በምድራችን ላሉ የተለያዩ ብሔረሰቦች ማድረስ ስናስብ ብዙ አይቻልም የምንላቸው ነገሮች ሊኖሩ ይችላሉ፡፡ - ነገር ግን ወንጌል ለሁሉም አስፈላጊ ስለሆነ በእግዚአብሔር ጉልበትና ኃይል በመታመን በድል አድራጊነት ወንጌልን ለሰው ሁሉ ለማድረስ መነሳት ያስፈልጋል፡፡

ቤተክርስቲያን የአዋጅ ነጋሪ ሆና ለዓለም ሁሉ እንድታስተላልፍ የተላከችበት ወንጌል ታላቅ ኃይል ያለው ነው፡፡ ሰዎችን ከሰይጣን ኃይል ነፃ የሚያወጣ፣ በሽተኞችን የሚፈውስ፣ የከፉውን ቀንበር የሚሰብር፣ የእግዚአብሔር ክንድ የሚገለጥበት ወንጌል ነው፡፡ ቤተክርስቲያን ይህን ታላቅ ወንጌል ለሰው ሁሉ በማወጅ በታላቅ ኃይል የሚሠራውን የእግዚአብሔርን ክንድ ለዓለም ሁሉ እንድታስተዋውቅ ተጠርታለች፡፡

## 4. የጥንቷን ቤተክርስቲያን ራዕይ መጨበጥ

ቀደም ተብሎም እንደተጠቀሰው የጥንቷ ቤተክርስቲያን ወንጌልን የምታሰራጭ ቤተክርስቲያን ነበረች፡፡ ወንጌልን ለሌሎች ለማድረስ ጥቂት "የምስክርነት ቡድን" አባላትን ብቻ ልካ አልተቀመጠችም፡፡ ነገር ግን የእግዚአብሔርን ቸርነት የቀመሱ ሁሉ ቸርነቱንና መልካምነቱን ለሌሎች ለማወጅ ወደ ዓለም ሁሉ ወጥተዋል፡፡

በዚህ ዘመን ያለች ቤተክርስቲያን ግን የወንጌልን አደራ ለጥቂት ሰዎች ብቻ "ለምስክርነት ጓድ" በመተው ዋና የነበረውና የሁሉም ተልዕኮ የነበረው የወንጌል ተልዕኮ እንዲረሳ ምክንያት ሆናለች፡፡ በየቤተክርስቲያኖቻችን እጅግ ብዙ ህዝብ ሰብስበን

ተቀምጠን ክርስቶስ የሞተለትን ሥራ ለጥቂት ፈቃደኛ ሰዎች ሰጥተናል፡፡ ወንጌልን መስበክ ግን ግዴታ ነው፡፡

ወንጌልን መስበክ ግዴታ መሆኑን የተረዳው ሐዋሪያው ጳውሎስ "ወንጌልንም ባልሰብክ ወዮልኝ" /1ቆሮ. 9፡16/ በማለት ሁልጊዜ ኃላፊነቱን ለመፈጸም መኖር እንዳለበት ለራሱ ያሳስባል፡፡ የጥንቷ ቤተክርስቲያን መድረስ የምትችልበትን ሥፍራ በሙሉ ሄዳለች፣ መላክ የምትችለውን ምዕመን በሙሉ ለወንጌል ሥራ ልካለች፡፡

ወደ ሌላው ዓለም ሳንሄድ በአገራችን እንኳ ያለውን ሁኔታ በምንመለከትበት ጊዜ "የእርሱን በጎነት እንዲናገሩ የተጠሩ" ሰዎች ቁጥር በሚሊዮን የሚቆጠር ሆኗል፡፡ ይህም ማለት ለወንጌል አደራ ታማኞች በነበሩ በአባቶቻችን የወንጌል አገልግሎት ምክንያት ከዛሬ ሠላሣ ዓመት በፊት ከሁለት መቶ ሺ በታች የነበረው በክርስቶስ ጌትነትና አዳኝነት ያመኑ ሰዎች ቁጥር ዛሬ በአገራችን ከሰባት ሚሊየን እንደሚበልጥ ይገመታል፡፡ ሆኖም ግን በአገራችን ካሉ ከሰማንያ በላይ ብሔረሰቦች መካከል አሁንም ግማሽ የሚያህለው ገና በወንጌል አልተደረሰም፡፡ አንዳንዱ ብሔረሰብ በጭራሽ "ኢየሱስ ክርስቶስ" የሚለውን ስም ሰምቶ የማያውቅ ነው፡፡

በቅርቡ ከውጭ ሀገር ከመጣ ከአንድ እንግዳ ጋር የወንጌልን ተልዕኮ በመፈጸም ላይ እንወያይ ነበር፡፡ ሰውዬውም "እስካሁን ለአፋር ብሔረሰብ ወንጌል ያልደረሰው በምን ምክንያት ነው?" ሲል ጠየቀኝ፡፡ እኔም ለጥያቄው መልስ ሳስብ ክርስቶስ ለአፋርም ሕዝብ እንደሞተ፣ እያንዳንዱን ሰው እግዚአብሔር እንደሚያፈቅር ፤ ነገር ግን ወንጌልን ይዞ ወደ አፋር ብሔረሰብ የገባና ለወንጌል ሲል የሞተ ሰው እኔ እስከማውቀው ድረስ እንደሌለ ተረዳሁኝ፡፡

የጥንት ቤተክርስቲያን የወንጌል አርበኞች ግን የተሰጣቸውን የወንጌልን አደራ ለመወጣት ሲሉ ወንጌል ወዳልደረሰበት ሥፍራ ሁሉ በመሄድ "... እስከ ሞት ድረስ ተደበደቡ፣ መዘበቻ በመሆንና በመገረፍ ከዚህም በላይ በእስራትና በወህኒ ተፈተኑ፣ በድንጋይ ተወግረው ሞቱ፣ ተፈተኑ በመጋዝ ተሰነጠቁ፣ በሰይፍ ተገድለው ሞቱ፣ ሁሉን እያጡ መከራን እየተቀበሉ እየተጨነቁ የበግና የፍየል ሌጦ ለብሰው ዞሩ፣ ዓለም አልተገባቸውምና በምድረ በዳና በተራራ በዋሻና በምድር ጉድጓድ ተቅበዘበዙ፡፡" /ዕብ. 11፡35-38/፡፡

የጥንት ዘመን ክርስቲያኖች ይህች ዓለም የእነርሱ እንዳልሆነች በሚገባ ያውቁ ነበር፡፡ ስለዚህም ላልተገባቸው ዓለም





አልኖሩለትም፡፡ ነገር ግን ለተጠሩበት ሰማያዊ ጥሪና ለተቀበሉት የወንጌል አደራ ታማኞች ሆነው አምላካቸውን አስከብረው ኖሩ፡፡ ይህ ዘመን ግን ለአብዛኞቹ ክርስቲያኖች ለወንጌል ሲሉ በመጋዝ መሰንጠቅ ይቅርና የኩሬና የወንዝ ውኃ እንኳን ወደሚጠጣበት የገጠር አካባቢ ወንጌልን ይዞ ለመሄድ እጅግ ከባድ ፈተና እየሆነ የመጣበት ዘመን ነው፡፡

ለወንጌል ሲባል የበግና የፍየል ሌጦ ለብሶ መዞር ይቅርና በኢትዮጵያ ውስጥ ዋጋ ከፍሎ ወንጌልን በጨለማ ውስጥ ላለ ሕዝብ ከማድረስ ይልቅ እንደ ምንም መንገዱን ፈልጎ ወደ አውሮፓና አሜሪካ መግባት የሚመረጥበት ዘመን ነው፡፡ ወደ አሜሪካም ይሁን የትም ሥፍራ የወሰደን መንፈስ ቅዱስ ከሆነ ግን ምንም ቅሬታ የለኝም፡፡ ዋጋ መክፈሉን ጠልተንና የተሻለ ኑሮ ፍለጋ ስንል ሥፍራችንን ለቀን ከሆነ ግን ወደ ሥፍራችን ብንመለስ እንደሚሻል አስባለሁ፡፡ በራዕይ ለመኖር ስንወስን የበግና የፍየል ሌጦ ሊያስለብሰን፣ ከምቾታችን ሊቀንስብን፣ መከራ ሊያበዛብን ይችላል ፤ ቢሆንም ግን በአምላካችን ዘንድ ብድራቱ ትልቅና የከበረ ነው፡፡

የወንጌልን አደራ መጠበቅ የሚቻለው ወንጌል የሚያስከፍለውን ዋጋ በታማኝነት በመክፈልና በሰማያዊ ራዕይ በመኖር ብቻ ነው፡፡ እንግዲህ አንተ ራዕይ ያለው መሪ ከሆንክ በመጀመሪያ ራስህ ወንጌል የሚያስከፍለውን ዋጋ ሁሉ ለመክፈል ተዘጋጅ፡፡ ቤተክርስቲያንህ የጥንቷን ቤተክርስቲያን ራዕይ እንድትጨብጥና የወንጌልን አደራ ለመፈጸም ወደ ብሔረሰቡ ሁሉና እስከ ምድር ዳርቻ እንድትንቀሳቀስ የማድረግ ኃላፊነትን ተሸክመሃል፡፡ ራዕይ ከሌለህ ደግሞ የራዕይ ሁሉ ምንጭና ባለቤት ወደሆነው ወደ እግዚአብሔር ቅረብ፣ እርሱም በውስጥህ እረፍት የማይሰጠውን ራዕይና የወንጌል እሳት ይፈጥራል፡፡

## 5. በድፍረትና በጀግንነት የተሞላ አመራር መስጠት

መሪው ደፋር ከሆነ ተከታዩም ህዝብ ደፋር ይሆናል፣ መሪው ፈሪ ከሆነ ደግሞ የሚከተለውም ህዝብ ፈሪ ይሆናል፡፡ "ልጅ አባቱን፣ አይብ አጓቱን ይመስላል" እንዲሉ ጥሩ መሪዎች በቤተክርስቲያን ካሉ ጥሩ መሪዎችን ያፈራሉ፡፡ መሪው ወኔ ያለውና ቆራጥ ከሆነ ተከታዩም ህዝብ ወኔ ያለውና ቆራጥ ህዝብ ይሆናል፡፡

በመጽሐፍ ቅዱስም ውስጥ ይህን እውነት የሚያረጋግጡ ብዙ ማስረጃዎች ይገኛሉ፡፡ ለእግዚአብሔር የማይታዘዙ ልጆች የነበሩት ካህኑ ዔሊ ያሳደገው ሳሙኤል ልጆቹ ለእግዚአብሔር የማይታዘዙ ሆኑ፡፡ ንጉሥ ሳኦል ከህዝቡ ጋር ለጦርነት ወጥቶ በነበረበት ጊዜ ጎልያድን ፈርቶ ስለነበረ፣ ለጦርነት ወጥቶ የነበረው እስራኤላዊ ሁሉ አርባ ቀን ሙሉ በጎልያድ ፊት ልቡ ቀለጠ፡፡

ንጉሡ ሳኦል ስለፈራ የሳኦል ጀግኖችም ፈሩ፡፡ ነገር ግን ደፋር የነበረው ዳዊት ሲመጣ ፈርቶ የነበረው ሠራዊት ሁሉ ደፋርና አሳዳጅ ሆነ፡፡ መሪው ጀግና ስለነበረ ሠራዊቱም ጀግና ሆነ፡፡ የሚገርመው ግን ከዳዊት ጋር ሆኖ የጎልያድን ራስ ከቆረጠ በኋላ ፍልስጥኤምን ያሳደደው ያው የሳኦል ሠራዊት ነበረ እንጂ ሌላ አዲስ ሠራዊት አልመጣም፡፡ ፈሪውን ሠራዊት ጀግና ያደረገው ጀግና መሪ በፈሪው ሠራዊት መካከል መገኘት ነበር፡፡ /1ሳሙ. 17 ተመልከት፡፡/

አንተ ምን ዓይነት መሪ ነህ? ባለህበት ትውልድ የተጣለብህን የወንጌልን አደራ ለመወጣት ደፋርና ቆራጥ መሪ መሆን አለብህ፡፡ ወጣቱ ዳዊት በድፍረቱና በእግዚአብሔር ላይ በነበረው ታላቅ እምነቱ ምክንያት በዘመኑ ታሪክ እንደሠራ ምናልባትም አንተንም እግዚአብሔር ታሪክ እንድትሠራ እየፈለገህ ይሆናል፡፡ እግዚአብሔር በየዘመናቱ ሀሳቡንና ፈቃዱን ለመፈጸም ሰውን ይፈልጋል፡፡ ዛሬም አንተን ይፈልጋል፡፡

እግዚአብሔር ሁልጊዜ ታሪክ ሠሪ ነው፡፡ ነገር ግን ታሪክ የሚሠራው ደፋር፣ ቆራጥና ታዛዥ ሰዎችን ሲያገኝ ነው፡፡ እግዚአብሔር ታሪክ ሠሪ አምላክ መሆኑን አምነው ከእርሱ ጋር ለመሥራት በልበ ሙሉነት የሚወጡትን ሰዎች ሲያገኝ እግዚአብሔር ከእነርሱ ጋር ሆኖ ታሪክ ይሠራል፡፡

አንድ የእግዚአብሔር ሰው ሲናገር "እኛ የእግዚአብሔር ኃይል መተላለፊያ ሽቦዎች ነን" አለ፡፡ ሽቦው ከሌለ ኃይሉ ሊተላለፍ እንደማይችል ሁሉ የእግዚአብሔርም ኃይል እንዲገለጥ እግዚአብሔር የሚጠቀምበት ሰው ያስፈልጋል፡፡ አንተ እግዚአብሔር የሚጠቀምብህ ዓይነት ሰው መሆን ትፈልጋለህ? እግዚአብሔር የሚልህን ሁሉ ለመታዘዝ ፈቃደኛ ሆነህ ከተገኘህ እግዚአብሔር ሀሳቡን በሕይወትህ ይፈጽማል፡፡





ሁልጊዜ የእግዚአብሔር ሰው ሆነህ፣ እርሱ የሚልህንና የልቡን ፈቃድ ለመፈጸም ከኖርህ በሕይወትህ ዘመን ሁሉ በራዕይ መኖር ትችላለህ፡፡ አንተ በእግዚአብሔር ላይ ያለህ መታመንና መደገፍ አድጎ፣ እንደ እግዚአብሔር ሀሳብ መኖር ስትጀምር አንተ የምትመራው ህዝብም የእግዚአብሔርን ሀሳብ በማገልገል እንዲኖር ከፍተኛ አስተዋጽኦ ታደርጋለህ፡፡

## 6. በሰማይ ሀብት መሰብሰብ

የቤተክርስቲያንና የቤተክርስቲያን መሪ ራዕይ ምድራዊ ሳይሆን ሰማያዊ ሀብትን መሰብሰብ መሆን አለበት፡፡ በሰማይ ሀብትን መሰብሰብ የሚቻለው የወንጌልን ተልዕኮ ለመፈጸም በመኖር ነው፡፡ ቤተክርስቲያን በዚህ ዘመን ለወንጌል የመጀመሪያውን ሥፍራ እንዳትሰጥ ምክንያት የሆኑ ሌሎች ብዙ ዕቅዶች አሏት፡፡

ለቤተክርስቲያን ለወንጌል ሥራ ተብሎ ከሚገባው ገንዘብ ምን ያህሉ በቀጥታ ለወንጌል አገልግሎት፣ ሰዎችን ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ለማምጣትና የምሥራቹን ለማወጅ አገልግሎት ይመደብ ይሆን? ልባችን የሚያውቀው እውነት ግን በብዙዎቻችን ዘንድ ለወንጌል ስርጭት አምስት መቶ ብር ከመመደብ ይልቅ ለሙዚቃ መሣሪያ አምስት ሺ ብር፣ ወይም ለህንፃ ግንባታ አምሳ ሺ ብር መመደቡ እጅግ ይቀለናል፡፡

የሙዚቃ መሣሪያውም ግንባታውም አስፈላጊ ቢሆንም በወንጌል የዳኑ ሰዎች ከሌሉ ለማን ይዘመራል? ማንስ ይዘምራል? በህንፃውስ ውስጥ ማን ይሰበሰባል? የቤተክርስቲያን ገንዘብ በቀጥታ ለወንጌል ሥራ መዋል ካልቻለ የቤተክርስቲያን ሀብት በሰማይ ሳይሆን በምድር እየተሰበሰበ ነው ማለት ነው፡፡ በሰማይ የሚሰበሰብ ሀብት ማለት ዛሬ የተሠራው ሥራ ውጤቱ በእግዚአብሔር መንግሥት ይገኛል ማለት ነው፡፡

በዚህ ዘመን በኢትዮጵያ ውስጥ ያለች ቤተክርስቲያን ለወንጌል ሥርጭት መጠቀም ያለባትን ገንዘብ የመሰብሰቢያ ህንፃዎች በመገንባት ወይም እርስ በርስ በመካሰስ እንዳትጨርስ ልትጠነቀቅ ይገባታል፡፡ የቤተክርስቲያን ራዕይዋ ሁልጊዜም ሰማያዊ መሆን አለበት፡፡ ክርስቶስ ቢመጣ በፊቱ ይዞ የምቆመው ምንድር ነው? እያለች ቤተክርስቲያን ሁልጊዜ ራስዋን ልትጠይቅ ይገባታል፡፡

ቤተክርስቲያን ጥንቃቄን ሳታደርግ የወንጌልን ተልዕኮ መፈጸም ረስታ፣ ራዕይዋ የህንፃ ሥራና ሌሎች ጉዳዮችን ማከናወን ብቻ ሆኖ ቢቀር ቀስ በቀስ ባዶ የቤተክርስቲያን አዳራሽ ይዛ መቅረትዋ የማይቀር ይሆናል፡፡ ስለዚህም የቤተክርስቲያን ራዕይ ማለት በአብዛኛው የመሪው ራዕይ ስለሆነ መሪው ቤተክርስቲያንን በእግዚአብሔር ዘንድ ደሃ ወይም ባለጸጋ ሊያደርጋት ይችላል፡፡

በእግዚአብሔር ዘንድ ደሃ የሆነች ቤተክርስቲያን ሲባል የተጣለባትን የወንጌልን አደራ በሚገባ ሳትፈጽም በሌሎች አጀንዳዎች ተይዛ የጌታን መመለስ የምትጠብቅ ቤተክርስቲያን ስትሆን፤ በእግዚአብሔር ዘንድ ባለጠጋ ቤተክርስቲያን ደግሞ ከየትኛውም አጀንዳ ይልቅ ለወንጌል ተልዕኮ ቅድሚያ በመስጠት፣ በሚገባ የእግዚአብሔርን ሀሳብ ለማገልገል ኖራ፣ ብዙዎችን ከእሳት ነጥቃ፣ ለእግዚአብሔር መንግሥት አዘጋጅታ የምትጠብቅ ማለት ነው፡፡

የቤተክርስቲያን መሪ ሁልጊዜ ማወቅና ማሰብ ያለበት እግዚአብሔር የሚፈልገው ህንፃውን ሳይሆን ህዝቡን፣ መንፈሳዊ ተቋም ማደራጀትን ሳይሆን የምሥራቹን ወንጌል ላልሰሙት ሁሉ ማብሰርን ነው፡፡ ስለዚህ የመሪው ራዕይ በሚታየው ድርጅት ሳይሆን በማትታየዋ በክርስቶስ ቤተክርስቲያን፣ በምድራዊ ሀሳብ ሳይሆን በሰማያዊና በመለኮታዊ ሀሳብ የተዋጠ መሆን አለበት፡፡

## 7. መለኮታዊ ዕቅድ ማቀድ

ክርስቲያን መሪ ሁሉን ቻይ ከሆነው ከእግዚአብሔር ትልቅን ነገር መመኘትና መጠየቅ አለበት፡፡ ራዕይ ማለት ከሩቅ ያለውንና ብዙዎች ሊያዩት የማይችሉትን ነገር አቅርቦ የመመልከት ችሎታ እንደሆነ ቀደም ተብሎ ተገልጿል፡፡ ራዕይ ያለው ሰው በሰው ዘንድ የማይቻለውን እግዚአብሔር ይችላል ብሎ ታላቅ እቅድ ያቅዳል፡፡ አንድን ሥራ እግዚአብሔር ብቻ ሠራ ማለት የሚቻለው፣ ሰው የማይችለውን በማቀድ ብቻ ነው፡፡ መለኮታዊው እግዚአብሔር የሚሠራዉ መለኮታዊን ሥራ ነው፡፡ ስለዚህ ክርስቲያን መሪ እግዚአብሔር ራሱ እንዲሠራ የሚያስፈልገውን ሥራ ማቀድን መለማመድ አለበት፡፡ የዚህ ዓይነት እቅድ ደግሞ እግዚአብሔርን ያስደስተዋል፡፡

እ.ኤ.አ. በ1972 ዓ.ም. በአሜሪካን ሀገር በቴክሳስ ግዛት በዳላስ ከተማ 85,000 ሰዎች በአንድ ላይ በአንድ ሥፍራ ለአንድ ሳምንት





የወንጌል ሥርጭትና የደቀመዝሙር ሥልጠና ለመካፈል ተሰብስበው ነበር፡፡ በዚህም ታላቅ ስብሰባ ላይ ዶ/ር ጁን ኪም የሚባሉ አንድ ኮሪያዊ ክርስቲያን መሪ ተገኝተው ነበር፡፡ እርሳቸውም በዳላስ እያሉ ከሁለት ዓመት በኋላ በሀገራቸው በኮሪያ እግዚአብሔር ሊያደርግ ያለውን ነገር በእምነት ከሩቅ ተመለከቱት፡፡ በዚያ ታላቅ የአሜሪካ ስብሰባ ላይ ቆመው "የዛሬ ሁለት ዓመት በደቡብ ኮሪያ በሴውል ከተማ ይህን ለመሰለ ሥልጠና 300,000 ሰዎችን በአንድ ላይ እንሰበስባለን፣ እናንተም ሁላችሁ ለዚህ ሥልጠና እንድትመጡ እጋብዛችኋለሁ፡፡" በማለት በአደባባይ እምነታቸውን ተናገሩ፡፡

ዶ/ር ጁን ኪም የደቡብ ኮሪያ የታላቁ ተልዕኮ አገልግሎት ዳይሬክተር ስለነበሩ ከአሜሪካ ከተመለሱ በኋላ ሠራተኞቻቸውን በሙሉ ሰብስበው እግዚአብሔር የሰጣቸውን ራዕይ አካፈሉ፡፡ የዛሬ ሁለት ዓመት በሴውል ከተማ 300,000 ሰዎችን ለአንድ ሳምንት ለወንጌል ሥርጭትና ለደቀመዝሙርነት ሥልጠና እንሰበስባለን፡፡ ስለዚህ ከዛሬ ጀምረን ሁላችንም ጠንክረን መሥራት አለብን አሏቸው፡፡ ሠራተኞቻቸውም ይህ ራዕይ በፍጹም የማይሞከርና ከቶም የማይቻል እንደሆነ ገለጹላቸው፡፡ እነዚህም ሠራተኞች የዚህ ዓይነቱ ህልም ወይም ቅዠት መሳይ ራዕይና እቅድ ለምን እንደማይቻል ለዶ/ር ኪም ሰባ አምስት ምክንያቶችን በመደርደር አቀረቡላቸው፡፡

ዶ/ር ኪም ግን እግዚአብሔር የሚጠቀምባቸው ታላቅ የራዕይና የእምነት ሰው ስለነበሩ ሠራተኞቻቸው ላቀረቡላቸው ሰባ አምስት ምክንያቶች አልሸነፍ አሉ፡፡ ምክንያቶቹ በሙሉ በዝርዝር በትልቅ ሰሌዳ ላይ ከተጻፉ በኋላ ዶ/ር ኪም ተነስተው በምክንያቶቹ ላይ በትልቅ ቀለም በዮሐ. 14:12 ላይ ያለውን ቃል ጻፉበት፡፡ "እውነት እውነት እላችኋለሁ፣ በእኔ የሚያምን እኔ የማደርገውን ሥራ እርሱ ደግሞ ያደርጋል፡፡ ከዚህም የሚበልጥ ያደርጋል" በማለት የማይቻልበትን ምክንያት ሁሉ ተቃወሙአቸው፡፡

ከዚያ በፊት በዓለም ላይ 300,000 ሰዎች ለሥልጠና በአንድ ሥፍራ ተሰብስበው አያውቁም፡፡ ከዶ/ር ኪም ሠራተኞች የቀረቡትም ምክንያቶች አብዛኞቹ ትክክለኛ ምክንያቶች ነበሩ፡፡ ዶ/ር ኪም ግን በሰው ዘንድ የማይቻል በእግዚአብሔር ዘንድ እንደሚቻል ያምኑ ስለነበር ዝግጅቱን ለብቻቸው ቀጠሉ፡፡ ቀስ በቀስም ራዕዩ ወደ ፍጻሜ መቃረቡን ሲያዩ ከሠራተኞቻቸው አብዛኞቹ ይቅርታ እየጠየቁ ወደ ዶ/ር ኪም ይመለሱ ነበር፡፡

ከሁለት ዓመትም በኋላ በአስደናቂ ሁኔታ ከሰባ ስምንት የዓለም አገሮች የተውጣጡ 323,419 ሰዎች ለአንድ ሳምንት የወንጌል ሥርጭት ስልጠና በሴውል ኮሪያ ተሰበሰቡ፡፡ ለዚህ ሁሉ ህዝብ በሚያስደንቅ ሁኔታ ምግብ ለቁርስ ለምሣ ለእራት ይዘጋጅ ነበር፡፡ ከህዝቡም አንድም ሰው ሳይቀር በተመደበለት የመመገቢያ ሰዓት ምግቡን በልቶ ጨርሶ ለሚቀጥለው ትምህርት በሰዓቱ ይገኝ ነበር፡፡ ከዚህ ታላቅ ታሪካዊ ስልጠና በኋላ በአራት ዓመታት ጊዜ ብቻ የኮሪያ ክርስቲያኖች ቁጥር ከሦስት ወደ ሰባት ሚሊየን ሊያድግ ቻለ፡፡ መለኮታዊ ዕቅድ ማለት እንግዲህ ይህ ነው፡፡

ራዕይህ የሰፋ፣ ዕቅድህም ታላቅ እንዲሆን እግዚአብሔር ይፈልጋል፡፡ ከእግዚአብሔር ታናሽን ነገር አትጠይቅ፡፡ እግዚአብሔር በዘመንህ ታላቅ ሥራ እንዲሠራና ወንጌል በሚያስደንቅ ፍጥነት ለሰዎች ሁሉ እንዲዳረስ ከፈለግህ እቅድህ ከተለመደው የላቀ፣ እግዚአብሔር የሚደሰትበት ዓይነት እንዲሆን ያስፈልጋል፡፡

እግዚአብሔርን ለትልቅ ነገር እመነው፡፡ "ያለ እምነት እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘት አይቻልም፡፡" /ዕብ. 11፡6/፡፡ ራዕ ይህና ዕቅድህ ትልቅ በሚሆንበት ጊዜ፣ ሁሉን የሚችል አምላክ ያስችለኛል ብለህ ትልቅን ሥራ ለመሥራት በምትነሳበት ጊዜ፣ የዕቅድህን ትልቅነት አይተው የሚያሾፉና ሀሳብህን የማይቀበሉ ሰዎች ሊያጋጥሙህ ይችላሉ፡፡ ቢሆንም ግን በእምነት ጸንተህ መቆም ይገባሃል፡፡ በማመንህ እግዚአብሔርን ታስደስታለህ፤ በመጽናትህ ደግሞ ወደ ዓላማህ ፍጻሜ ትደርሳለህ፣ ፍሬውንም ትበላለህ፡፡

ዊሊያም ኬሪ የተባሉ አንድ የእግዚአብሔር ሰው ሲናገሩ "ለእግዚአብሔር ትልቅን ነገር ሞክር፣ ከእግዚአብሔርም ትልቅን ነገር ጠብቅ፡፡" ብለዋል፡፡ አንተ በዘመንህ ለእግዚአብሔር ክብር ምን ለመሞከር ታቅዳለህ? ከእግዚአብሔርስ ምን ትጠብቃለህ?

# 8. በዘላለማዊ አመለካከት መኖር

በምድር ላይ እንድንኖር የተሰጠን ጊዜ እጅግ አጭር መሆኑን ማስተዋል እጅግ ጥበብ ነው፡፡ ይህንን የማያስተውሉ ሰዎች ኑሮአቸውን እንደፈለጉት በመኖር፣ አንድም ዘላለማዊ ዋጋ ያለውን ሥራ ሳይሠሩበት ያልፋሉ፡፡ በራዕይ መኖር ማለት የዛሬው ሥራችን ለነገው የሚያስገኘውን ዋጋና ውጤት እያዩ መኖር ማለት ነው፡፡ ዛሬ የሠራሁት ሥራ ነገ ዋጋ ይኖረዋል ወይስ አይኖረውም



የወንጌል ባለአደራ

ብሎ በመጠየቅ፤ ዋጋ ላለው ሥራ ጊዜያችንን፣ ጉልበታችንንና ገንዘባችንን በሚገባ በመጠቀም መኖር ማለት ነው፡፡

ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ዘላለማዊ ዋጋ ላለው ነገር ቅድሚያ ሰጥቶ በራዕይ የኖረን አንድ ሰው በዚህ ሥፍራ መጥቀሱ አስፈላጊ እንደሚሆን አምናለሁ፡፡ ይህም ሰው አብርሃም ነው፡፡

እግዚአብሔር አብርሃምን ሲጠራው "ከአገርህ ከዘመዶችህም ከአባትህም ቤት ተለይተህ እኔ ወደማሳይህ ምድር ውጣ፡፡ ታላቅ ህዝብም አደርግሃለሁ፣ እባርክሃለሁ" (ዘፍ. 12፡1-3) ብሎት ነበር፡፡ እግዚአብሔር ይህንን የተናገረው ለእኛ ቢሆን ኖሮ፣ የዚህን ዓይነት የተስፋ ቃል ይዘን ከእግዚአብሔር የምንጠብቀው በረከት ምን ሊሆን እንደሚችል በቀላሉ መገመት አያስቸግርም፡፡ "እግዚአብሔር ታላቅ ህዝብ አደርግሃለሁ" ቢለን ኖሮ ምናልባት ጥሩ ቤት መሥራት፣ ጥሩ መኪና መግዛት፣ የተሻለ ሀብት ማከማቸት ሊሆን ይችላል የምንጠብቀው፡፡ በአብርሃም ሕይወት ግን እንደዚህ ዓይነቱን ፍላጎት አንመለከትም፡፡ ምክንያቱም አብርሃም በራዕይ የሚኖር ሰው ነበርና፡፡

ከብዙ ዘመን በኋላ የዕብራውያን መልዕክት ጸሐፊ የአብርሃምን ሕይወት ሲገልጽ እንደዚህ ብሎ ጻፈ፡፡ "አብርሃም የተባለው ርስት አድርጎ ሊቀበለው ወዳለው ሥፍራ ለመውጣት በእምነት ታዘዘ፣ ወዴትም እንደሚሄድ ሳያውቅ ወጣ፡፡ ለእንግዶች እንደሚሆን በተስፋ ቃል በተሰጠው አገር በድንኳን ኖሮ ያን የተስፋ ቃል አብረውት ከሚወርሱ ከይስሐቅና ከያዕቆብ ጋር እንደ መጻተኛ በእምነት ተቀመጠ፡፡ መሠረት ያላትን እግዚአብሔር የሠራትንና የፈጠራትን ከተማ ይጠብቅ ነበርና" /ዕብ. 11፡8-11/፡፡

በዚህ ሥፍራ ከአብርሃም ሕይወት ለሕይወታችን ብዙ ቁም ነገሮችን እንማራለን ብዬ አምናለሁ፡፡ አብርሃምን እግዚአብሔር የራሱን ዓላማና ሀሳብ እንዲያገለግል ሲጠራው አብርሃም ወዴትም እንደሚሄድ ሳያውቅ እግዚአብሔርን ታዞ ወጣ፡፡ ምንም የራሱን ምክንያት ሳያቀርብ ለእግዚአብሔር ጥሪ እሺ አለ፡፡

አብርሃም እግዚአብሔር "ታላቅ ህዝብ አደርግሃለሁ" ብሎ ተናግሮት የነበረ ቢሆንም ታላቅ ለመሆን የራሱን ጥረት አላደረገም፡፡ አብርሃም የራሱ ቤት እንኳ አልነበረውም፡፡ አብርሃም የኖረው በድንኳን ውስጥና እንደ እንግዳ ነበር፡፡ በአብርሃም ዘመን የነበሩ ሌሎች ሰዎች የየራሳቸውን ከተማ ሲመሠርቱ አብርሃም ግን የራሱን ቤትና ከተማ ለመሥራት ፍላጎት አልነበረውም፤ ምክንያቱም የዚህ

ምድር ኑሮው የእንግድነት እንደሆነና መሠረት ያላትና እግዚአብሔር የሠራት ከተማ እንደተዘጋጀችለት ያውቅ ነበርና፡፡

አብርሃም በእምነት ይጠብቅ የነበረውና ራዕዩም ያች እግዚአብሔር የሠራት ከተማ ነበረች፡፡ በራሱ በተወሰነለት ዘመን መኖር ይችል ከነበረው ኑሮና ሕይወት ባሻገር ያለውን የተሻለውን ሕይወት አርቆ ይመለከት ነበር፡፡ ስለዚህም ድንኳኑን ከሥፍራ ሥፍራ ሲያዘዋውር፣ ሲተክልና ሲነቅል አንድም ቀን በእግዚአብሔር ላይ አጉረምርሞ አያውቅም፡፡ ነገር ግን የራዕይ ሰው በመሆን ኖረ፡፡

እግዚአብሔር ሀብት የሰጣቸው ክርስቲያኖች በዘመናችን አንድ ቤት አፍርሰው ሌላ ሲሰሩ፣ ምድር ቤት ያላቸው ፎቅ ሲጨምሩ፣ ፎቅ ያላቸው ደግሞ ምድር ቤት ሲሰሩ፤ ወይንም ደግሞ ከአንድ አካባቢ ይልቅ ወደሚሻል አካባቢ ለመሄድ ሲጥሩ የሚታዩ ቁጥራቸው ጥቂት አይደለም፡፡ ይህ ሁሉ ምርጫ ጊዜያዊና አላፊ እንደሆነ በጭራሽ የዘነጉት ይመስላሉ፡፡ ይህን መዘንጋት ትልቅ ሞኝነት ነው፡፡

አብርሃም ግን ይህን እውነት አልዘነጋውም፤ እንደ እንግዳና እንደ መጻተኛ ኖረ እንጂ፡፡ እግዚአብሔር ሀብት ሲሰጠን የራሱን ፈቃድ እንድናገለግልበት እንጂ ማን እንደሚበላው ሳናውቅ ዝም ብለን እንድናከማች አይደለም፡፡ የእግዚአብሔር ፈቃድ ደግሞ በእያንዳንዱ ትውልድ የወንጌል ተልዕኮ በሚገባ እንዲፈጸም ነው፡፡ ስለዚህ፣ ልክ አብርሃም እንደኖረ እኛም በራዕይ ልንኖር ይገባል፡፡ የወንጌል ባለአደራነታችንን በሚገባ ለመወጣት እንድንችል ለወንጌል ሥራ ገንዘባችንን መስጠት መማር ይኖርብናል፡፡ ራዕይ ባይኖር ህዝብ መረን ይሆናል፡፡ በእያንዳንዱ ቀን ሕይወታችን በራዕይ መኖር እንድንችል እግዚአብሔር ይርዳን፡፡

በራዕይ ለመኖር ስንወስንና የእግዚአብሔርን ዓላማ በሕይወታችን ለመፈጸም ራሳችንን ስንሰጥ እንዲያው ሁልጊዜ የተመቻቸና ሰው ሁሉ እሰይ የሚል ዓይነት ሕይወት መጠበቅ የለብንም፡፡ ራዕይ መከራም አለበት፡፡ የራዕይ ሰው ሆኖ ለመኖር ዋጋን ለመክፈል መዘጋጀትን፣ በመከራ ውስጥ መጽናትንና የእያንዳንዱን ቀን የሕይወት ጉዞ በትዕግስት መቀጠልን ይጠይቃል፡፡

ራዕይ የሚፈጸመው የራዕዩ ባለቤት የሆነውን እግዚአብሔርን በመታመንና ራዕይ የሚያስከፍለውን ዋጋ በመክፈል፣ በታማኝነት ራዕዩን ይዞ በመጓዝ ነው፡፡ ራዕይ በመከራ ሲታጀብ ተስፋ





የምንቆርጥ ከሆነ የራዕዩን ፍሬ ልንበላ አንችልም፡፡ የራዕይ ሰው ሆኖ ለመኖር የሚቻለው ራዕዩ የሚያስከፍለውን ማንኛውንም ዋጋ ለመክፈል በቂ የሆነ የአእምሮ፣ የመንፈስና የስሜት ዝግጅት ሲኖር ነው፡፡ ለወንጌል ዋጋ ለመክፈል እንዴት መዘጋጀት እንዳለብን በሚቀጥለው ምዕራፍ እንመለከታለን፡፡

# ምዕራፍ አሥራ አንድ

## ለወንጌል ዋጋ መክፈል

ወንጌልን ለሰዎች ሁሉ መመስከር ለክርስቲያኖች ሁሉ የተሰጠ ከተልዕኮዎች ሁሉ እጅግ የላቀና የከበረ ተልዕኮ ነው፡፡ ይህን ተልዕ ኮ ለመፈጸም ራሳችንን ለእግዚአብሔርና ለጥሪው ስንሰጥ እጅግ ብዙ ዋጋ ያስከፍላል፡፡ በዘመናት ሁሉ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማገልገል የኖሩ አባቶች የተሰጣቸውን አደራ በታማኝነት ለመጠበቅ ሲሉ አስፈላጊውን ዋጋ ሁሉ ከፍለዋል፡፡ በዚህም በታማኝነት በተከፈለው ዋጋ ምክንያት የወንጌል መልዕክትና ተልዕኮው ከትውልድ ወደ ትውልድ እየተላለፈ አሁን ለዚህ ትውልድ ደርሷል፡፡

ይህም ትውልድ የራሱን ምቾት እየፈለገ፣ የወንጌልን አደራ ለመጠበቅና የተሰጠውን ተልዕኮ ለመፈጸም እየጣረ ዘመኑን በከንቱ ከማሳለፍ ይልቅ ወንጌል የሚያስከፍለውን ዋጋ ከፍሎ ትክክለኛውን የክርስትና ኑሮ መኖር ይጠበቅበታል፡፡ ለወንጌል የኖሩ የእግዚአብሔር ባሪያዎች ወንጌል የሚያስከፍለውን ዋጋ ከፍለው በተሰጣቸው ዘመን እንዴት በትክክል እንደኖሩ የዕብራውያን መጽሐፍ ጸሐፊ ሲጽፍ እንደዚህ ይላል፡-

"... ሌሎችም መዳንን ሳይቀበሉ የሚበልጠውን ትንሣኤ እንዲያገኙ እስከ ሞት ድረስ ተደበደቡ፣ ሌሎችም መዘበቻ በመሆንና በመገረፍ ከዚህም በላይ በእስራትና በወኅኒ ተፈተኑ፣ በድንጋይ ተወግረው ሞቱ፣ ተፈተኑ፣ በመጋዝ ተሰነጠቁ፣ በሰይፍ ተገድለው ሞቱ፣ ሁሉን እያጡ መከራን እየተቀበሉ እየተጨነቁ የበግና የፍየል ሌጦ ለብሰው ዞሩ፣ ዓለም አልተገባቸውምና በምድረ በዳና በተራራ፣ በዋሻና በምድር ጉድጓድ ተቅበዘበዙ" (ዕብ. 11፡35-38)፡፡

ይህ ሁሉ መከራ ለምን ደረሰባቸው? ይህንንስ ሁሉ ዋጋ ለመክፈል እንዴት ቻሉ? ብለን ብንጠይቅ መልሱ ቀላል ነው፡፡ ዋጋ ለመክፈልና የተሰጣቸውን አደራ በታማኝነት ለመጠበቅ መረጡ፡፡ ይህ ዓለም የዘላለም ቤታቸው እንዳልሆነ ገብቷቸዋል፡፡

ከዚህ ዓለም የሚሻል የዘላለም ቤት እንደሚጠብቃቸውና ለዚያ ለሚሻለው መኖር እንዳለባቸው በሚገባ አውቀዋል፡፡ ጥቂት ጊዜ በዓለም ታውቀው ለዘላለም ከመረሳት ይልቅ ጥቂት ጊዜ በዓለም ተረስተው ለዘላለም መታወቅን መረጡ፡፡

ከራሳቸው ምቾት ይልቅ የአምላካቸውን ፈቃድ ለመፈጸም ነፍሳቸውን በፈቃዳቸው ሰጡ፡፡ ከዚህም የተነሳ በዓለም ላይ ሀብት አከማችተው፣ ዝና አትርፈውና እጅግ ገናና ሆነው ካለፉቱ ይልቅ ታሪካቸውና ስማቸው ለዘላለም ይኖራል፡፡ ምክንያቱም ከጊዜያዊው ይልቅ ዘላለማዊውን መርጠዋልና፡፡ ከሚታየው ይልቅ ለማይታየው በሕይወታቸው ቅድሚያ ሰጥተዋልና፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስም ሆነ በቤተክርስቲያን ታሪክ ለወንጌል ዋጋ ከፍለው የኖሩ ምሳሌዎቻችን የሚሆኑ የወንጌል ባለአደራዎች እጅግ ብዙ ናቸው፡፡

በዘመናችን ግን ወንጌልን መስበክና የግል ምቾትን መጠበቅ ጎን ለጎን እንዲሄዱ ከመፈለጋችን የተነሣ የወንጌል ትርጉም የጠፋብን ብዙዎች ነን፡፡ ከገጠር ይልቅ ከተማን፣ ጥቂት ህዝብ ከተሰበሰበበት ይልቅ ትልቅ ጉባዔ፣ ከኢትዮጵያ ይልቅ አውሮፖና አሜሪካ ወዘተ... ማገልገል ምርጫችን የሚሆን ብዙዎች ነን፡፡

ስለሆነም ወንጌልን መስበክ መደበኛ ሥራን ከመሥራትና ለእንጀራ ከመኖር ተለይቶ የማይታይበት ጊዜ ደርሰናል፡፡ ከተመቸን እንሰብካለን፣ ካልተመቸን ደግሞ ዋጋ ከፍለን ቁም ነገር ለመሥራት ስለማንወድ ይህ አጭሩ ዘመናችን እንዲሁ በከንቱ ያልፍብናል፡፡ በዚህ ጊዜ ለወንጌል የኖሩ ሰዎች እንዴት ኖሩ የሚለውን ለመረዳት ጥቂት የመጽሐፍ ቅዱስ ምሳሌዎችን ማየቱ ጠቃሚ ስለሚሆን የአብርሃምን፣ የሙሴንና የጳውሎስን ሕይወት ባጭሩ ከዚህ ቀጥሎ አቅርቤአለሁ፡፡

## 1) አብርሃም

አብርሃም የወንጌል ሰው እንደነበር ቀደም ብለን ተመልከተናል፡፡ ይህ ሰው የወንጌል ሰው ተብሎ ሊጠራ እንዴት እንደቻለ መረዳት እጅግ አስፈላጊ ይሆናል፡፡ የወንጌል ሰው ተብሎ ለመጠራት የወንጌል ሰው ሆኖ መኖር አስፈላጊ እንደሆነ ከአብርሃም ሕይወት በሚገባ እንረዳለን፡፡

የዕብራውያን መጽሐፍ ጸሐፊ ስለ አብርሃም ሕይወት አጠር ያለ ማጠቃለያ ሲሰጥ እንዲህ ይላል፡- "አብርሃም የተባለው ርስት አድርጎ





ሊቀበለው ወዳለው ስፍራ ለመውጣት በእምነት ታዘዘ፣ ወዴትም እንደሚሄድ ሳያውቅ ወጣ፡፡ ለእንግዶች እንደሚሆን በተስፋ ቃል በተሰጠው አገር በድንኳን ኖሮ፣ ያን የተስፋ ቃል አብረውት ከሚወርሱ ከይስሐቅና ከያዕቆብ ጋር እንደ መጻተኛ በእምነት ተቀመጠ፣ መሠረት ያላትን እግዚአብሔር የሠራትንና የፈጠራትን ከተማ ይጠብቅ ነበርና" (ዕብ. 11፡8-10)፡፡

አብርሃም የወንጌል ሰው ሆኖ ሊኖር የቻለበት በሁለት ዋና ዋና ምክንያቶች እንደሆነ አስባለሁ፡፡ የመጀመሪያው ምክንያት እግዚአብሔር አብርሃምን "ከአገርህ ከዘመዶችህም ከአባትህም ቤት ተለይተህ እኔ ወደማሳይህ ምድር ውጣ" (ዘፍ. 12፡1) ሲለው "አብርሃምም እግዚአብሔር እንደነገረው ሄደ" (ዘፍ. 12፡4)፡፡ እግዚአብሔር ሂዱ ብሎ ካዘዘን ትክክለኛው ምላሽ መሆን ያለበት መታዘዝና መሄድ ብቻ ነው፡፡ እግዚአብሔር ለወንጌል ሥራ ራስህን ስጥ፣ እንጀራ የምታገኝበትን ሥራህን እንኳ ልቀቅ፣ እኔ ወደምልክህ ሥፍራ ሁሉ ሂድ፣ ለወንጌል ሥራ ገንዘብህን ጊዜህንና ዕውቀትህን ስጥ ብሎ ካዘዘህ ትክክለኛው ምላሽ "እሺ" ማለትና መስጠት ብቻ ነው፡፡

አንተ ለእግዚአብሔር ስትታዘዝ እግዚአብሔር ደግሞ ለአንተ የሚያስፈልግህን ሁሉ ያዘጋጃል፡፡ /ማቴ. 6፡33/ እግዚአብሔር አንተን የሚያሳይበት መንገድና የሚመራበት አመራር ሁሉ መልካም ነው፡፡ አብርሃም እግዚአብሔር ሲያዘው በመታዘዝ የእግዚአብሔርን አመራር ተከትሎ ሄደ፡፡ የወንጌል ሰው ለመሆን የእግዚአብሔርን ድምጽ መታዘዝ ያስፈልጋል፡፡

አብርሃም የወንጌል ሰው ሊሆን የቻለበት ሁለተኛው ምክንያት አብርሃም እግዚአብሔር በሰጠው የተስፋ አገር ልክ እንግዳ እንደሚኖር በድንኳን ኖረ፡፡ እግዚአብሔር "ታላቅ አደርግሃለሁ ብሎኛል" በማለት በምድር ላይ ታላቅ ለመሆን በመሞከር፣ የራሱን ቤትና ከተማ በመሥራት አልኖረም፡፡ ነገር ግን ከዚህ የተሻለውን እየናፈቀ ኖረ፡፡ "መሠረት ያላትን እግዚአብሔር የሠራትንና የፈጠራትን ከተማ ይጠብቅ ነበርና"፡፡

ዛሬ በኑሮአችንና በሕይወታችን ቅድሚያ የምንሰጠው ለምን ይሆን? አንዳንድ ክርስቲያኖች በኑሮአቸው መርካት ስላልቻሉ ከዓመት ዓመት የተሻለ ኑሮ ፍለጋ መሥሪያ ቤታቸውን እንደለዋወጡ፣ አካባቢን እንደቀያየሩ፣ ከአገር ወደ አገር እንደተንከራተቱ መቼም የትም የፈለጉትን ዓይነት የተሻለ እርካታ ሳያገኙ ይኖራሉ፡፡

እውነተኛ ሰላምና እርካታ የሚገኘው ግን ለእግዚአብሔር ፈቃድ በመታዘዝ፣ እግዚአብሔርን የሚያስደስተውን በማድረግ ለመኖር ራስን በመስጠት እንደሆነ አላወቁም፡፡ አሊያም ደግሞ አውቀውም ሊኖሩ አልቻሉም፡፡ የወንጌል ሰው ተብለን ለመጠራትና በእግዚአብሔር ፊት "አንተ በጎና ታማኝ ባሪያ" ለመባል ወንጌል የሚያስከፍለውን ማንኛውንም ዋጋና መስዋዕትነት ከፍለን ለመኖር ፈቃደኛ መሆን ያስፈልጋል፡፡

## 2) ሙሴ

የወንጌል ሰው ሆኖ ለመኖር ትክክለኛን ምርጫ የመረጠው ሌላው የእግዚአብሔር ሰው ሙሴ ነው፡፡ ሙሴ የራሱን ምርጫ ማድረግ ወደሚችልበት ዕድሜ በደረሰ ጊዜ በፊቱ ሁለት ትላልቅ ምርጫዎች ነበሩት፡፡ ከሁለቱም ምርጫዎች አንዱን መምረጥ ነበረበት እንጂ ሁለቱንም ምርጫ በአንድ ጊዜና በአንድ ላይ ይዞ መጓዝ አይችልም ነበር፡፡ እነዚህም በፊቱ የነበሩ ሁለት ምርጫዎች የግብፅ ሰው በመሆን በግብፅ ምድር የሚጠብቀው ሥልጣን ወይም የእግዚአብሔር ሰው በመሆን ከእግዚአብሔር ህዝብ ጋር መከራን መቀበልና ስለ ክርስቶስ መነቀፍ፡፡

ሙሴ ግን ምርጫው ምን እንደነበረ በመጽሐፍ ቅዱስ ተጽፎለታል፡፡ "ሙሴ ካደገ በኋላ የፈርዖን የልጅ ልጅ ተብሎ መጠራትን እምቢ ያለው በእምነት ነው፤ ስለዚህም በኃጢአት ከሚገኘው ጊዜያዊ ደስታ ይልቅ ከእግዚአብሔር ሕዝብ ጋር መከራ መቀበልን መረጠ፡፡ ወደፊት የሚቀበለውን ሽልማት ስለ ተመለከተ፣ ከግብፅ ሀብት ይልቅ ስለ መሲሕ (ክርስቶስ) መዋረድ የበለጠ ሀብት መሆኑን አሰበ፡፡ ..... የማይታየውንም አምላክ እንዳየው ያህል ሆኖ በዓላማው ጸና፡፡" (ዕብ. 11፡24-27፣ አዲሱ ትርጉም፡፡)

ሙሴ ከጊዜያዊው ይልቅ ዘላለማዊውን፣ ከሚታየው ይልቅ የማይታየውን፣ ከራሱ ምኞት ይልቅ የእግዚአብሔርን ፈቃድ መፈጸምን መረጠ፡፡ ይህንንም በመምረጡ ምክንያት የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማገልገል የሚያስከፍለውን ዋጋ ሁሉ ከፍሏል፡፡





## 3) ጳውሎስ

ጳውሎስ በደማስቆ መንገድ ሕይወቱ ከተለወጠበት ጊዜ ጀምሮ እስከ ሕይወቱ ፍጻሜ ድረስ የኖረው ለወንጌል ነበር፡፡ ወንጌል የሚጠይቀውንም ዋጋ ሁሉ እንደሚገባ በመክፈል ኖሯል፡፡ የከፈለውም ዋጋ ምን ይመስል እንደነበር ሐዋሪያው ጳውሎስ በራሱ አንደበት እንደሚከተለው ይናገራል፡፡ "... ብዙ ጊዜ በሥራ ደክሜአለሁ፣ ብዙ ጊዜ ታስሬአለሁ፣ ብዙ ጊዜ ተገርፌአለሁ፣ ብዙ ጊዜ በሞት አደጋ ላይ ተገኝቻለሁ፣ ሠላሳ ዘጠኝ ጅራፍ አምስት ጊዜ በአይሁዳውያን ተገርፌአለሁ፣ ሦስት ጊዜ በዱላ ተደብድቤአለሁ፣ አንድ ጊዜ በድንጋይ ተወግሬአለሁ፣ ሦስት ጊዜ የመርከብ አደጋ ደርሶብኛል፣ አንድ ሌሊትና አንድ ቀን በባሕር ላይ ነበርሁ፣ በጉዞዬ ብዛት የወንዝና የጉርፍ፣ የሽፍቶች አደጋ ደርሶብኛል፣ በከተማና በበረሃ በባሕርም አደጋ ደርሶብኛል፣ እንዲሁም ከሐሰተኞች አማኞች አደጋ ደርሶብኛል፡፡ ብዙ ሥራና ድካም ነበረብኝ፣ ብዙ ጊዜ እንቅልፍ አጥቻለሁ፣ በረሃብና በውሃ ጥም ተጨንቄአለሁ፣ ብዙ ጊዜ የምግብ እጦት ደርሶብኛል፣ ብርድና መራቆትም ደርሶብኛል፡፡" (2ቆሮ. 11፡23-27፣ አዲሱ ትርጉም፡፡)

የወንጌል ባለአደራ ማለት እንግዲህ ይህ ነው፡፡ ወንጌላዊ ለመባል የወንጌልን መልዕክት ተሸክሞ መዞር፣ ታማኝ ለመባል ታማኝ ሆኖ መገኘት፣ ወንጌል የሚያስከፍለውን ዋጋ ሁሉ ለመክፈል ራስን መስጠት፡፡ ሐዋሪያው ጳውሎስ በዘመኑ የወንጌልን አደራ እንደሚገባ የተወጣ የወንጌል ሰው ነበር፡፡ ኃላፊነቱንም ሊወጣ የቻለው በበረሃ፣ በባሕር፣ በከተማ፣ በገጠር፣ በወንዝ፣ በጫካ በመንከራተት እንጂ ተመችቶት አልነበረም፡፡ የተመቸውና እርካታን የሰጠው ነገር ቢኖር ከአምላኩ ጋር መሆኑና ማንኛውንም ዋጋ ከፍሎ የአምላኩን ፈቃድ በሕይወቱ ዘመን መፈጸም መቻሉ ነው፡፡

ከዚህ በላይ ያየናቸውን ሦስቱን የወንጌል ሰዎች፣ እንዲሁም የወንጌል ባለ አደራነታቸውን በታማኝነት የፈጸሙትን የሌሎች የእግዚአብሔር ባሪያዎች ሁሉ ሕይወት ልዩ የሚያደርገው ነገር ለወንጌል ዋጋን ለመክፈል ፈቃደኞች መሆናቸው ነው፡፡

በየዘመናቸው ሁሉ የኖሩ የወንጌል ባለአደራዎች ራሳቸውን መሥዋዕት አድርገው እንደኖሩና የወንጌልን ተልዕኮ እንደፈጸሙ ሁሉ እኛም በዘመናችን እግዚአብሔር የሚጠብቅብንን ሁሉ

ልንፈጽም ይገባናል፡፡ ይህንንም ለመፈጸም የምንችለው ታማኝነት የሚጠይቀውን ዋጋ ሁሉ ለመክፈል ስንቆርጥ ብቻ ነው፡፡

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር ላይ በኖረበትና ባገለገለበት ጊዜ ሁሉ በሕይወቱ ቅድሚያ ሰጥቶ የኖረውና በመጨረሻም ሕይወቱን መሥዋዕት ያደረገው ለወንጌል ነበር፡፡ በምድር ላይ የነበረውንም ተልዕኮውን ፈጽሞ ወደ ሰማይ ያረገውና በአብ ቀኝ የተቀመጠው እርሱ በምድር ላይ የጀመረውን ሥራ እኛ እንድንቀጥል ለእኛ አደራ ሰጥቶ ነው፡፡ እርሱ ዋጋ ከፍሎ እንደፈጸመ ሁሉ እኛም ዋጋ ከፍለን ሥራውንም እንድንጀምርና እንድንፈጽም ይጠብቀናል፡፡ ከጌታ ይህንን አደራ የተቀበልን እኛ ክርስቲያኖች አደራውን ቸል ብንል እንኳ እግዚአብሔር ከዚህ ሌላ የተለየ ዕቅድ የለውም፡ ሰነፎች ወይም ትጉህ ሠራተኞች ብንሆን እግዚአብሔር ሥራውን እንድንሠራለት የሚጠብቀው እኛኑ ነው፡፡

በእርግጥም ክርስቶስ እኛን ከማመንና ከመላክ የተለየ ዕቅድ የለውም፡፡ ዛሬም የሚጠብቀው እኛ እንድንሄድለት፣ የምሥራቹን ለሰው ልጆች ሁሉ እንድናደርስና በዘመናችን የሚጠበቅብንን ሩጫ እንደሚገባ ሮጠን የወንጌልን ችቦ ለሚቀጥለው ትውልድ እንድናስተላልፍ ነው፡፡

ለዓላማ መኖርን ጥቅም ያወቁና በሕይወታቸው ትክክለኛ ምርጫ የመረጡ ሰዎች እጅግ የታደሉ ናቸው፡፡ ከንቱና ጊዜያዊ የሆነውን የምድራዊ ሕይወታቸውን ዋጋ ላለውና ዘላለማዊ ለሆነው ነገር ያስገዙ ሁሉ እጅግ ጥበበኞች ናቸው፡፡ በታሪክ ውስጥ ይህን እውነት አጥብቀው ከተረዱና መልካም ምርጫ ከመረጡ ሰዎች መካከል የሦስት ሰዎችን አስደናቂ የሕይወት ምሳሌነት ቀጥሎ ለማቅረብ ሞክሬአለሁ፡፡

## ሀ) ወርቅ ቆፋሪው በኤርዬ ሐይቅ

አንድ ጊዜ በካናዳና በአሜሪካ ግዛት መካከል በሚገኝ ኤሪዬ በሚባል ሐይቅ ላይ በነበረውና በእንፋሎት ኃይል በሚሠራው ጀልባ ላይ እሳት ተነሣ፡፡ ስለዚህም በጀልባው ላይ የነበሩ ሰዎች በቅርቡ ወደሚገኝ የብስ ለመድረስና ነፍሳቸውን ለማዳን ብርቱ ትግል ማድረግ ጀመሩ፡፡ ነገር ግን እሳቱ እያየለ በመሄዱ በጀልባው ላይ ትልቅ መደናገር፣ ግርግርና ሽብር ተፈጠረ፡፡ በዚያ ጀልባ ላይ ከነበሩ ሰዎች መካከል አንዱ ከካልፎርኒያ ግዛት የመጣና ዕድሜውን በሙሉ ወርቅ በመቆፈር በዚህ ሐይቅ አካባቢ ያሳለፈ ሰው ነበር፡፡



የወንጌል ባለአደራ

እሳቱ በጀልባው ላይ በሚነሳበት በዚህ ጊዜ በብዙ ልፋትና ድካም ያጠራቀመውን የወርቅ ክምችት ይዞ ይጓዝ ነበር፡፡ እርሱም በዚህ ትርምስ መካከል እጅግ ብዙ ዋጋ ያለውን ወርቁን በጥንቃቄ በቀበቶው በወገቡ ላይ በማሰር በዋና ወደ መሬት ለመድረስ ራሱን ወደ ውኃ ሊወረውር ተዘጋጀ፡፡

ልክ ወደ ውኃ ከመዝለሉ በፊት አንዲት የምታምር ትንሽዬ ልጅ ፈጠን ብላ ቀረበችና እጁን ዳሰሰችው፡፡ እርስዋም በመለማመጥ ፊቱን ተመለከተችና "ጋሽዬ ራስህን ብቻ ነው የምታድነው? እኔን አታድነኝም? እንዳያድኑኝ አባባም እማማም የሉኝም፣ እባክህን ከዚህ እሳት አድነኝ" ስትል ለመነችው፡፡

የወርቅ ቆፋሪው በዚህን ጊዜ ምን ያድርግ? ዕድሜ ልኩን ሲለፋና ሲጥር ያካበተውን የወርቅ ጥሪቱን ወደ ማዶ ያሻግረው ወይስ ይህችን ልጅ? ሁለቱን በአንድ ጊዜ ማዳን አይችልም፡፡ ይህ ሰው በዚያች ቀውጢ ቅጽበት አንዱን ለማንሳት፣ ሌላውን ለመጣል መምረጥ ነበረበት፡፡ ኑሮውንና ትዳሩን ይጣል ወይስ ልጅቷን? የተለያየ ሀሳብ በአእምሮው ተመላለሰ፡፡ ወዲያውኑ ጊዜ ሳያጠፋ መወሰን ነበረበት፤ ወርቁን ለመጣል፣ ልጅቷን ለማሻገር፡፡ ወደ ውኃም ዘለለ፣ ከዚያም የነፍስ አድን ዋናውን ተያያዘው፡፡ ወደ የብስም ደረሰ፡፡

ያኔም ይህች ትንሽዬ ልጅ በድካም በዛለው ክንዱ ላይ ተደግፋ እጅግ እንባ ስታፈስ ተመለከታት፡፡ "ወርቅህን ጥለህ እኔን ከእሳት ያዳንክ ባለውለታዬ ነህ አለችው፡፡" እርሱም "ለካስ የሰው ሕይወት እንደዚህ ውድ ናት?" አለ፡፡ የሕይወት ዘመኑን ድካምና ልፋት ጣለ፣ ይህችን ውድ ሕይወት ግን አዳነ፡፡ ይህን በማድረጉም አዲስ የሕይወት ተስፋ በውስጡ ለመለመ፡፡

ዛሬም ብዙ ትርምስ፣ ሽብር፣ ግርግርና መደናገር ከሞላበት ዓለም ውስጥ "ጋሽዬ ራስህን ብቻ ነው የምታድነው? እኔንስ አታድነኝም?" የሚል የብዙ ሰዎች ድምፅ በዝምታ ውስጥ ወደ አንተ ይመጣል፣ ወደ ጆሮህም ይገባል፡፡

ከጌታ ጋር ሆነህ እነዚህን ሰዎች ማዳን ትችላለህ፡፡ ነገር ግን ምርጫ ማድረግ አለብህ፡፡ ብርና ወርቅህን ለመጣል፣ ለዘላለም ሕይወት ሰዎችን ለማዳን፡፡ ሕይወታችንም ኑሮአችንም ለጌታ ክብርና ለነፍሳት ደህንነት መዋል አለበት፡፡ ያኔ በእኛ ምክንያት፣ እኛ ዛሬ ገንዘባችንን በመስጠታችን ምክንያት፣ ሰዎችን ከዘላለም

ሥቃይ ለማዳን ምርጫ በማድረጋችን ምክንያት፣ የዳኑት ሰዎች በሰማይ በጌታችን ፊት ስንቆም "ጌታ ሆይ ይህ ሰው ሕይወቴን ከእሳት ያዳነ ባለውለታዬ ነው" ሲሉ እንሰማቸዋለን፡፡

በዚያን ጊዜ ጌታችንም መልሶ "መልካም፣ አንተ በጎ ታማኝም ባሪያ" ይለናል፡፡ (ማቴ. 25፡23) ስለዚህም ነው ጠቢቡ ንጉሥ ሰለሞን "እንጀራህን በውኃ ላይ ጣል፣ ከብዙ ቀንም በኋላ መልሰህ ታገኘዋለህ" (መክ. 11፡1) በማለት የሚመክረን፡፡ እርግጥ ነው እንጀራን በውኃ ላይ ስንጥል መልሰን የምናገኝ አይመስለንም፡፡ ነገር ግን በእግዚአብሔር ዘንድ ሁሉ ይቻላል፣ መልሰንም እናገኘዋለን፡፡

እግዚአብሔር ከእኛ የሚፈልገው "እንጀራህን በውሃ ላይ ጣል" ሲለን በመታዘዝ መጣልን ብቻ ነው፡፡ እንዴት መልሼ አገኘዋለሁ ብለን እግዚአብሔርን መጠየቅ መብታችን አይደለም፡፡ መጣል ግን መብታችን ነው፡፡ መበተንና ለምስኪኖች መስጠት እግዚአብሔር ከእኛ የሚጠብቀው ተግባር ሲሆን ጽድቃችንን ለዘላለም ማኖርና ዛሬ የጣልነውን ነገር ነገ ፍሬ አድርጎ መልሶ መስጠት የእግዚአብሔር ተግባር ነው፡፡ ስንጥልና ስንበትን ደግሞ የእግዚአብሔር ቃል እንደሚመክረን "በደስታ እንጂ በኀዘን ወይም በግድ አይደለም" (2ቆሮ. 9፡6-9)፡፡

ዛሬ ወንጌል ለሰዎች እንዲደርስ እግዚአብሔር ገንዘብህን እንድትሰጥ ይፈልጋል፡፡ አንተ ሕይወት ያገኘኸው ጌታ ኢየሱስ ነፍሱን በመስጠቱ መሆኑን መዘንጋት የለብህም፡፡ ገንዘብ ተጨማሪ ሳገኝ እሰጣለሁ አትበል፣ እግዚአብሔር ለአንተ የሰጠው አንድያ ልጁን ነው፡፡ በትክክል የሚያገለግል ቤተክርስቲያን፣ መንፈሳዊ አገልግሎት ወይም የወንጌል አገልጋይ ሳገኝ እሰጣለሁ አትበል፡፡ ክርስቶስ ለእኔና ለአንተ የሞተው እኛ ገና ክፉዎች ሆነን ሳለ ነው፡፡ ስለዚህ ገንዘብህን ለወንጌል አገልግሎት ስጥ፣ የምትሰጥበትም ጊዜ አሁን ነው፡፡ ዋጋ የሚገኘው ዋጋ ስትከፍል ብቻ ነው፡፡

## ለ) ሐውልት ሠሪው በፓሪስ ከተማ

በፈረንሳይ አገር በፓሪስ ከተማ ፋይን አርትስ ጋለሪ በሚባል ሙዚየም ውስጥ አንድ በጣም የሚደነቅና ዝነኛ ሀውልት አለ፡፡ ሀውልቱ የተሠራው በጣም ዝነኛ በሆነ ሰው ነበር፡፡ ግን ሰውዬው ሕይወቱን ሁሉ የኖረው በድህነትና በጉስቁልና ነው፡፡ ማደሪያውም





ሳሎኑም መሥሪያ ቤቱም አንዲት ጠባብና በጭቃ የተሠራች ጎጆ ነበረች፡፡ ከዕለታት አንድ ቀን እኩለ ሌሊት ላይ ታላቅ ውርጭ በፓሪስ ላይ ወደቀ፡፡

ይህም ዕለት ይህ ሰው በሕይወት ዘመኑ ያለመለት ይህ ሀውልት ገና የተጠናቀቀበት ዕለት ነበር፡፡ ይህም ያልደረቀው ሀውልት በእሳት አልባው የጭቃ ቤት በፊቱ ተጋድሞ ነበር፡፡ ይህ ውርጭ የሕይወት ዘመኑን ድካም በዚያች ሌሊት ሊያጠፋ ሆነበት፡፡ ስለዚህም ይህ ሰው ያለውን ኮቱንና የሌሊት ልብሱን ሁሉ አምጥቶ ሀውልቱን በደንብ ከሸፈነ በኋላ እርሱ እንቅልፉን ተኛ፡፡

በጧት ጎረቤቶቹ ሰውዬውን ሞቶ አገኙት፣ ሀውልቱ ግን ተረፈ፡፡ ሕይወቱን ለሀውልቱ ሰጠ፡፡ ሀውልቱ ዳነ፣ እርሱ ግን ሄደ፡፡ የሰውዬው ታሪክና ዝና ዛሬም በሀውልቱ ውስጥ አለ፡፡ ለኑሮውና ለሕይወቱ አልሳሳም፣ ነገር ግን በሥራው ውስጥ አዲስ ሕይወትን አገኘ፡፡

ሰዎች የዘላለም መታሰቢያ ለሌለው ነገር እንደዚህ ይጨክናሉ፡፡ እኛስ በክርስቶስ ደም ከኃጢአታችን ታጥበን ለእርሱ መንግስትና ካህናት እንድንሆን የተዋጀን የዘላለም መታሰቢያ በመንግስተ ሰማያት ለማኖር እንዴት አንጨክንም? የሰው ሕይወት በወንጌል ምክንያት ከዳነ እኛ ደግሞ ለወንጌል ብራችንም ወርቃችንም ሕይወታችንም እንዲሄድ ለምን አንፈቅድም?

ለወንጌል ሥራ ገንዘብ ስጡ በሚባሉበት ጊዜ ገንዘባቸውን፣ ወርቃቸውን ንብረታቸውን ሳይሰስቱ የሚሰጡ እነርሱ በእግዚአብሔር መንግስት መታሰቢያን የማስቀመጥና ለወንጌል የመኖር ትርጉም የገባቸው ናቸው፡፡ ይህ ትርጉም ያልገባቸው ግን ለወንጌል ሥራ ገንዘብ መስጠት ሳይጀምሩ ይሞታሉ፣ ጌታቸውንም ለመገናኘት ይሄዳሉ፡፡ ከጌታ ጋር ፊት ለፊት ሲገናኙ ምን ይሰማቸው ይሆን?

## ሐ) ሻማ አብሪዋ በሰሜን እስኮትላንድ

በሰሜን እስኮትላንድ በአከኔይ ደሴት በአንድ ባህር አጠገብ በምትገኝ ደሳሳ ጎጆ መስኮት አጠገብ ሁል ጊዜ ማታ ማታ ሌሊቱ እስከሚነጋ ድረስ አንዲት ሻማ ትበራለች፡፡ ይህንንም ሻማ የሚያበሩት ፀጉራቸው ሁሉ ሽበት የሆነ ነገር ግን እጅግ ደስተኛ የሆኑ አንዲት አሮጊት ሴት ናቸው፡፡ ሰው ሁሉ በተኛበት ሰዓት በእኩለ ሌሊት ጥጣቸውን እየፈተሉ ነፋሱ የሻማውን መብራት

እንዳያጠፋው ወዲያና ወዲህ እየዞሩ ነፋስ በሚነፍስበት በኩል ሁሉ ከነፋሱ ይከላከሉታል፡፡ ሌሊቱን በሙሉ ጥጣቸውን እየፈተሉ የሻማዋን ብርሃን ይጠብቃሉ፡፡ በባህሩ ላይ ዓሣ ለሚያጠምዱ ሰዎች ይህች በደሳሳ ጎጆ ውስጥ ያለችዋ ትንሿ የሻማ ብርሃን ሕይወታቸውን ከአደጋ የምታድን ትልቅ ቁም ነገር ናት፡፡

እኚህ አሮጊት ሴትዮ ይህችን ትንሽ ሻማ እንዳትጠፋባቸው ከ50 ዓመታት በላይ በየሌሊቱ ጠብቀዋታል፡፡ ይህንንም የሻማ ብርሃናቸውን ለሌሎች መስጠት የጀመሩት በዚህ ምክንያት ነው፡፡ እሳቸው ወጣት በነበሩበት ጊዜ አባታቸው በሌሊት በጨለማ፣ በዚህ ባህር ዓሣ በሚያጠምዱበት ጊዜ ማዕበል በመነሳቱ ወዴት አቅጣጫ እንደሚሄዱ ባለማወቃቸው ጀልባው ከትልቅ ድንጋይ ጋር በመጋጨቱ ምክንያት ጀልባው ሰጥሞ እሳቸውም ሞተው ያድራሉ፡፡ በነጋም ጊዜ የአባታቸው አስከሬን በባህሩ ዳር ተገኘ፡፡ በባህላቸውም መሠረት አስከሬን እስከሚቀበር ድረስ ሰው ስለሚያየው የአባታቸውን በድን አካል እስኪቀበር ድረስ ተመለከቱት፡፡

ከዚያም በኋላ አልጋቸውን አነጠፉና በቀን እንቅልፋቸውን ተኙ፡፡ በመሸም ጊዜ ከእንቅልፋቸው ነቁ፣ ትንሽ ሻማ አብርተው የጎጆው መስኮት አጠገብ አስቀመጡ፣ ከዚያም ጥጣቸውን መፍተል ጀመሩ፣ በባህር ላይ ዓሣ ለሚያጠምዱ ለማያውቋቸው ሰዎች ሕይወት ሲሉ ሻማውን እየጠበቁ ሌሊቱን ቁጭ ብለው አደሩ፡፡

ሌሊቱን በሙሉ፣ ሕይወታቸውን በሙሉ፣ የዚህች ሴት ፍቅርና የሻማቸው ብርሃን አንድም ቀን አልተቋረጠም፡፡ ከወጣትነታቸው እስከ እርጅናቸው፣ በበጋና በክረምት፣ ባህሩ ጸጥ ቢል ማዕበል ቢነሳበት፣ ጭጋግ ቢሸፍነው ወይም የጠራ ሰማይ ቢሆን እኚህ ሴት የሻማ ብርሃናቸውን አቋርጠው አያውቁም፡፡

በእያንዳንዱ ሌሊት ብዙ ጥጥ ይፈትላሉ፡፡ የፈተሉትን እየሸጡ በሚያገኙዋት አነስተኛ ገንዘብ ዳቦና ሻማ ይገዛሉ፡፡ ዳቦውን ለመብላት ሻማውን ለማብራት፡፡ እርሳቸውም ቀኑን ሌሊት፣ ሌሊቱን ቀን አድርገው የሕይወታቸውን አቅጣጫ ለወጡት፡፡ ኑሮአቸውን በሙሉ ሌሎችን ለማዳን አሳልፈው ሰጡ፡፡ በዚህች ትንሽ የሻማ ብርሃን ምክንያት ብዙዎች ከሞት ተርፈዋል፡፡ እግዚአብሔርንም ስለዚህች ትንሽ ሻማ ምክንያት ብዙዎች አመስግነዋል፡፡ ለእኚህም ሴት መታሰቢያ ተጽፎላቸዋል፡፡ ይህም ታሪክ በሚነገርበት ሥፍራ ሁሉ ታሪካቸውና የከፈሉት ዋጋ ይነገርላቸዋል፡፡





አንተም ሌሎች እንዲድኑ ሻማህን አብራ፡፡ በአገልግሎትህና በመታዘዝህ ምክንያት ከዘላለም ሞት የተረፉ ሰዎች በእግዚአብሔር ፊት ተሰብስበው እንዲያመሰግኑህ ዛሬ ሻማህን አብራ፡፡ የአንተ ትንሿ ሻማ ሌሎች እንዲድኑ፣ ሌሎች እግዚአብሔርን እንዲያመሰግኑ የምታደርግ ከሆነ ሻማህን አብራ፡፡

ለሰዎች የወንጌልን የምሥራች የማወጅህን ሻማ አብራ፡፡ ለወንጌል ሥራ ገንዘብ የመስጠትህን ሻማ አብራ፡፡ "ከሁሉ ከሚያንሱ ከእነዚህ ወንድሞቼ ለአንዱ እንኳ ስላደረጋችሁት ለእኔ አደረጋችሁት" (ማቴ. 25፡40) እንድትባል ያለህን ለሌሎች የማካፈል ሻማህን አብራ፡፡ የታማኝነትና የእውነት ሻማህን አብራ፡፡ መታሰቢያህንም በእግዚአብሔር ፊት ታገኛለህ፡፡

እንግዲህ ለወንጌል መኖር ምርጫን ይጠይቃል፡፡ ለዘላለማዊው ለመኖር መምረጥን፣ ከሁሉ ይልቅ የሚሻለውን መምረጥን፣ ዋጋ ለመክፈል መምረጥን፣ ያለህንና የምትችለውን በማድረግ የሌሎችን ሕይወት ለማትረፍ ለመኖር መምረጥን ይጠይቃል፡፡

ስለዚህ አንተም ባለህ በዚህ በአጭሩ የሕይወት ዘመንህ ከሁሉ ይልቅ የሚበልጠውን ምረጥ፡፡ ለወንጌል መኖርን ምረጥ፣ ወንጌል የሚያስከፍለውን ዋጋ እየከፈልክ መኖርን ምረጥ፡፡ ይህንንም በማድረግህ የእግዚአብሔርን ሀሳብ በዘመንህ ታገለግላለህ፡፡

# ምዕራፍ አሥራ ሁለት

## የእግዚአብሔርን ሀሳብ ማገልገል

እያንዳንዱ ክርስቲያን የእግዚአብሔርን ሀሳብ እንዲያገለግል ተጠርቷል። ደግሞም እያንዳንዱ ክርስቲያን የእግዚአብሔርን ሀሳብ ለማገልገል ይፈልጋል። ለመሆኑ የእግዚአብሔር ሀሳብ ምንድር ነው? የእግዚአብሔርንስ ሀሳብ እንዴት ልናገለግል እንችላለን? የእግዚአብሔርንስ ሀሳብ በዘመናቸው ያገለገሉ ሰዎች ሕይወታቸውና ኑሮአቸው ምን ይመስል ነበር? በዚህ ምዕራፍ ውስጥ እነዚህንና የመሳሰሉትን ሀሳቦች በማንሳት እኛም በዘመናችን የእግዚአብሔርን ሀሳብ እንዴት ማገልገል እንደምንችል እንማራለን። በቅድሚያም የእግዚአብሔርን ሀሳብ በዘመናቸው ያገለገሉ ሰዎች እንዴት እንዳገለገሉት እንመለከታለን።

## 1) ዳዊት

ዳዊት በምድር ላይ እንዲኖር በተሰጠው ዘመን ኖሮ ካለፈ ከአንድ ሺ ዓመታት ገደማ በኋላ ስለ ዳዊት አገልግሎት በሐዋሪያው ጳውሎስ የተሰጠው ምስክርነት "ዳዊትም በራሱ ዘመን የእግዚአብሔርን ሀሳብ ካገለገለ በኋላ አንቀላፋ" (የሐዋ. 13:36) የሚል ነበር። ለዳዊት ከተሰጠው ከዚህ ምስክርነት ሦስት ዋና ዋና ነጥቦችን እንመለከታለን። እነዚህም ሦስት ነጥቦች ዳዊት የእግዚአብሔርን ሀሳብ እንዴት ሊያገለግል እንደቻለ ያመለክቱናል።

### ሀ) ዳዊት በራሱ ዘመን አገለገለ

ዳዊት በምድር ላይ እንዲኖር የተሰጠው ጊዜ ውስን መሆኑን በሚገባ ያውቅ ነበር። "እግዚአብሔር ሆይ በራሴ ዘመን እንዳገለግልህ እርዳኝ" ብሎ የሚጸልይ ሰው ነበር። እግዚአብሔር ከእርሱ የሚጠብቅበት በዚያ በራሱ በዳዊት ዘመን እንደሆነ ዳዊት ያውቅ ነበር። ዳዊትም ዘመኑን የዋጀ ጥበበኛ ሰው ነበር። በዘመኑ ሁሉ ጥበበኛ ሆኖ ለመኖርም ያስቻለው፣ ማስተዋሉና

ዘመኑን በሚገባ እንዲጠቀም እግዚአብሔር እንዲረዳው ለዘመኑ
ቅድሚያ ሰጥቶ መጸለዩ ነው።

የዳዊት የሕይወት ሚስጥሩ ምንድር ነው ብለህ ብትጠይቅ ዳዊት
ለሕይወቱ ዘመን ከእግዚአብሔር የጠየቀው አንድ ነገር ብቻ ነበር።
ይህንንም ዳዊት በራሱ አንደበት ሲገልጽ እንዲህ አለ። “አንድ ነገር
ብቻ እንዲሰጠኝ እግዚአብሔርን ለመንሁት፤ የምፈልገውም አንድ
ነገ[illegible] ብቻ ነው፤ ይኸውም፣ በሕይወቴ ዘመን ሁሉ በእግዚአብሔር
[illegible] እንድኖር፣ በዚያም ሆኜ የእግዚአብሔርን ቸርነት እንዳደንቅ፣
አ[illegible]ና[illegible]ም እንድጠይቅ ነው።” (መዝ. 27፡4፣ አዲሱ ትርጉም)።
ዳ[illegible] “በዘመኔ ሁሉ” ብሎ ነበር እግዚአብሔርን የጠየቀው።
“ጀምሬ እስከፈጽም ድረስ በቤትህ አኑረኝ፣ የሀሳብህ አገልጋይ
አድርገኝ” የሚል ነበር የዳዊት ጸሎት።

እግዚአብሔርም ዳዊት እንደጠየቀው ስለመለሰለት “ዳዊት በራሱ
ዘመን አገለገለ” ተብሎ ተመስክሮለታል። አንተ ከእግዚአብሔር
አንድ ነገር ብቻ እንድትጠይቅ ዕድል ቢሰጥህ ምን ትጠይቃለህ?
አስተውል፣ ይህን ዘመንህን መልሰህ አታገኘውም። ወይንም ደግሞ
በዚህ ዘመን ተመልሰህ ልትኖር አይችልም። ይህን ጽሑፍ ስጽፍ
ጥር 30 ቀን 1991 ዓ.ም. ዕለተ እሁድ ከሰዓት በኋላ አሥራ ሁለት
ሰዓት ተኩል ነው። ይህ ሰዓትና ይህ ቀን ተመልሶ እንደማይመጣ
አስተዋልኩ።

ስለዚህም በዚህ ሰዓት ለራሴ የምጸልየው ጸሎት “እግዚአብሔር
ሆይ ይህ ቀን ተመልሶ እንደማይመጣ አወቅሁ። ይህ ቀን በራሴ
ዘመን ከሰጠኸኝ ቀኖች መካከል ቁም ነገር የሠራሁበትና አንተን
ያገለገልኩበት ቀን ይሁን። በዚህን ሰዓት የምጽፈው ይህ መልዕክት
በእኔ ዘመንና በሚቀጥሉት ዘመናት የሚኖሩ ሰዎች በዘመናቸው
አንተን ለማገልገል ጥበበኞች መሆን እንዲችሉ በሕይወታቸው ለውጥ
እንዲያመጣ አንተ ተጠቀምበት። ይህን ቀን ስለሰጠኸኝና በዚህ
ቀን በሕይወት ስላኖርከኝ አመሰግንሃለሁ። በዚህ ቀን በሕይወት
መኖሬ ለአንተ ክብር ይዋል” የሚል ነው።

## ለ) ዳዊት የእግዚአብሔርን ሀሳብ አገለገለ

በምድር ላይ ብዙ ሀሳቦች አሉ። የሰው ሀሳብ፣ የሰይጣን
ሀሳብ፡ የክብር ሀሳብ፣ የዝና ሀሳብ፣ የሀብት ሀሳብ፣ የሥልጣን
ሀሳብ፣ የዕውቀት ሀሳብ፣ ወዘተ። ነገር ግን እነዚህ ምድራዊ
ሀሳቦች ሁሉ ያልፋሉ። ለዘላለም የሚኖረው ግን የእግዚአብሔር





ሀሳብ ብቻ ነው። ሰዎች በተሰጣቸው ዘመን የተለያዩ ሀሳቦችን
ሊያገለግሉ ይችላሉ። እግዚአብሔር እኛ እንድናገለግለው
የሚፈልገው ግን የራሱን ዘላለማዊ ሀሳብ ነው።

ለመሆኑ የእግዚአብሔር ሀሳብ ምንድር ነው? የእግዚአብሔር
ሀሳብ እግዚአብሔር ራሱ የሰውን ሥጋ ለብሶ ወደ ምድር
የመጣበትና ሕይወቱን መሥዋዕት አድርጎ የሰጠበት የወንጌል ሀሳብ
ነው። ይህንንም አምላክ ወደ ምድር መጥቶ የሰውን ሥፍራ
የወሰደበትን ዓላማ ጌታችን ሲናገር “የሰው ልጅ የጠፋውን ሊፈልግና
ሊያድን መጥቷልና” (ሉቃ. 19፡10) ብሏል።

የጠፋውን ለመፈለግና መዳንን ለማወጅ መሄድ ነው
የእግዚአብሔር ሀሳብ። እግዚአብሔር “ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ
ወንጌልንም ለፍጥረት ሁሉ ስበኩ” (ማር. 16፡15) ሲለን ሀሳቡን
ገልጾልናል። እኛም ለእግዚአብሔር ሀሳብ ታዘን፣ የጠፉትን
ለመፈለግ ከቤተክርስቲያን ወጥተን፣ የምሥራቹን ቃል መስማት
ያለባቸው ሰዎች ወዳሉበት ስንሄድ የእግዚአብሔርን ሀሳብ ማገልገል
እንችላለን ማለት ነው። በቤት ውስጥ ያሉ ዘጠና ዘጠኝ በጎችን
ለመከፋፈል መጣላትን ትተን የጠፋውን አንድ በግ ፍለጋ
መሽቀዳደም የእግዚአብሔርን ሀሳብ ማገልገል ነው።

የእግዚአብሔርን ሀሳብ እንዳገለገለ የተመሠከረለት ዳዊት
በዘመኑ ምንም ኃጢአት አልሠራም ማለት አይደለም። ብዙ
ኃጢአቶችን ሠርቷል። ነገር ግን በትህትና ወደ እግዚአብሔር ፊት
ቀርቦ ኃጢአቱን ይናዘዝ ነበር። እንደገናም እግዚአብሔር ሀሳቡን
ማገልገል ወደሚችልበት ንጽህና እንዲመልሰው ይለምን ነበር። ወደ
ትክክለኛው የእግዚአብሔር ሀሳብም ለመግባት “ከአዳኝነትህ
የሚመነጨውን ደስታ መልሰህ ስጠኝ፣ እንድታዘዝህም ፈቃደኛ
አድርገኝ። ከዚህ በኋላ ትእዛዝህን ለኃጢአተኞች አስተምራለሁ፣
እነርሱም ወደ አንተ ይመለሳሉ” (መዝ. 51፡12-13፣ አዲሱ ትርጉም)
ብሎ ይጸልይ ነበር።

ዳዊት ትሁት፣ ልቡ ንጹህና በዘመኑ ሁሉ እግዚአብሔርን
የሚያስደስተውን ነገር ብቻ ለማድረግ የሚፈልግ ሰው ስለነበር
እግዚአብሔር ራሱ ስለ ዳዊት ሲመሰክር “እንደ ልቤ የሆነ ሰው
ፈቃዴንም ሁሉ የሚያደርግ የእሴይን ልጅ ዳዊትን አገኘሁ” አለ።
(1ሳሙ. 13፡14፣ መዝ. 89፡20፣ የሐዋ. 13፡22)።

እግዚአብሔር የልቡን ሀሳብ የሚያገለግሉትን ሰዎች በየዘመናቱ
ፈልጎአል፣ ዛሬም በመፈለግ ላይ ነው። የእግዚአብሔርን ህዝብ

በዘመናቸው እንዲመሩና ሀሳቡንም እንዲያገለግሉ በእግዚአብሔር ተለይተው የነበሩ ካህኑ ዔሊና ሁለት ልጆቹ የእግዚአብሔርን ሀሳብ ትተው የራሳቸውን ክፉ ሀሳብ ባገለገሉ ጊዜ "የታመነም ካህን ለእኔ አስነሣለሁ፣ በልቤም በነፍሴም እንዳለ እንዲሁ ያደርጋል" (1ሳሙ. 2፡35) በማለት እግዚአብሔር የልቡን ሀሳብ የሚያገለግለውን ሰው ይፈልግ እንደነበር እናያለን፡፡

አንተ ዛሬ የምታገለግለው የማንን ሀሳብ ይሆን? እግዚአብሔር ዛሬ ስለአንተ ቢመሰክር ምን የሚል ምስክርነት ይሰጣል ብለህ ታስባለህ? ማንን ማገልገል ወይም የማንን ሀሳብ ማገልገል እንዳለብህ ዛሬ ልታስተካክል ትችላለህ፡፡ በዘመንህ ሁሉ የእግዚአብሔርን ሀሳብ ብቻ ለማገልገል እንድትችል እግዚአብሔር እንዲረዳህ ጸልይ፡፡

## ሐ) ዳዊት ካገለገለ በኋላ አንቀላፋ

በምድራችን ላይ በሕይወታቸው ዘመን አንድም ቁም ነገር ሳይሠሩ የሚሞቱ ሰዎች እጅግ ብዙ ናቸው፡፡ ማንኛውም ዓይነት ሰው ይሞታል፡፡ ጥቁር ነጭ፣ ደሃ ሃብታም፣ የተማረ ያልተማረ፣ በሽተኛ ሐኪም፣ ህፃን አዋቂ፣ ሁሉም ዓይነት ሰው ይሞታል፡፡ ነገር ግን ትልቁ ጥያቄ፣ እግዚአብሔር በሰጣቸው ዘመን ምን ሠርተው ሞቱ? ስማቸው ከመቃብር በላይ የሚኖረው እንዴት ነው? የሚለው ነው፡፡

ዳዊት የሞተው የእግዚአብሔርን ሀሳብ አገልግሎ ነው፡፡ ስለዚህ ነው ዛሬም ዳዊት እግዚአብሔርን ካገለገለበት ከሦስት ሺ ዓመት በኋላም ስለ ዳዊት አገልግሎት የምንናገረው፡፡ ዳዊት ዘመኑን ተጠቀመበት እንጂ በከንቱ አላሳለፈም፡፡ ከመሞታችን በፊት ለዘላለም መታሰቢያ ያለው ቁም ነገር እንድንሠራ እግዚአብሔር ይርዳን፡፡

ሞት ቀኑን ጠብቆ ይመጣል፣ አንተ ግን ዘላለማዊውን የእግዚአብሔርን ሀሳብ ለማገልገል ዛሬ ጀምር፡፡ ሰው እንዴትም ሆኖ ቢኖር፣ እንዴትም ሆኖ ቢሞት ከመቃብር ላይ መጥፎ ታሪክ አይጻፍም፡፡ ሟቹ መጥፎ ታሪክም ቢኖረው ያ መጥፎ ታሪኩ ተረስቶም ይሁን ተሸፍኖ ከመቃብር በላይ ግን መልካም ታሪክ ያኖሩለታል፡፡ ስለዚህም የኑሮአችን ታሪክ መመዘኛ በእግዚአብሔር ፊት የሚጻፈው ታሪካችን እንጂ ከሐውልት ላይ የሚኖረው የተድበሰበሰ ታሪክ አይደለም፡፡ በእግዚአብሔር ፊት ምን ታሪክ





እንዲጻፍልህ ትፈልጋለህ? ይህን ታሪክ ለማስጻፍ ኑሮህን መጀመር ያለብህ ዛሬ ነው፡፡

## 2) ጳውሎስ

በዘመኑ የእግዚአብሔርን ሀሳብ ያገለገለ ሌላ ምሳሌ የሚሆነን ሰው ሐዋሪያው ጳውሎስ ነው፡፡ ሐዋሪያው ጳውሎስ ጌታ ኢየሱስ በደማስቆ መንገድ ተገናኝቶት ራሱን ከገለጠለትና "ይህ በአሕዛብም በነገሥታትም በእስራኤልም ልጆች ፊት ስሜን ይሸከም ዘንድ ለእኔ የተመረጠ ዕቃ ነው" (ሐዋ. 9፡15) በማለት ከላከው ጊዜ ጀምሮ እስከ ዕለተ ሞቱ ድረስ በታማኝነት የእግዚአብሔርን ሀሳብ በማገልገል የኖረ ሰው ነው፡፡ ሕይወቱንም በሙሉ እንዴት እንደኖረ ለመመልከት ሐዋሪያው ስለራሱ ከተናገራቸው ሀሳቦች አንዱን ብቻ ማየቱ በቂ ይሆናል ብዬ አምናለሁ፡፡

"ወደ እስያ ከገባሁበት ቀን ጀምሮ ዘወትር ከእናንተ ጋር እንዴት እንደኖርሁ እናንተ ታውቃላችሁ፤ በአይሁዳውያን ሴራ ምክንያት መከራ ቢደርስብኝም እንኳ በፍጹም ትህትናና በእንባ ጌታን አገለግላለሁ፡፡ በአደባባይም ሆነ በየቤታችሁ ሳስተምራችሁ የሚጠቅማችሁን ሁሉ ነገርሁአችሁ እንጂ ምንም ነገር አላስቀረሁባችሁም፡፡ አይሁዳውያንም ሆኑ አረማውያን ንስሃ ገብተው ወደ እግዚአብሔር እንዲመለሱና በጌታችን በኢየሱስ እንዲያምኑ አስጠነቀቅሁአቸው፡፡ ... እኔ ግን አገልግሎቴን እስክፈጽምና ጌታ ኢየሱስ የሰጠኝን ሥራ እስካከናውን ድረስ፣ ለገዛ ሕይወቴ እንኳ አልሳሳም፤ አገልግሎቴም የእግዚአብሔርን የጸጋ ወንጌል ማብሠር ነው፡፡" (ሐዋ. 20፡18-24፣ አዲሱ ትርጉም፡፡)

ሐዋሪያው ጳውሎስ በገዛ ዘመኑ የእግዚአብሔርን ሀሳብ እንዴት እንዳገለገለ ሲናገር 1ኛ) በፍጹም ትህትና 2ኛ) በታማኝነት 3ኛ) በመከራ በመጽናት 4ኛ) እግዚአብሔር ለጠራው ጥሪ ነፍሱን አሳልፎ በመስጠት 5ኛ) ለወንጌል በመኖር እንደሆነ ይመሰክራል፡፡ ሐዋሪያው ጳውሎስ በዘመኑ ሁሉ የእግዚአብሔርን ሀሳብ እንዲያገለግል የሚገፋፉት ምክንያቶች ምን እንደሆኑ በሚገባ አውቆ የኖረ ሰው ነው፡፡ እነዚህም ምክንያቶች፡-

## ሀ) ከጌታ የተቀበለው አገልግሎት

አገልግሎታችንን ከእግዚአብሔር እንደተቀበልን ማወቅ በዘመናችን ሁሉ እግዚአብሔርን እያየንና እርሱን እየፈራን

እንድናገለግል ያስችለናል፡፡ አገልግሎትን ከእግዚአብሔር እንደተቀበልን ካወቅን በዙሪያችን ያሉ ሁኔታዎች አስቸጋሪ እንኳ ቢሆኑ፣ ዋጋ የሚያስከፍለን ነገር እንኳ ቢበዛ፣ ማንኛውንም ዋጋ ከፍለን አገልግሎታችንን እስከ መጨረሻ ለመፈጸም ቆርጠን እንነሳለን፡፡

ከጌታ እንደተቀበልን ካላወቅን ግን ሰዎች አላንቀሳቅስ ሲሉን ወይም ዋጋ የምንከፍልበት ነገር ሲበዛ ተስፋ መቁረጥና ማጉረምረም ወደ ሕይወታችን ይመጣል፡፡ ነፍሴን በእኔ ዘንድ እንደማትከብር እንደ ከንቱ ነገር እቆጥራለሁ ብለን፣ እንደ ጳውሎስ ለአገልግሎት ዋጋ ለመክፈል ለመዘጋጀት፣ አገልግሎቱን በመጀመሪያ ከእግዚአብሔር እንደተቀበልን እርግጠኞች መሆን ያስፈልጋል፡፡

ሐዋሪያው ጳውሎስን ነፍሱን እንኳን አሳልፎ እስከመስጠት ድረስ በመከራ እንዲጸና ያደረገው፣ አገልግሎቱን የተቀበለው ከእግዚአብሔር እንደሆነ ማወቁ ነው፡፡ አገልግሎቱን ከእግዚአብሔር እንደተቀበለ የሚያውቅ አገልጋይ እግዚአብሔር በሚመራው መንገድ ሁሉ ከመሄድ ወደ ኋላ አይልም፡፡ ማንኛውም ዓይነት መከራ ቢመጣበት አይናወጥም፡፡

## ለ) በጸጋ ያዳነው ወንጌል

ሐዋሪያ ጳውሎስን በዘመኑ የእግዚአብሔርን ሀሳብ እንዲያገለግል የገፋፋው ሌላው ምክንያት በጸጋ ያዳነውን የእግዚአብሔርን ወንጌል ታላቅነት በሕይወቱ መለማመዱ ነው፡፡ ጳውሎስ ከአገልግሎት ሁሉ የሚበልጥብኝ አገልግሎት ወንጌልን የመመስከር አገልግሎት ነው ብሎ ይናገራል፡፡ በደማስቆ መንገድ ላይ ያገኘውን ጌታ ኢየሱስን በፍጹም አይረሳውም፡፡ ለዚህ የጸጋ ወንጌል ሕይወቱን መሥዋዕት አድርጎ ለማቅረብ መዘጋጀቱን ይገልጻል፡፡ እኛ ብዙ ነገር በማገልገል ዘመናችንን ልንጨርስ እንችላለን፡፡ ከአገልግሎት ሁሉ የሚልቅ አገልግሎት ግን ጌታ ኢየሱስን ወደ ምድር መጥቶ ለሰዎች ኃጢአት ራሱን ቤዛ አድርጎ እንዲሰጥ ያስገደደው የጸጋ ወንጌል ነው፡፡

ሐዋሪያው ጳውሎስ ሕይወቱን መሥዋዕት አድርጎ ለመስጠት የተዘጋጀበት ሌላው ምክንያት አገልግሎትን መፈጸም ነው፡፡ "አገልግሎቴን እስክፈጽም ድረስ ለገዛ ሕይወቴ እንኳ አልሳሳም" ይላል፡፡ ሁልጊዜ በፊቱ የሚያስበው አገልግሎትን ስለመፈጸም





ነው፡፡ አገልግሎትን መጀመር አንድ ነገር ሲሆን፣ መፈጸም ግን ሌላ ነገር ነው፡፡

እግዚአብሔር ከእኛ የሚፈልገው አገልግሎትን መጀመር ብቻ ሳይሆን መፈጸምን ነው፡፡ ዋጋና ሽልማት ያለው በመፈጸም እንጂ በመጀመር አይደለም፡፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ፣ በቤተክርስቲያን ታሪክ እንዲሁም በዘመናችንም በምናይበት ጊዜ አገልግሎት ጀምረው የፈጸሙና ያልፈጸሙ ብዙ ሰዎች አሉ፡፡

በጥሩ አነሳስ ጀምረው በመጥፎ አወዳደቅ የጨረሱ ብዙ ናቸው፡፡ እንደ ንጉሥ ሳኦል ያሉ በትህትና ጀምረው በትዕቢት የፈጸሙ፣ እንደ ንጉሥ ሰለሞን ያሉ በመንፈስ ጀምረው በሥጋ የፈጸሙ፣ እንደ ዴማስ ያሉ ጌታን በመውደድ ጀምረው የአሁኑን ዓለም በመውደድ የጨረሱ አያሌ ሰዎች አሉ፡፡ እግዚአብሔር ሲጠራን አገልግሎትን ጀምረን እንድንፈጽም ነው፡፡

አገልግሎትን ጀምረው የፈጸሙትን ሰዎች ሕይወት በምንመለከትበት ጊዜ እያንዳንዱ ሰው የመፈጸም ዓላማን መሠረት አድርጎ የተነሣውንና ምሳሌ ሆኖ አገልግሎትን የፈጸመውን ክርስቶስን በማየት የሮጡ፣ ሥጋቸውንና ምድራዊ ፍላጎታቸውን ለቀዳሚውና ለሰማያዊው ሀሳብ አስገዝተው የኖሩ እንደሆኑ እንመለከታለን፡፡ ለምሳሌ ያህል አገልግሎት የፈጸሙትን የጥቂቶቹን ሕይወት ቀጥሎ ብንመለከት በራሳቸው ዘመን የእግዚአብሔርን ሀሳብ አገልግለው ሊፈጽሙ የቻሉበት ምክንያቱ ወይም ሚስጥሩ ምን እንደሆነ እንረዳለን፡፡

## ጌታ ኢየሱስ እንዴት ፈጸመ?

ጌታ ኢየሱስ አገልግሎትን ጀምሮ ለመፈጸም ትልቁ ምሳሌያችን ነው፡፡ ጌታችን ኢየሱስ በመስቀል ላይ ሆኖ "ተፈጸመ" (ዮሐ. 19:30) ብሎ የተናገረበት እንዲሁም በአገልግሎቱ ያፈራቸውን ደቀ መዛሙርት ለአባቱ ሲያስረክብ "እኔ ላደርገው የሰጠኸኝን ሥራ ፈጽሜ በምድር አከበርሁህ" (ዮሐ. 17:4) ለማለት የቻለበት ምክንያት ሕይወቱን በሙሉ አገልግሎትን ለመፈጸም በመኖሩ ነበር፡፡

የጌታ ኢየሱስንም የዕለት ተዕለት ሕይወቱን የሚገልጹ ከዮሐ. 4:34 እና ዮሐ. 9:4 የተሻሉ ጥቅሶችን አናገኝም ብዬ አስባለሁ፡፡ "የእኔስ መብል የላከኝን ፈቃድ አደርግ ዘንድ ሥራውንም

እፈጽም ዘንድ ነው፡፡" (ዮሐ. 4፡34) "ቀን ሳለ የላከኝን ሥራ ላደርግ ይገባኛል፤ ማንም ሊሠራ የማይችልባት ሌሊት ትመጣለች፡፡" (ዮሐ. 9፡4)

ጌታ ኢየሱስ የእያንዳንዱን ቀን ሕይወቱንና ኑሮውን በዚህ ቃል መመሪያ በመኖር አገልግሎትን መፈጸም ማለት ምን እንደሆነ በትክክል አሳይቶናል፡፡ እኛም እንደ ጌታ ኢየሱስ ዓላማችን አገልግሎትን መፈጸም ከሆነ በየዕለቱ ሕይወታችንን የሚገዛ የሕይወት መመሪያ ሊኖረን ያስፈልጋል፡፡ የእግዚአብሔርን ሀሳብ ማገልገል፤ አገልግሎትንም ለመፈጸም መኖርና ከሌሎቹ ጉዳዮች ይልቅ በሕይወታችን ቅድሚያ ለምንሰጣቸው ነገሮች መኖር፤ እንዲሁም ዓላማችንን ከግብ ለማድረስ መኖር ያስፈልጋል፡፡

## ጳውሎስ እንዴት ፈጸመ?

ሐዋርያው ጳውሎስ አገልግሎቱን ስለመፈጸሙ "እኔ ግን መሥዋዕት ለመሆን ተቃርቤአለሁ፤ ከዚህ ዓለም ተለይቼ የምሄድበት ጊዜም ደርሶአል፤ ጦርነትን በመልካም ተዋግቻለሁ፤ ሩጫውን እስከ መጨረሻው ሮጫለሁ፤ ሃይማኖትን ጠብቄአለሁ፡፡ ከእንግዲህ ወዲህ የጽድቅ አክሊል ተዘጋጅቶ ይጠብቀኛል፤ ይህንንም አክሊል ቅን ፈራጅ የሆነው ጌታ በዚያን ቀን ይሰጠኛል፤ ይህንንም ለእኔ ብቻ ሳይሆን የእርሱን መገለጥ ለሚወድዱ ሁሉ ይሰጣቸዋል፡፡" (2ኛ ጢሞ. 4፡6-8፤ አዲሱ ትርጉም) በማለት ይመሰክራል፡፡ ለመሆኑ ሐዋሪያው ጳውሎስ አገልግሎቱን ለመፈጸም የኖረው እንዴት ነበር?

## ሀ) ሥጋውን ለእግዚአብሔር ፈቃድ በማስገዛት

ሐዋሪያው ጳውሎስ በዘመኑ የእግዚአብሔርን ሀሳብ ሊያገለግልና አገልግሎቱንም ሊፈጽም የቻለው ሥጋውን ለመንፈስ ቅዱስ በማስገዛት፤ እንዲሁም ሩጫውን ለማሸነፍ በመሮጡ ነው፡፡ ይህንንም ዓላማውን ለቆሮንቶስ ምዕመናን በጻፈው መልዕክቱ በግልጽ አስቀምጦታል፡፡

"ይህን ሁሉ ማድረጌ የምሥራቹን ቃል በረከት ለመካፈል፤ ስለ ምሥራቹ ቃል ብዬ ነው፡፡ .... በሩጫ የሚወዳደሩ ሁሉ አድካሚ ልምምድ ያደርጋሉ፤ እነርሱ እንዲህ የሚደክሙት የሚጠፋውንና ጊዜያዊ የሆነውን አክሊል ለማግኘት ነው፤ እኛ ግን የምንደክመው የማይጠፋውንና ዘላለማዊ የሆነውን አክሊል ለማግኘት





ነው፡፡ እኔ ግን ግብ እንደሌለው ሰው በከንቱ አልሮጥም፤ ከነፋስ ጋር እንደሚታገል በከንቱ የምታገል ሰው አይደለሁም፡፡ ስለዚህ ሌሎችን ወደ ውድድር ከጠራሁ በኋላ እኔ ራሴ ከውድድሩ ውጭ ሆኜ እንዳልገኝ ሰውነቴን እየተቆጣጠርሁ እንዲታዘዝልኝ አደርገዋለሁ፡፡" (1ቆሮ. 9፡23-27፤ አዲሱ ትርጉም፡፡)

የእግዚአብሔርን ሀሳብ ማገልገል የምትችለው ለምድራዊና ለሥጋዊ ሀሳብ እምቢ ብለህ ወደ ዓላማህ ስትሮጥ ነው፡፡

## ለ) መከራን በትዕግስት በማሳለፍ

"አንተ ግን ትምህርቴንና አካሄዴን ሀሳቤንም እምነቴንም ትዕግስቴንም ፍቅሬንም መጽናቴንም ስደቴንም መከራዬንም ተከተልህ፤ በአንጾኪያና በኢቆንዮን በልስጥራንም የሆነብኝን የታገስሁትንም ስደት ታውቃለህ፡፡" (2ጢሞ. 3፡10-11)

የእግዚአብሔርን ሀሳብ ማገልገል የምትችለው በመከራ ውስጥ ጸንተህ ለጠራህ አምላክ ታማኝ በመሆን ነው፡፡ ትዕግስት የእግዚአብሔርን ሀሳብ ለማገልገልና አገልግሎትንም ለመፈጸም እጅግ አስፈላጊ ነገር ነው፡፡ ማሸነፍ የሚቻለውና ታላላቅ ነገሮችም የሚከናወኑት በትዕግስት ነው፡፡

## ሐ) ለጽድቅ አክሊል በመሮጥ

"... ኢየሱስ ክርስቶስ እኔን የእርሱ አድርጎ ያዘጋጀልኝን ሽልማት ለማግኘት ወደፊት በመሮጥ እተጋለሁ፡፡ ወንድሞቼ ሆይ! ገና ወደዚያ እንደደረስሁ አልቆጥርም፤ ነገር ግን አንድ ነገር አደርጋለሁ፤ ይኸውም በስተኋላዬ የነበረውን እየረሳሁ፤ በፊቴ ያለውን ለመያዝ እተጋለሁ፡፡ ሽልማቴንም ለማግኘት በፊቴ ወዳለው ግብ እሮጣለሁ፡፡" (ፊል. 3፡12-14፤ አዲሱ ትርጉም፡፡)

የእግዚአብሔርን ሀሳብ ለማገልገል የምትችለው እስከዛሬ ለአገልግሎት ስትል የከፈልከውን ዋጋ በመቁጠር ሳይሆን በየዕለቱ ለአዲስ አገልግሎት በመዘጋጀት ነው፡፡ ለሽልማትና ወደ ፊት በመሮጥ ማገልገል አገልግሎትን የመፈጸም ትልቁ መሣሪያ ነው፡፡

## መ) አገልግሎትን ለመፈጸም በማገልገል

"አሕዛብ እንዲታዘዙ ክርስቶስ በቃልና በሥራ፣ በምልክትና በድንቅ ነገር ኃይል፣ በመንፈስ ቅዱስም ኃይል በእኔ አድርጎ ከሠራው በቀር ምንም ልናገር አልደፍርም ስለዚህ ከኢየሩሳሌም ጀምሬ እስከ እልዋሪቆን ድረስ እየዞርሁ የክርስቶስን ወንጌል ፈጽሜ ሰብኬአለሁ፡፡" (ሮሜ. 15፡18-19)

የምታገለግለው ለመፈጸም ነውን? የማገለግለው ለመፈጸም ነው የምትለው፣ እስከ መጨረሻው ጸንተህ ለመፈጸም ቆርጠህ ስታገለግል ብቻ ነው፡፡ ስለዚህ አንተም አገልግሎትህን ለመፈጸም አገልግል፡፡

## ሠ) ወንጌልን ሌላው ሰው ባልሰበከበት በመስበክ

"የዘወትር ምኞቴም ሌላው ሰው በጣለው መሠረት ላይ መገንባት ሳይሆን፣ የክርስቶስ ስም ባልተሰማበት ስፍራ ሁሉ መልካሙን ዜና ማብሠር ነው፡፡" (ሮሜ. 15፡20፣ አዲሱ ትርጉም)

የእግዚአብሔርን ሀሳብ በዘመንህ ማገልገል የምትችለው ወንጌል በተሰበከበት ሥፍራ ደግመህ ለመስበክ ወይም በቤት ውስጥ ያለውን የእግዚአብሔርን መንጋ እኔ "የተሻለ ትምህርት አስተምራለሁ" በማለት ከሌላ ጋር እየተጣለህ ሳይሆን ወንጌል ፈጽሞ ወዳልተሰበከበት ሄደህ በጨለማ ውስጥ ላሉ ለመጀመሪያ ጊዜ የወንጌሉን የምሥራች ስትነግራቸው ነው፡፡

## ረ) ለወንጌል ቅድሚያን በመስጠት

"የቀረውንም ነገር ሳልቆጥር ዕለት ዕለት የሚከብድብኝ የአብያተክርስቲያናት ሁሉ አሳብ ነው፡፡" (2ቆሮ. 11፡28) ሌላውንም ሁሉ ነገር የሚላቸው የሚመካባቸውን ነገሮች ሳይቆጥር ዕለት ዕለት የሚያሳስበው ለዓላማው መጨከን፣ ተልዕኮውን መፈጸም፣ የተሰጠውን አደራ መጠበቅ፣ መክሊቱን ማትረፍና ወንጌልን መመስከር ናቸው፡፡

የተጠራነው የእግዚአብሔርን ሀሳብ ለማገልገል ነው፡፡ ሀሳቡንም ለማገልገል መጀመራችን ሳይሆን ትልቁ ቁም ነገር አገልግለን መፈጸማችን ነው፡፡ ለመፈጸም የምንችለው ደግሞ በትህትና ጀምረን በትህትና ስንጨርስ፣ በመንፈስ ቅዱስ ጸጋና ቅባት ጀምረን በዚያው





ጸጋና ቅባት ስንጨርስ፣ እግዚአብሔርን በማክበር ጀምረን በማክበር ስንጨርስ ብቻ ነው፡፡

እኔነት፣ የገንዘብ ፍቅር፣ ከእግዚአብሔር ክብር ይልቅ የራስን ክብር መፈለግ፣ ከሰማያዊ ራዕይ ይልቅ ምድራዊ ሀሳብ ሕይወታችንን መግዛት ሲጀምር፣ ወደ ፍጻሜ ሳንደርስ በመንገድ ላይ እንቀራለን፡፡ የተጠራነው እግዚአብሔርን ለማገልገል ነው፡፡ መኖር ያለብንም ለእግዚአብሔር መንግስት ነው፡፡

ወገኔ ሆይ ዘመን ተሰጥቶሃል፣ በዘመንህ ደግሞ ሌላውን ሁሉ ሀሳብ ትተህ የእግዚአብሔርን ሀሳብ ብቻ አገልግል፡፡ የጽድቅ አክሊልህንም ከእግዚአብሔር ብቻ ጠብቅ፡፡ ክርስቲያን ሆነህ ለመኖር ከፈለግህ ወንጌልን እያገለገልህ ኑር፡፡ አንተ የወንጌል ባለአደራ ነህ፣ ይህንንም አደራ በዘመንህ ሁሉ በታማኝነት ፈጽም፡፡ እግዚአብሔር ዘመንህን ይባርክ፡፡ አሜን፡፡

## ዋቢ መጻሕፍት (Bibliography)


Bright, Bill. *Witnessing without Fear: How to share your faith with confidence.* San Bernardino, CA: Here's Life Publishers, 1987.

________. *The Coming Revival: America's Call to Fast, Pray, and "Seek God's Face."* Orlando, Florida: New Life Publications, 1995.

________. *Come Help change the World.* San Bernardino, CA: Here's Life Publishers, 1985.

Gordon, S.D. *What it will take to change the World.* Grand Rapids, Michigan: Baker Book House, 1979.

Stot, John. *Christian Mission in the Modern World.* Downers Grove, Illinois: Intervarsity Press, 1975.

Mahoney, Ralph. *The Shepherd's staff.* San Fernando, CA: World Map, 1993.

Haggai, John. *Lead on: Leadership that endures in a changing World.* Waco, Texas: Word Books Publisher, 1986.

Foltz, Howard. *Triumph: Missions Renewal for the Local Church.* Joplin, Missouri: Mesenger Publishing House, 1994

# ተጨማሪ መግለጫ (Appendix)

በመንፈሳዊ ሕይወትና በአገልግሎትህ ለማደግ፣ እንዲሁም ሌሎችን ሰዎች በወንጌል ሥርጭትና በደቀመዝሙርነት ለማሰልጠን የሚጠቅሙ፤ የተለያዩ ትራክቶች፣ መጽሔቶች መጻሕፍት፣ የቴፕና የቪዲዮ ካሴቶች በተለያዩ የብሔረሰብ ቋንቋዎች የተተረጐሙ የኢየሱስ (JESUS) ፊልሞች በግሬት ኮሚሽን ሚኒስትሪ ቢሮዎች ልታገኝ ትችላለህ ::

እነዚህንም ማቴሪያሎች ወንጌልን ለሌሎች በማድረስ፣ የክርስቶስን ደቀመዛሙርትን በማፍራትና ሌሎችም ይህንኑ እንዲያደርጉ በማሰልጠን ልትጠቀምባቸው ትችላለህ :: አስፈላጊም ሆኖ ሲገኝ የግሬት ኮሚሽን ሚኒስትሪ አገልጋዮች እስካለህበት ድረስ በመምጣት ከአንተ ጋር አብረው ክርስቲያኖችን በወንጌል ስርጭት ለማሰልጠን፣ ወንጌልን እንዲመሰክሩ ለማድረግና የኢየሱስን ፊልም ለማሳየት ስለሚችሉ ደብዳቤ በመጻፍ ወይም የግሬት ኮሚሽን ሚኒስትሪ ቢሮዎች ወደሚገኙበት በመሄድ ልትጠይቃቸው ትችላለህ ::

በግሬት ኮሚሽን ሚኒስትሪ የሚገኙ ዋና ዋና ማቴሪያሎች የሚከተሉት ናቸው ::

1. የአራቱ መንፈሳዊ ሕጎች ትራክት፣ መጽሔትና የቴፕ ካሴት
2. በመንፈስ ቅዱስ የተሞላ ሕይወት ትኖራለህን የሚል? ጥራዝ
3. መሠረታዊ የወንጌል ስርጭትና የደቀመዝሙር ማሰልጠኛ ጥራዝ ቁጥር 1፣ ቁጥር 2፣ ቁጥር 3
4. ከፍተኛ የወንጌል ሥርጭትና የደቀመዝሙር ማሰልጠኛ መጽሔት ቁጥር 1፣ ቁጥር 2፣ ቁጥር 3
5. የክትትል ትምህርት ጥራዞች ከቁጥር 1-6
6. የተለያዩ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት መጻሕፍት

7. የኢየሱስ ፊልም በዋና ዋና የአገሪቱ ብሔረሰብ ቋንቋዎች በቪዲዮ ካሴትና በፕሮጀክተር

8. የተለያዩ መንፈሳዊ ፊልሞች (ለወንጌል ሥርጭትና ለመንፈሳዊ ሕይወት ዕድገት የሚጠቅሙ)

9. ምዕመናንን ለወንጌል ሥራ የሚቀሰቅሱና ራዕይ የሚያስጨብጡ ተከታታይ ትምህርቶች (በታላቁ ተልዕኮ አገልጋዮች የሚሰጡ)

10. በመሪነት ላይ የሚሰጡ ተከታታይ ትምህርቶች

11. ገንዘብን ለእግዚአብሔር ሥራ በመስጠት ላይ ያተኮሩ ተከታታይ ትምህርቶች

12. የተለያዩ የመልዕክትና የመዝሙር የቴፕና የቪዲዮ ካሴቶች ይገኛሉ

ከዚህ በታች በተዘረዘሩት የታላቁ ተልዕኮ አገልግሎት ቢሮዎች በማንባር በመገኘት ወይም በደብዳቤ በመጠየቅ የምትፈልጋቸውን ማቴሪያሎች ልታገኝ ትችላለህ፡፡ በተጨማሪም በኢትዮጵያ ውስጥ ወንጌልን የምናሰራጨው እንደ አንተ ያሉ የወንጌል ቅናት ያላቸው ክርስቲያኖች በሚሰጡት የገንዘብ ድጋፍ ስለሆነ አንተም እግዚአብሔር ይህንኑ በልብህ ካስቀመጠ የታላቁ ተልዕኮ አገልግሎትን በገንዘብና በማንኛውም በምትችለው ሁሉ ልታገለግል ትችላለህ፡፡ ይህንንም አገልግሎት በገንዘብ የሚደግፉ ብዙ ክርስቲያኖች አሉ፡፡

መደበኛ የአገልግሎቱ ደጋፊዎች ሆነው ገንዘባቸውን ለወንጌል አገልግሎት በየወሩ የሚሰጡ እንዲሁም እግዚአብሔር እንዳስቻላቸው በዓመት አንድ ጊዜ፣ ሁለት ጊዜና ከዚያም በላይ የሚሰጡ ራሳቸውን ለእግዚአብሔር የሰጡ ብዙ ወገኖች ስላሉ አንተም ከዛሬ ጀምሮ የአገልግሎቱ ደጋፊ ልትሆን ትችላለህ፡፡ የእግዚአብሔርን ሀሳብ በዘመናችን ማገልገል የምንችለው በአንድነትና በመስጠት ስንነሳ ነው፡፡ እግዚአብሔር ሕይወትህን፣ ኑሮህንና አገልግሎትህን ይባርክ፡፡



የግሬት ኮሚሽን ሚኒስትሪ - ኢትዮጵያ ቢሮዎች አድራሻ፡-

<u>*ዋናው ቢሮ፡-*</u>

አዲስ አበባ
የመ.ሣ.ቁ. 41303

<u>*ቅርንጫፍ ቢሮዎች፡-*</u>

አዋሣ
የመ.ሣ.ቁ. 359

ባህር ዳር
የመ.ሣ.ቁ. 1158

ጅማ
የመ.ሣ.ቁ. 1182

ሐረር
የመ.ሣ.ቁ. 808